# 4

# መልእክቶች፣ የሥነ አፈታት ጥያቄዎች

እሁን ቀደም ሲል የሥነ አፈታት ጥያቄዎች ወዳልናቸው ነገሮች ደርሰናል። እነዚህ ምንባቦች ለእኛ የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው? ይህ የሁሉም ነገር እምብርት ሲሆን፥ ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ሐቲት ቀላል ነው ማለት ይቻላል። ሐቲት ላይ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ አለመስማማት ቢኖርም እንኳ ብዙዎቹ ምሁራን በፍች ዳርቻዎች ላይ ይስማማሉ። ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ዓውዶች የሚያስቀምጧቸው ድንበሮች አሉ። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ እርሱና አንባቢዎቹ ሰምተው ስለማውያውቋቸው ነገሮች ሊናገር አይችልም ነበር። ይህም ማለት የመልእክቱ ፍች ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት ተደራሲያን የሚስማማ ነው ማለት ነው።

የአፈታት ጥበብ (ለዘመናችን ዓውድ የቃሉን ፍች ለመስማት መማር) ግን እንዲህ ዓይነት ገደብ ያለው አይመስልም። ስለ ሐቲት ምንም ባያውቁ እንኳ ሰዎች ሁሉ ሥነ አፈታትን ያካሂዳሉ። በክርስቲያኖች መካከል ብዙ ልዩነቶች እንዳሉ ግልጽ ነው። ከዚህ በላይ የሚገርመው ደግሞ ከሚታወቁት የበለጡ ልዩነቶች አለመኖራቸው ነው። ለዚህም ምክንያቱ በግልጽ ባንለየውም የጋራ የሆነ የሥነ አፈታት መሠረት መኖሩ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ልናከናውነው የምንፈልገው በመጀመሪያ ደረጃ የብዙ ሰዎችን የጋራ የአፈታት ጥበብ መዘርዘር፥ ደካማና ጠናካራ ጎኑን ማሳየት፥ አሳቦችን መሰንዘርና ይኸው የጋራ የአፈታት ጥበብ ብቃት በሚያጣባቸው ነጥቦች ላይ መርሆዎችን መስጠት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመታዘዝ ለወሰኑ ክርስቲያኖች ትልቁ ችግር የባሕላዊ አንጻራዊነት ጉዳይ ነው። ባሕላዊ በመሆኑ ከአንደኛው ምእተ ዓመት ላይ የሚያበቃውና ባሕልን አልፎ ለሁልጊዜም የእግዚአብሔር ቃል የሚሆነው የትኛው ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ቀላል አይደለም። በዚህ ምዕራፍ ይህንን ጥያቄ በስፋት እንዳስሰዋለን።

## የጋራ ሥነ አፈታት

«ሥነ አፈታት ደግሞ ምን የሚሉት ነው?» ብለው ከሚጠይቁት ወገን ብትሆንም እንኳ ሁልጊዜም ሥነ አፈታት እንደምታካሂድ ግልጽ ነው። ሁላችንም መልእክቶችን በምናነብበት ጊዜ የምናደርገው ነገር ምንድን ነው? በቀላሉ የጋራ ግንዛቤያችንን በመጠቀም ምንባቡን

ለራሳችን ሁኔታ እንጠቀምበታለን። ከእኛ ሕይወት ጋር የሚዛመድ የማይመስለውን ደግሞ ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት እንተወዋለን።

ለምሳሌ፥ ምንባቡ በትእዛዛዊ አንቀጽ የተቀመጠ ቢሆንም እንኳ ማናችንም የጳውሎስን ልብስ ከአክርጳ አምጥተን ወደታሰረበት ሮም አገር ለመውሰድ ጢሮአዳ እንሄድ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተጠርተናል ብለን አናስብም (2ኛ ጢሞ. 4፡13)። ነገር ግን ከዚያው መልእክት ውስጥ እግዚአብሔር «እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር» ሆነው መከራን እንዲቀበሉ እንደሚያስተምራቸው ብዙ ክርስቲያኖች ያምናሉ (2፡3)። ብዙዎቻችን መልእክቱን ለመታዘዝ በምንሞክርበት ጊዜ የሚያጋጥሙን ትግሎች ሊኖሩ ቢችሉም፥ ማናችንም ስለ እነዚህ ሁለት ምንባቦች ሚና ጥያቄዎችን አናነሣም።

እዚህ ላይ በመልእክቶች ውስጥ የሚገኙ ብዙ አሳቦች ከጋራ ሥነ አፈታት ጋር እንደሚስማሙ መገንዘቡ ተገቢ ነው። የብዙዎች ምንባቦች ትኩረት አንድን ነገር የማድረግ ወይም ያለማድረግ ጉዳይ ሳይሆን፥ የማሳሰብ ጥሪ ነው። «እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ» (2ኛ ጴጥ. 1፡15)።

ችግሮቻችንና ልዩነቶቻችን በእነዚህ ሁለቱ መካከል የሚገኙ ናቸው። ይህም አንዳንዶቻችን የተጻፈውን በትክክል መታገዝ አለብን ስንል፥ ሌሎቻችን ግን እርግጠኞች አለመሆናችንን እንድንናገር አድርጎናል። እዚህ ላይ የሥነ አፈታት ችግሮቻችን ብዙዎች ቢሆኑም፥ ሁሉም ከአንድ ነገር ማለትም ከቀጣይነት እጦት ጋር የሚዛመዱ ናቸው። ይህ የጋራ ሥነ አፈታት ትልቁ ህፀፅ ነው። ሆን ብለን ባናደርገውም መልእክቶችን በምናነብበት ጊዜ ሥነ መለኮታዊ ውርሳችን፥ የቤተ ክርስቲያን ትውፊታችን፥ ባሕላዊ ግብረገቦቻችን ወይም የህላዌ ስጋቶቻችን እዚያው ውስጥ ይደባለቃሉ። ይህም ሁሉ ምርጫን ወይም በተወሰኑ ምንባቦች ዙሪያ መሽከርከርን ያስከትላል።

ለምሳሌ፥ የአሜሪካ ወንጌል አማኞች ወይም አክራሪ ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡3 እና 4፡13 ካቀረብነው አሳብ ጋር እንደሚስማሙ ግልጽ ነው። ነገር ግን ከእነዚሁ ክርስቲያኖች ብዙዎች በአካባቢያቸው ተገፋፍተው 1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡23ን ላለመታዘዝ ይሟገታሉ። «ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ።» በዚያን ጊዜ ውኃ መጠጣቱ ለጤንነት ጥሩ ስላልነበር ይህ ለጢሞቴዎስ የተላለፈ መልእክት እንጂ ከእኛ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ሲሉ ይከራከራሉ። እንዲያውም «ወይን» የተባለው ከወይን ዘለላ የተዘጋጀ ጭማቂ ነው የሚሉም አሉ። መጭመቂያና ማቀዝቀዣ በሌሉበት ሁኔታ ግን ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ከዚሁ ጋር

ለጢሞቴዎስ የተሰጠው ትእዛዝ (2ኛ ጢሞ. 3፡14–16) ለሁሉም ክርስቲያኖች እያገለገለ የወይን ጠጅ ጉዳይ እኛን የማይመለከተን ለምንድን ነው? ልብ በል፤ አንድ ሰው 1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡23 ከእኔ ሕይወት ጋር ግንኙነት የለውም ብሎ ሊያልፍ ይችላል። ጥያቄው ግን ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉት የሥነ አፈታት መሠረቶች የትኞቹ ናቸው? የሚል ይሆናል።

ወይም ደግሞ በ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ አብዛኞቹ በተለምዶ ቤተ ክርስቲያን አዘውታሪዎች ከ«ኢየሱስ ሕዝቦች» (Jesus People) ተከታዮች ጋር ያሳለፉትን አስቸጋሪ ውዝግብ መመልከት ይቻላል። በ1960ዎቹ የሂፒ ባሕል የወንዶች ፀጉርን ማስረዘም የአዲስ ምዕራፍ ምልክት ሆኖ ነበር። «ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት. . . ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን?» የሚለውን የ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡14 ምንባብ ለሚያውቁት ክርስቲያኖች ይህንን ማድረግ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ መስሎ ታየ። ነገር ግን የወጣቱን ባሕል በመቃወም ይህንን ምንባብ ይጠቅሱ የነበሩት ብዙዎቹ ሰዎች ክርስቲያን ሴቶች (ቁ. 15ን ጥሰው) ፀጉራቸውን ሲቆረጡ፥ በአምልኮ ጊዜ ፀጉራቸውን ሳይሸፈኑ ሲቀሩ እየተመለከቱ ይታገሡ ነበር። በዚህም ተፈጥሯዊ ባልሆነው ፀጉርን የመቆረጥ ተግባር «ተፈጥሮን» መቀዳጀት እንደተቻለ አላሰቡም ነበር።

እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ለእያንዳንዳችን የጋራ ግንዛቤን ስለሚያስተምሩ ነገሮች ጠቃሚ ሁኔታዎችን ያሳያሉ። ነገር ግን የጋራ ግንዛቤን የሚያስተምሩ ሌሎች ነገሮችም አሉ። ለምሳሌ፥ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት። በብዙ ወንጌል አማኝ አብያተ ክርስቲያናት በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ውስጥ የሚገኙት ነገሮች በአብዛኛው ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ጋር እንደማይስማሙ እየተነገረ ነገር ግን ሴቶች በቤተ ክርስቲያን እንዳይናገሩ (14፡34–35) የሚከለከሉት ለምንድን ነው? ከ1–5፥ 25–33 እና 39–40ን የመሳሰሉ ትንቢትን ስለ መናገርና በልሳን ስለ መናገር መመሪያ የሚሰጡ ምንባቦች ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት ብቻ እንደሚያገለግሉ እየተነገረ፥ ቁጥር 34–35 ለሁሉም ባሕሎችና ጊዜያት እንደሚያገለግሉ የሚገለጸው እንዴት ነው?

በተጨማሪም፥ ለሃያኛው ምእተ ዓመት ክርስቲያኖች የራሳቸውን የቤተ ክርስቲያን ትውፊት በ1ኛ ጢሞቴዎስና ቲቶ ላይ መጫኑ እንዴት ቀላል እንደሆነ ልትመለከት ትችላለህ። ነገር ግን ከእነዚህ ምንባቦች ጋር የሚመሳሰል ብዝሃ አመራር ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎች አይደሉም (1ኛ ጢሞ. 5፡17፤ ቲቶ 1፡5፤ ጢሞቴዎስ ነገሮችን እንዲያስተካክል በጳውሎስ የተወከለ አገልጋይ እንጂ መጋቢ አልነበረም።) እንዲሁም የ1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡3–15ን

መመሪያዎች ተከትለው መበለቶችን የሚመግቡ አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎች አይደሉም።

ቀደም ሲል የያዝናቸው ሥነ መለኮታዊ አሳቦች ብዙዎቻችን እነዚህኑ አሳቦች ወደ ምንባቦቹ አስገብተን እንድናነብና ሌሎቹን ግን እንድናገል እንደሚያደርጉን አስተውለሃል? አንዳንድ ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያኖች ሕጻናትን ለማጥመቅ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡16፤ 7፡14 ወይም ቆላስይስ 2፡11-12 የመሳሰሉትን ምንባቦች ድጋፍ ሲጠቅሱ፥ ሁለት ደረጃዎች ላሉት ዳግም ምጽአት 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1ን፥ ወይም ቅድስና ሁለተኛው የጸጋ ተግባር ስለመሆኑ ቲቶ 3፡5ን አስደግፈው ሲያስተምሩ ይደነቃሉ። በአሜሪካ ባሕል የአማኞችን ነፃ ፈቃድና ኃላፊነት ለማሳየት እንደ ሮሜ 8፡30፤ 9፡18-24፤ ገላትያ 1፡15፤ ኤፌሶን 1፡4-5 የመሳሰሉትን ምንባቦች ድጋፍ ሰጪነት መጠቀሙ ለብዙዎች አሳፋሪ ነገር ነው። ሌሎች ክርስቲያኖችም በራሳቸው መንገድ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-13፤ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡20-22 እና ዕብራውያን 6፡4-6ን ይጠቀማሉ። እንደ አስተማሪዎች ይህን ልማድ የሚከተሉ ተማሪዎች የእነዚህን ምንባቦች ፍች ሳይሆን ለምንባቦቹ «እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ» ሲጠይቁ አስተውለናል።

ካለፉት ጥቂት አንቀጾች ወዲህ ብዙ ወዳጆቻችንን አጥተን ይሆናል። ነገር ግን ችግሩን እንዴት ጠልቆ መመልከት እንደሚቻልና ክርስቲያኖች በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ እንዴት እርስ በርሳቸው መነጋገር እንደሚገባቸው ለማሳየት እየሞከርን ነው። እንግዲህ፥ ለመልእክቶች ይበልጥ ቀጣይነት ያለው ሥነ አፈታት ለመመሥረት ምን ዓይነት መመሪያዎች ያስፈልጋሉ?

## መሠረታዊው ደንብ

በምዕራፍ አንድ *አንድ ምንባብ ለደራሲው ወይም ለተደራሲያኑ ያላስተላለፈውን መልእክት ለእኛ ሊያስተላልፍ አይችልም* የሚል መሠረታዊ ደንብ መጥቀሳችንን ታስታውሳለህ። ለዚህ ነው ሁልጊዜም ሐቲት መቅደም ያለበት። ይህ አንዳንድ የፍች ገደቦችን ስለሚመሠርት በተለይ በዚህ ስፍራ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው። ይህ ደንብ ሁልጊዜም አንድ ሰው የአንድን ምንባብ ፍች እንዲያውቅ አይረዳውም። ነገር ግን ምንባቡ ሊያስተላልፍ የማይችላቸውን ፍችዎች ዳርቻ ለመገደብ ይረዳል።

ለምሳሌ፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 የተጠቀሱትን መንፈሳዊ ስጦታዎች ስለ መፈለግ የቀረቡትን ትእዛዛት ላለመከተል በምክንያትነት የሚጠቀሰው «ፍጹም የሆነ ሲመጣ ተከፍሎ የነበረው ይሻራል» (1ኛ ቆሮ. 13፡10) ለሚለው ጥቅስ የሚሰጠው ትርጉም ነው። ፍጹም የሆነው በአዲስ ኪዳን መልክ ስለ መጣ ተከፍሎ የነበረው (ትንቢትና

ልሳን) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማገልገል እንደ ታቀበ የሚያስረዱ ወገኖች አሉ። ነገር ግን ይህ ምንባቡ ሊያስተላልፍ ከማይችላቸው ፍችዎች አንዱ ነው። ምክንያቱም ጥሩ ሐቲት ከዚህ ፍች ላይ አያደርሰንምና። ጳውሎስ ይህንን አሳብ ሊያስተላልፍ የሚችልበት ምንም አማራጭ መንገድ የለም። በዚያን ጊዜ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ፊት አዲስ ኪዳን እንደሚዘጋጅ አያውቁም ነበር። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ አማኞቹ ጭራሽ ስለማያውቁት ነገር እንዲጽፍ የሚያሳስብበት ምክንያት አይኖረውም።

## ሁለተኛው ደንብ

በመሠረቱ ሁለተኛው ደንብ የጋራ የአፈታት ጥበባችንን በሌላ መንገድ እንደ መግለጽ የሚቆጠር ነው። እንዲህ ይላል፤ *«ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት መቼት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ለእኛ የሚውለው የእግዚአብሔር ቃል ለእነርሱ ያገለገለው ነው።»* አብዛኞቹ ሥነመለኮታዊ ምንባቦችና በመልእክቶች ውስጥ የምናገኛቸው በማኅበረሰብ ላይ ያተኮሩ ግብረገባዊ ትእዛዛት የአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖች ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት ጋር እንዲቀራረቡ የሚያደርገው ይኸው ደንብ ነው። «ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና»፤ «ጸጋው በእምነት አድኖናል» የሚሉት ሁሉ ዛሬም እውነት ናቸው። «ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ» (ቆላስይስ 3፡12) የሚለው ዛሬም ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ሐቲት የሠራንላቸው ሁለት ረዣዥም ምንባቦች የዚህ ዓይነቶች ይመስላሉ። ሐቲት ሠርተን ለእነርሱ የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል ከተገነዘብን በኋላ፥ ወዲያውኑ ራሳችንን ከዚያው ተመሳሳይ ቃል ሥር አኑረናል። አሁንም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና አብያተ ክርስቲያናቱን በጥንቃቄ ለመገንባት ይችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰሙ የሚገባቸው መሪዎች አሉን። ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በወርቅ፥ ብርና የከበሩ ድንጋዮች ሳይሆን፥ በአገዳ፥ በእንጨትና በሣር የምትገነባ ይመስላል። እንዲህ ዓይነቱ ሥራ በእሳት በሚፈተንበት ጊዜ ብቃት የጎደለው ሆኖ ይገኛል። 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡16–17 ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለሚኖረን ኃላፊነት እግዚአብሔር የሰጠን ትእዛዝ ነው ብለን ልንከራከር እንችላለን። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ መኖሩ የሚታወቅባት ስፍራና ለዓለማዊው ማኅበረሰብ የኃጢአት ሕይወት አማራጭ መንገድ ልትሆን ይገባል።

ትልቁ ጥንቃቄ እዚህ ላይ ሐቲታችንን አሟልተን ስለ ሠራን የእኛ ሁኔታ በትክክል ከእነርሱ ጋር የሚነጻጸር መሆኑን ማረጋገጣችን ነው።

የእነርሱን ችግር በጥንቃቄ መልሶ ማዋቀሩ አስፈላጊ የሚሆነው ለዚህ ነው። ለምሳሌ፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፡1-11 ሁለት ክርስቲያኖች ተጣልተው በቆሮንቶስ ገበያ ላይ በሚሰየም የአረማውያን ዳኛ ፊት መቅረባቸው ለአፈታት ጥበባችን አስፈላጊ ነው። ምርመራው የሚካሄደው በችሎት በመሆኑ ዳኛው ክርስቲያን ቢሆንም፥ የምንባቡ አሳብ አይለወጥም ብለን ልንከራከር እንችላለን። ከቁጥር 6-11 እንደተመለከተው፥ ለሁለት ክርስቲያኖች ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ወደ ሕግ ቦታ መሄዱ ትክክል አይደለም። በሌላ በኩል፥ ይህ አንድ ክርስቲያን ኮርፖሬሽኖችን ለሚከስበት ዘመናዊ ሕይወት ተዛማጅነት እንዳለው የሚጠይቁ ወገኖች ይኖራሉ። በዚህ ጊዜ ምንም እንኳ ጳውሎስ የክርስቶስን ከበቀል የፀዳ ግብረገብ ከግንዛቤ እንድናስገባ የሚያቀርብልንን ልመና ማጤኑ አስፈላጊ ቢሆንም (ቁ.7)፥ ውስን ሁኔታችን ከቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጋር አንድ ዓይነት አለመሆኑ ግልጽ ነው።

እስካሁን የተነገረው ሁሉ ቀላል ይመስላል። ነገር ግን እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡1-11 የመሳሰሉት ምንባቦች ከውስን ሁኔታዎች ባሻገር እንዴት ከአማኙ ጋር እንደሚዛመዱ የሚነሣው ጥያቄ ልንወያይባቸው ከሚገቡን አያሌ ጥያቄዎች አንዱ ነው። በዚሁ ምዕራፍ ቀሪ ክፍል ውስጥ እንዲህ ዓይነት አራት ጥያቄዎችን እናነሣለን።

## የተዛምዶ መስፋፋት ችግር

የመጀመሪያው ችግር አሁን የተጠቀሰው ነው። በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ተነጻጻሪ ውስን ሁኔታዎችና ዓውዶች በሚኖሩበት ጊዜ የምንባቡን ተዛምዶ ወደ ሌሎች ዓውዶች ማዛመዱ ተገቢ ነው። ይህም ምንባቡ ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት ጭራሽ በተለየ ዓውድ ውስጥ ተዛማጅነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚካሄድ ተግባር ነው።

ለምሳሌ፥ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡16-17 ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚናገር ቢሆንም፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በውስጡ በማኖር ለራሱ የለየው ነገር ሁሉ የተቀደሰ እንደሆነና ይህንኑ የሚያጠፋ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር አስከፊ ፍርድ ሥር እንደሚወድቅ የሚያስረዳ መርህ ያስተላልፋል። ይህ አሳብ እግዚአብሔር የራሱን ሰውነት የሚበድለውን ሰው እንደሚቀጣ ለማስተማር ከግለሰብ ክርስቲያን ጋር አይዛመድም ይሆን? በተመሳሳይ ሁኔታ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡10-15 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማነጽ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ግለሰቦች በማመልከት ጥሩ አድርገው የማያንጹ ወገኖች ሁሉ ለሥቃይ እንደሚዳረጉ ያስረዳል። ክፍሉ ደኅንነትና ፍርዱ «በእሳት» እንደሚፈጸም አድርጎ ስለሚያቀርብ፥ ይህንን ምንባብ በመጠቀም ስለ አማኙ ዋስትና ማስተማሩ ተገቢ ነው ወይ?

የእነዚህ ተዛማጆች ሁኔታ ደብዘዝ ካለብን፥ ጥንቃቄ ለማድረግ በቂ ምክንያት አለን። እንዲህ ዓይነቱ ተዛምዶ ሐቲቱን ሙሉ ለሙሉ የማግለል ባሕርይ አለውና። ለብዙ ምእተ ዓመታት ብዙዎች 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡16-17ን ከአማኙ ጋር እያዛመዱ ሲያስተምሩ ኖረዋል። እንዲህ ከሆነ፥ ሐቲት ማድረግ ለምን ያስፈልጋል? ለምን በዚህና አሁን ጀምረን የብዙ ክፍለ ዘመናት ስሕተት አንወርስም?

ስለሆነም፥ ተነጻጻሪ ሁኔታዎችና ውስን ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ ለእኛ የሚተላለፈው የእግዚአብሔር ቃል ሁልጊዜም በመጀመሪያ መልእክትነቱ መገደብ እንዳለበት እንሚገታለን። በተጨማሪም፥ የተስፋፋ ተዛምዶ እውነት በመሆኑ ምክንያት ብዙውን ጊዜ ቸገቢ ነው ተብሎ ይታሰባል። ይህም በአንድ ምንባብ ላይ በተስፋፋ ተዛምዶ የተገኘው ፍች በሌሎች ይህንኑ ፍች እንዲሰጡ ተደርገው በተጻፉት ምንባቦች የሚደገፍ መሆኑ ነው። እንዲህ ከሆነ፥ በተስፋፋ ተዛምዶ ብቻ የሚገኝ አሳብ የእግዚአብሔር ቃል ነው ሊባል ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል።

እንደ 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14 ዓይነት ምንባቦች ደግሞ ይበልጥ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ያስከትላሉ፤ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ።» በባሕላዊ መልኩ ይህ ምንባብ ክርስቲያን ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻን እንዳይመሠርት የሚከለክል እንደሆነ ይነገር ነበር። ነገር ግን የ«ቀንበር» (መጠመድ) ምሳሌ ብዙም ስለ ጋብቻ የሚጠቀስ ባለመሆኑ በዓውደ ንባቡ ውስጥ ጋብቻን የሚያመለክት አሳብ መመልከቱ አስቸጋሪ ነው።

በዚህ ስፍራ የመጀመሪያ ምንባቡ ምንን እንደሚከለክል ማወቁ አስቸጋሪ ነው። ምናልባትም በጣዖት አምልኮ ላይ መሳተፍ እንደማይገባ የሚያስረዳ (ከ1ኛ ቆሮ. 10፡14-22 ጋር አነጻጽር) ተጨማሪ ማብራሪያ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም፥ የቀድሞ ፍችውን ስለማናውቅ የዚህን ምንባብ መርህ ሰፋ ማድረግ አንችልም ይሆን? ይቻል ይሆናል። ይህም ቢሆን ከዚህ ምንባብ ውጭ በሌላ ስፍራ የተደገፈ በመሆኑ ነው።

## ሊነጻጸሩ የማይችሉ የውስን ጉዳዮች ችግር

ይህ ችግር በመልእክቶች ውስጥ የሚገኙትን ሁለት ዓይነት ምንባቦች የሚመለከት ነው። እነዚህም ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ስለሌላቸው የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ጉዳዮች የሚናገሩና ምናልባት በሃያኛውም ክፍለ ዘመን ሊፈጸሙ ስለሚችሉ ነገሮች የሚናገሩ ምንባቦች ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ምንባቦች ከእኛ ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው? ቀድሞ ነገር ከእኛ ጋር ግንኙነት አላቸው ወይ?

ለመጀመሪያው ዓይነት ምሳሌ የሚሆነን ጳውሎስ ስለ ሦስት ዓይነት ነገሮች የሚናገርበት የ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8–10 ክፍል ነው። ሦስቱ ጉዳዮች፥ (1) ከጎረቤቶቻቸው ጋር በጣኦት አምልኮ ስፍራዎች ተገኝተው በዓል ለማክበር የሚሿገቱ ክርስቲያኖች (8:10፤ 10:14–22 አንብብ)። (2) የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን የሚጠራጠሩ የቆሮንቶስ ሰዎች (9:1–23)። (3) ለጣኦት ከተሠዋ በኋላ ገበያ ላይ የሚሸጥ ምግብ ነበሩ (10:23–11:1)።

ጥሩ ሐታቴ (የምንባብን ፍች የሚተረትር ሰው) ጳውሎስ ለእነዚህ ችግሮች የሚከተሉትን ምላሾች እንደ ሰጠ ያመለክታሉ። (1) ሌላውን ከማሰናከል መርህ የተነሣ ወደ እነዚህ የጣኦት አምልኮ በዓላት መሄድ አልነበረባቸውም (8:7–13)። ለዚህም ምክንያቱ የዚህ ዓይነቱ አመጋገብ በክርስቶስ ካለ ሕይወት ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ (10:16–17)፥ ከአጋንንታዊ ነገሮች ጋር መተባበርን የሚያሳይ መሆኑ ነው (10:19–22)። (2) ምንም እንኳ ጳውሎስ የተወው ጉዳይ ቢሆንም ሐዋርያዊ ሥልጣኑ የገንዘብ ድጋፍ ሊያስገኝለት እንደሚገባ ይሿገታል። በተጨማሪም ብዙም በማያሳስቡ ጉዳዮች ላይ የወሰዳቸው እርምጃዎች ትክክል መሆናቸውን ያስረዳል (9:19–23)። (3) ለጣዖት የተሠዋ ምግብ ገበያ ላይ ቢቀርብ ገዝቶ መብላት ይቻላል። ከሌላ ሰው ቤትም መብላት ይቻላል። ሰው ቤት መብላቱ ለሌላ ሰው ችግር የሚፈጥር ከሆነ መተው ይቻላል። አንድ ሰው አንድን ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ሊበላ ይችላል። ነገር ግን ሌላውን ሰው የሚያስቀይም ነገር መብላቱ ትክክል አይሆንም።

ችግሩ እነዚህ ችግሮች በምዕራቡ ዓለም ስለማይታወቁ (1) እና (2) ጉዳይ የማይነሣ መሆኑ ነው። በተጨማሪም ከትንሣኤው በኋላ ክርስቶስን ያዩ (9:1ን ከ15:8 ጋር አነጻጽር)፥ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን የመሠረቱና በእነርሱ ላይ ሥልጣን ያላቸው (9:1–2ን ከ2ኛ ቆሮ. 10:16 ጋር አነጻጽር) እንደ ጳውሎስ ዓይነት ሐዋርያት የሉንም።

ሁለተኛውን ዓይነት ችግር በ1ኛ ቆሮንቶስ 5:1–11 ከተጠቀሰው ዘማዊ ወይም በቅዱስ ቁርባን ላይ ጠጥተው ከሚሰክሩ ሰዎች (1ኛ ቆሮ. 11:17–22) መረዳት ይቻላል። ወይም ደግሞ ያልተገረዙ ክርስቲያኖች እንዲገረዙ ከሚገፋፉ ወገኖች ሁኔታ መመልከት ይቻላል (ገላ. 5:2)። እነዚህ ነገሮች ሊፈጸሙ የሚችሉ ቢሆኑም በምዕራቡ ዓለም ዘንድ የማይታሰቡ ናቸው።

ጥያቄው እንግዲህ ለእነዚህ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ለሌሉት ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች፥ እንዴት ለሃያኛው ክፍለ ዘመን

ክርስቲያኖች ይናገራሉ? የሚል ነው። እዚህ ላይ ተገቢ የአፈታት ጥበብ ሁለት ደረጃዎችን መውሰድ እንዳለበት ለመግለጽ እንሻለን።

በመጀመሪያ፥ ሐቲታችንን በጥንቃቄ በማካሄድ ለእነርሱ የተላለፈው የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደነበር መረዳት አለብን። በዚህ ጊዜ በአመዛኙ ችግሩ ከተዛመደበት ውስን ታሪካዊ ሁኔታ ያለፈ ግልጽ መርህ ማግኘት ይቻላል።

ሁለተኛ፥ አስፈላጊው ነጥብ እዚህ ጋ ነው። «መርሁ» ዘመን የማይሽረው (ት ም ል ስስ) ተዛማጅነት የሚኖረው በዘፈቀደ ወይም ለየትኛውም ሁኔታ አይደለም። *በትክክል ተመጣጣኝ ለሆነ ሁኔታ መዛመድ* እንዳለበት እንገልጻለን።

እስኪ እነዚህን ሁለቱንም ነጥቦች እናብራራ። በመጀመሪያ፥ ጳውሎስ በማሰናከያ መርህ ላይ በመመሥረት ለጣዖት በተሠዋ ምግብ ላይ መሳተፍን ይከለክላል። ነገር ግን ይህ ሌላውን አማኝ የሚያስቀይመውን ጉዳይ ብቻ እንደማይመለከት አጢን። የማሰናከያ መርህን የሚያመለክተው አንድ አማኝ በንጹሕ ሕሊና ሊያደርግ እንደሚችል የሚያስበውንና በተግባሩ ወይም በማግባባቱ በጥሩ ሕሊና ሊያደርግ የማይችለውን ሌላ አማኝ ለተመሳሳይ እርምጃ የሚያነሣሣው መሆኑን ነው። በዚህ ጊዜ ሌላው አማኝ *መቀየም* ብቻ ሳይሆን፥ የዚያን አማኝ ተግባር *በመኮረጅ* «ይጠፋል።» ስለሆነም መርሁ ሊነጻጸሩ ለሚችሉ ሁኔታ ብቻ የሚዛመድ ይመስላል።

ሁለተኛ፥ ጳውሎስ በመጨረሻ ከአጋንንታዊ ሥራዎች ጋር መካፈል ስለሚሆን ክርስቲያኖች ለጣዖት የተሠዋ ምግብ እንዳይመገቡ ይከለክላል። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች በአጋንንታዊ ሥራዎች ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በትክክል ካለመገንዘባቸው የተነሣ ግራ ይጋባሉ። ይሁንና፥ ክርስቲያኖች ከየትኛውም የመናፍስት አሠራር፥ ጥንቆላ፥ ኮከብ ቆጠራ፥ ወዘተ. . . ላይ እንዳይሳተፉ መከልከሉ ተገቢ ይመስላል።

በዚህ ዘመን ሐዋርያት ላይኖሩን ይችላሉ። ፕሮቴስታንቶች ደግሞ አገልግሎታቸው ሐዋርያዊ ተዋረድ እንዳለው (ከሐዋርያት የተቀበሉት) እንደሆነ አያስቡም። ነገር ግን በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተደገፈ በመሆኑ (ለምሳሌ፥ 1ኛ ጢሞ. 5፡17-18) «ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ» (1ኛ ቆሮ. 9፡14) የሚለው መርህ ከአሁኑ ዘመን አገልግሎት ጋር የሚጣጣም ይመስላል።

በገበያ የሚሸጠውን ለጣዖት የተሠዋ ምግብ የመመገቡ ጉዳይ (1ኛ ቆሮ. 10፡23-11፡1) ይህንኑ ሥነ አፈታታዊ ጉዳይ በበለጠ አጣብቂኝ ውስጥ ይከተዋል። እንዲህ ዓይነቱ ምግብ ጳውሎስንም ሆነ እግዚአብሔርን የሚያሳስብ አልነበረም። በሮሜ ምዕራፍ 14 የሚገኘው

የምግብ፥ የመጠጥ፥ የበዓላት ቀናት አከባበርና ቆላስይስ 2፥16–23 የተጠቀሱት ተመሳሳይ ጉዳዮችም እንደዚሁ አሳሳቢ ያልሆኑ ነገሮች ናቸው።

ለእኛ ችግሩ አሳሳቢ ያልሆኑትን ነገሮች ከአሳሳቢዎቹ እንዴት ለመለየት እንደምንችል ነው። እነዚህ ነገሮች ከባሕልና ከተለያዩ ክርስቲያናዊ ቡድኖች መካከል (በመጀመሪያው ምእተ ዓመት እንደነበረው) የሚለያዩ መሆናቸው ችግሩን በበለጠ ያወሳስበዋል። በሃያኛዋ ክፍለ ዘመን አሜሪካ ብቻ የእነዚህ ነገሮች ዝርዝር ልብሶችን (የልብሶች ርዝመት፥ ክራባቶች፥ የሴት ሱሪዎች)፥ ኮስሞቲኮችን፥ ጌጣጌጦችን፥ መዝናኛዎችን (ፊልሞች፥ ቴሌቪዥን፥ ካርታዎች፥ ዳንስ፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር መዋኘት) አትሌቲክስን፥ ምግብንና መጠጥን ይጨምራል። ጳውሎስ ለጣዖት የተሠዋን ምግብ ስለ መመገብ የነበረውን ነጻነት እንደተቃወሙት ሰዎች ሁሉ፥ እነዚህን ነገሮች አለመጠቀሙ በእግዚአብሔር ፊት ቅድስናን ያስገኛል የሚሉ ወገኖች ሁልጊዜም እንደ ተራ ጉዳዮች አይመለከቷቸውም።

እንግዲህ አንድን ነገር አሳሳቢ አይደለም የሚያሰኙ ነጥቦች ምን ምንድን ናቸው? የሚከተሉትን እንደ መመሪያ እናቀርባለን።

1. መልእክቶች አሳሳቢ እንዳልሆኑ የሚጠቅሷቸው ነገሮች (ምግብ፥ መጠጥ፥ የቀናት አከባበር፥ ወዘተ. . .) እንደዚያው ሊወሰዱ ይችላሉ።

2. አሳሳቢ ያልሆኑ ነገሮች ሥነ ምግባራዊ ሳይሆን (ሃይማኖታዊ ባሕሎች ቢመስሉም እንኳ) ባሕላዊ ጉዳዮች ናቸው። በእውነተኛ ክርስቲያኖች መካከል እንኳ ከባሕል ባሕል የሚለያዩ ነገሮች ብዙውን ጊዜ አሳሳቢ እንዳልሆኑ ጉዳዮች ይቆጠራሉ። (ለምሳሌ፥ ወይን የሚጠጣባቸውና የማይጠጣባቸው ባሕሎች።)

3. በመልእክቶች ውስጥ ኃጢአቶችን የሚዘረዝሩ ምንባቦች (ለምሳሌ፥ ሮሜ 1፥29–30፤ 1ኛ ቆሮ. 5፥11፤ 6፥9–10፤ 2ኛ ጢሞ. 3፥2–4) ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች የመጀመሪያ ምእተ ዓመት አቻዎች አያካትቱም። ከዚህም በላይ፥ እነዚህ ዝርዝሮች ለክርስቲያኖች ከተሰጡት የተለያዩ ትእዛዛት ውስጥ አልተጨመሩም (ለምሳሌ፥ ሮሜ 12፥ ኤፌ. 5፤ ቆላ. 3፤ ወዘተ. . .)።

ሁሉም ሰው ከእኛ አሳብ ጋር እንደማይስማማ እናውቃለን። ይሁንና፥ በሮሜ 14 መሠረት ከእነዚሁ ሁለት አመለካከቶች የትኛውንም የሚከተሉ ክርስቲያኖች አንዳቸው በሌላው ላይ እንዳይፈርዱ መገንዘቡ ተገቢ ነው። ነጻው ሰው ነጻነቱን ለማወጅ መጣር የለበትም። እነዚህን ነገሮች ለማከናወን ከልቡ ያመነና የቆረጠ ሰው ደግሞ ሌላውን መኮነን የለበትም።

# የባሕል አንጻራዊነት ችግር

አብዛኛዎቹ የአሁኑ ዘመን ችግሮችና ልዩነቶች የሚውሉት እዚህ ላይ ነው። *በታሪካዊ ውስን ሁኔታ* የተሰጠው የእግዚአብሔር *ዘላለማዊ ቃል* ከፍተኛ ውጥረት የሚፈጥረው እዚህ ላይ ነው። ችግሩ የሚከተሉትን ደረጃዎች ያካታል፤ (1) መልእክቶች የመጀመሪያውን ምእተ ዓመት ቋንቋና ባሕል የያዙና በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስን ሁኔታዎች የሚናገሩ ሰነዶች ናቸው። (2) ብዙዎቹ ውስን ሁኔታዎች በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መቼት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው በርቀት መርሆዎችን ለመንደፍ ካልሆነ በስተቀር (ለምሳሌ፥ የጳውሎስን ልብስ ከጢሮአዳ ማምጣት) ከዛሬው ዘመን አማኝ ግላዊ ሕይወት ጋር ያላቸው ተዛማጅነት ጥቂት ወይም ምንም ነው። (3) ሌሎች ምንባቦችም በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መቼት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ነገር ግን ለእነርሱ የተሰጠው ቃል ወደ አዲስ ተነጻጻሪ መቼት ሊተላለፍ ይችል ይሆናል። (4) ስለሆነም፥ ሌሎች ምንባቦች ተነጻጻሪ ውስኖች ቢኖሯቸውም፥ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት መቼት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ወደ አዲስ መቼት መለወጥ አለባቸው ወይስ እዚያው በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ውስጥ መተው አለባቸው? የሚለው አጠያያቂ ነው።

ሁሉም ክርስቲያኖች ማለት ይቻላል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን ወደ አዳዲስ መቼቶች ይለውጣሉ። ለዚህም ነው የሃያኛው ዘመን ክርስቲያኖች፥ «ለሆድህ ሕመም ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ» የሚለውን ምንባብ ተግባራዊ የማያደርጉት። ይህም ብቻ ሳይሆን ሴቶች ራሳቸውን እንዲሸፋፈኑና ፀጉራቸውን እንዲያስረዝሙም አይጠይቁም። የተቀደሰ አሳሳምንም ተግባራዊ አያደርጉም። እነዚሁ ወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች ግን ከዚሁ አንጻር ሴት ወንዶች እያሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልታስተምር እንደምትችል ወይም ግብረ ሰዶማዊነት ተገቢ ልምምድ ሊሆን እንደሚችል ሲነገር ተቆጥተው ይቃወማሉ።

አንዳንድ ሰዎች የባሕልን አንጻራዊነት ከግንዛቤ ላለማስገባት ጥረው ነበር። ይህም የመጀመሪያው ምእተ ዓመት እንዳለ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወደ መቀበሉ አምርቷቸዋል። ይህ ግን ብዙም ፍሬያማ ሆኖ አልተገኘም። የዚህ አስተሳሰብ ተከታይ የሆኑ ሰዎች ሴት ልጆቻቸውን ቤት ውስጥ ሊያስቀምጧቸው፥ ትምህርት ቤት ላይልኳቸውና የሚያገቧቸውን ወንዶች ሊያዘጋጁላቸው ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ግን መጻሕፍትን ከማንበብና መንገድ ላይ ሳይሸፋፈኑ ከመሄድ ሊከላከሏቸው አይችሉም። ለዚህም ችግሩ እንደ መጀመሪያው ክፍለ ዘመን ነዋሪዎች እነዚህን ጉዳዮች በትክክል መፈጸም የማይቻል መሆኑ

ነው። ምክንያቱም መለኮታዊ የሆነ ባሕል አለመኖሩ ነው። ባሕሎች በመሠረቱ የተለያዩ ናቸው። ይህም የመጀመሪያው ምእተ ዓመት ባሕል ከአሁኑ ዘመን ጋር መለያየቱ ብቻ ሳይሆን፥ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አገሮች ባሕሎች ራሳቸው የተለያዩ መሆናቸው ግልጽ ነው።

ስለሆነም፥ የባሕላዊ አንጻራዊነትን ደረጃ መገንዘቡ አግባብነት ያለው የሥነ አፈታት ሂደትና የመልእክቶች በሁኔታዎች ላይ የመደገፍ ውጤት እንደሆነ ለማስገንዘብ እንወዳለን። ነገር ግን ዋጋ ያለው ሥነ አፈታት ማዘጋጀት የሚቻለው ተገቢ መመሪያዎችን በመጠቀም የመሆኑ እውነታ ግንዛቤ ሊያገኝ ያሻል።

ስለሆነም ባሕላዊ አንጻራዊነት የሚታይባቸውና ከመጀመሪያው መቼታቸው አልፈው ሁልጊዜም ለክርስቲያኖች ሁሉ ከሚያገለግሉት ለመለየት የሚከተሉትን መመሪያዎች አቅርበናል። እነዚህ መመሪያዎች «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ የተሰጡ ናቸው» ባንልም፥ የአሁን ዘመን አስተሳሰባችንን እንደሚወክሉ በመግለጽ ተጨማሪ ውይይቶችና የአሳብ ልውውጦች ጠቃሚዎች መሆናቸውን ለማሳሰብ እንወዳለን። (ከእነዚህ ብዙዎቹን ያዘጋጀነው የቀድሞው ባልደረባችን ከሆነው ከዴቪድ ኤም. እስኮለር ጋር ነበር።)

1. መጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስን ማዕከላዊ መልእክት እርሱ ላይ ከተደገፈው መለየት ያሻል። ይህ ግን ባለው ቀኖና ውስጥ ሌላ ቀኖና ለመፍጠር ማለትም አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ለሌሎች መሠረታዊ እንደሆኑ ለመግለጽ የቀረበ አሳብ አይደለም። ይልቁንም ወንጌሉ በባሕል ወይም በሃይማኖታዊ ልማዶች ምክንያት ወደ ሕግነት እንዳይለወጥ ለመጠበቅና ወንጌሉ ባሕላዊ መገለጫዎችን ሁሉ ለማንጸባረቅ እንዳይለወጥ ለመከላከል ነው።

ስለሆነም የሰው ልጆች ሁሉ ውድቀት፥ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኩል ባከናወነው የጸጋ ተግባር ከዚያ ውድቀት መቤዠታቸው፥ ወዘተ. . . የዚያ ማዕከላዊ ክፍል አካል መሆናቸው ግልጽ ነው። ነገር ግን የተቀደሰ አሳሳም፥ የሴቶች ፀጉርን መሸፋፈን፥ ካሪዝማቲካዊ አገልግሎቶችና የጸጋ ስጦታዎች ያንን ያህል መሠረታዊ ጉዳዮች አይመስሉም።

2. በተመሳሳይ ሁኔታ፥ አንድ ሰው አዲስ ኪዳን እንደ ጥብቅ የሥነ ምግባር ክፍል አድርጎ የሚወስደውንና የማይወስደውን ጉዳይ ለይቶ ማየቱ አስፈላጊ ነው። ጥብቅ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ፍጹማዊና ለሁሉም ባሕል የሚያገለግሉ ሲሆኑ፥ እንደዚህ ያልሆኑት ግን ባሕላዊና ከአንዱ ባሕል ወደ ሌላው የሚለዋወጡ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለምሳሌ ያህል፥ ጳውሎስ ስለ ኃጢአቶች ባቀረበው ዝርዝር ውስጥ ባሕላዊ ነገሮች የሉም። አንዳንድ ኃጢአቶች ከሌላው በላይ በአንድ ባሕል ውስጥ ጎልተው ሊታዩ ቢችሉም፥ እነዚህ ነገሮች ክርስቲያናዊ አመለካከቶችና ተግባራት ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ዝሙት፥ አምልኮተ ጣዖት፥ ስካር፥ ግብረ ሰዶማዊነት፥ ስርቆት፥ ስግብግብነት፥ ወዘተ. . . (1ኛ ቆሮ. 6፡9–10) ሁልጊዜም ስሕተት ናቸው። ይህ ማለት ግን ክርስቲያኖች እነዚህን ኃጢአቶች ፈጽመው አያውቁም ማለት አይደለም። ነገር ግን እነዚህ እንደ ተፈላጊ ሥነ ምግባራዊ ምርጫዎች ሊወሰዱ አይችሉም። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲጽፍ አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደዚህ ዓይነት ሕይወት እንደነበራቸው በመግለጽ አሁን ግን ታጥበው እንደነጹ አስረድቷል።

በሌላ በኩል፥ እግርን ማጠብ፥ በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ መለዋወጥ፥ ገበያ ላይ የቀረበ የጣዖት ምግብ መመገብ፥ ሴቶች ሲጸልዩ ወይም ትንቢት ሲናገሩ ራሳቸውን መከናነብ፥ ጳውሎስ ላለማግባት መወሰኑ ወይም የሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር ጥብቅ የሥነ ምግባር ጉዳዮች አይደሉም። ሥነ ምግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ወይም የማይችሉት እነዚህን ነገሮች ማድረጉ ወይም አለማድረጉ አለመታዘዝን ወይም የፍቅርን እጦት የሚገልጽ በሚሆንባቸው ሁኔታዎች ነው።

3. አዲስ ኪዳን አንድ ዓይነት (uniform) እና ተያያዥነት ያለው አሳብና ልዩነቶችን የሚያስተናግድባቸውን ነገሮች ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል። አዲስ ኪዳን በአንድ ዓይነትነት ከገለጻቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉትን ምሳሌዎች መመልከት ይቻላል። እነዚህም ፍቅር የክርስቲያን የሥነ ምግባር ምላሽ መሆኑ፥ በቀል የሌለበት የግል ባሕርይ፥ የአድመኝነት፥ የጥላቻ፥ የግድያ፥ የስርቆት፥ የግብረ ሰዶማዊነት፥ የስካርና የየትኛውም ዓይነት ወሲባዊ እርኩሰት ትክክል አለመሆኑን የሚያሳዩ ናቸው።

በሌላ በኩል፥ የሴቶችን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት (ፌቤን በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን በዲያቆንነት እንዳገለገለች የሚያስረዳውን ሮሜ 16፡1–2፥ ዩልያ ከሐዋርያት ጋር የተጠቀሰችበትን ሮሜ 16፡7፥ ጵርስቅላ ከጳውሎስ ጋር አብራ እንደምትሠራ የሚገልጸውን ሮሜ 16፡3 ተመልከት። በ1ኛ ቆሮንቶስ 3፡9፤ ፊልጵስዩስ 4፡2–3 ተመሳሳይ ቃል ለአቂላ አገልግሏል። እነዚህን በመጀመሪያዎቹ ምንባቦች ውስጥ መኖሩ አጠራጣሪ ከሆነው ከ2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡12 ጋር አነጻጽር)፥ የሮም ፖለቲካዊ ምርመራ (ሮሜ 13፡1–5 እና 1ኛ ጴጥ. 2፡13–14ን ከራእይ 13–18 ጋር አነጻጽር)፥ የአንድ ሰው ሀብቱን ይዞ መቆየት (ሉቃስ 12፡33፤ 18፡22ን ከ1ኛ ጢሞ. 6፡17–19 ጋር አነጻጽር)፥ ወይም

ለጣዖት የተሠዋ ምግብ መመገብ (1ኛ ቆሮ. 10፡23–29ን ከየሐዋ. 15፡29፤ ራእይ 2፡14፥ 20 ጋር አነጻጽር) የመሳሰሉትን ጉዳዮች አስመልክቶ አዲስ ኪዳን አንድ ዓይነት መልእክት አያስተላልፍም። በነገራችን ላይ ከእነዚህ አሳቦች የትኛውም ስሜታዊ ውጥረት ከፈጠረብህ፥ «ለምን?» ብለህ ራስህን ልትጠይቅ ይገባል።

ትክክለኛ ሐቲት አሁን ካለው በላይ የጠነከረ አንጻይነት ሊያሳየን ይችላል። ለምሳሌ፥ ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ አስመልክቶ እንደዚህ ዓይነቱን ምግብ ለመመገብ ወደ ቤተ ጣዖታት ስለመሄድ በሐዋርያት ሥራ ወይም በዮሐንስ ራእይ ያገለገለውን የፅርዕ ቃል ማጥናት ይቻላል። በዚህ ረገድ የአጥኚው አመለካከት ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡14–22 ከገለጸው አሳብ ጋር ይመሳሰላል። ነገር ግን እነዚህ ሌሎች ጉዳዮች ከሥነ ምግባራዊ ይልቅ ባሕላዊ ስለሚመስሉ አንጻይነትነት ባይኖራቸው መረበሽ የለብንም። በተመሳሳይ መልኩ፥ የጋራ ግንዛቤን ወይም የምንባቡን ግልጽ መልእክት በመሠዋት እንኳ ቢሆን አንጻይነትነትን ለማሳየት ሲባል ብቻ ሐቲት ማካሄዱ ተገቢ አይሆንም።

4. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመርሆችና ውስን ተዛምዶዎች መካከል ያለውን ልዩነት መለየቱ አስፈላጊ ነው። አንድ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ አንጻራዊውን ተዛምዶ በፍጹማዊ መርህ ሊያስደግፍና ይህንን በማድረጉም የተዛምዶውን ፍጹማዊነት ሊያቅብ ይችላል። ለምሳሌ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡2–16 ጳውሎስ ስለ መለኮታዊ የፍጥረት ቅደም ተከተል በመግለጽ (ቁ. 3) በማኅበር አምልኮ ጊዜ ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ክብር የሚያጎድል ተግባር እንዳይፈጽም የሚያስረዳ መርህ መሥርቷል (ቁ. 7፥ 10)። ነገር ግን ጳውሎስ በተደጋጋሚ ስለ «ልማድ» ወይም «ተፈጥሮ» ስለሚናገር (ቁ. 6፥ 13–14፥ 16) ውስን ተዛምዶው አንጻራዊ ይመስላል።

ይህም በእንደዚህ ዓይነት ውስን ተዛምዶዎች ወቅት፥ «ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ባናነበው ኖሮ ይህ ለእኛ አሳሳቢ ጉዳይ ይሆን ነበር ወይ?» የሚል ጥያቄ የሚያስነሣ መሆኑን እንድናጤን አድርጎናል። በምዕራቡ ዓለም የሴቶች ፀጉራቸውን አለመሸፈን ምንም ዓይነት ችግር አያስከትልም ነበር። እንዲያውም አንዲት ሴት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብትታዘዝ የምንባቡን «መንፈስ» አላግባብ ታውለዋለች። ነገር ግን አምልኮን የሚያደናቅፍ አንዳንድ የወንድም ሆኑ የሴት ልብሶች መኖራቸውን ለመገንዘብ አፍታም አይወስድም።

5. በጥንቃቄ ማድረግ እስከተቻለ ድረስ በየትኛውም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ፊት ክፍት የነበሩትን ባሕላዊ አማራጮች መወሰኑ ጠቃሚ ነው። አንድ አማራጭ ብቻ ካለበት ባሕላዊ ሁኔታ ጋር አንድ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ የሚስማማበት ደረጃ የእንደዚህ ዓይነቱን ባሕላዊ

አንጻራዊነት አቋም ተግባራዊነት ይጨምራል። ስለሆነም፥ ግብረ ሰዶማዊነት በጥንት ጸሐፍት ሳይቀር የተኮነነ ተግባር ሆኖ ሳለ አዲስ ኪዳን በዚህ ጉዳይ ላይ ለየት ያለ አቋም ይይዛል። በሌላ በኩል፥ በባርነት ሥርዓት ወይም በሴቶች ስፍራና ሚና ላይ የሚቀርቡት አመለካከቶች በመሠረታዊነት የተለዩ ነበሩ። ባርነትን ክፉ ነው ብሎ የተቃወመ ማንም አልነበረም። ሴቶችም ከወንዶች እንደሚያንሱ ተደርገው ሲታዩ ኖረዋል። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ባርነትን እንደ ክፉት አልኮነኑትም። በሌላ በኩል፥ የሴቶችን ሁኔታ በዚያን ዘመን ከነበረው አመለካከት አልቀው ገልጸውታል። ይህም ሆኖ፥ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የነበሩትን ባሕላዊ አመለካከቶች በሚያንጸባርቁበት ደረጃ በአካባቢያቸው ባለው ዓለም የነበረውን ብቸኛ አመለካከት አንጸባርቀዋል።

6. አንዳንድ ጊዜ በግልጽ የማይታዩትን የመጀመሪያውና የሃያኛው ክፍለ ዘመን ባሕላዊ ልዩነቶች ለመለየት መጣር ያሻል። ለምሳሌ፥ በሃያኛዋ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሴቶች ሚና ምን መሆን እንዳለበት ለመወሰን በመጀመሪያው ለሴቶች የተወሰኑ የትምህርት ዕድሎች ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ግን የሴቶች መማር የተለመደ ጉዳይ መሆኑን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ይህ ምናልባትም እንደ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡9–15ን በመሳሰሉት ምንባቦች ላይ የሚኖረንን አመለካከት ሊቀይረው ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ በሚናገርበት መንግሥት (ሮሜ 13፡1–7) ብዙኃን የሚሳተፉበት ዲሞክራሲ አይታወቅም ነበር። ብዙኃን በሚሳተፉበት መንግሥት ኀጂ ሕግጋትና ባለሥልጣናት በሌሎች እንዲተኩ ይደረጋል። ሮሜ 13ን ወደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመለስ ይህንን መገንዘቡ አስፈላጊ ነው።

7. በመጨረሻም በዚህ ጉዳይ ላይ ክርስቲያናዊ ቸርነትን መላበስ ይገባል። ክርስቲያኖች ችግሮችን ሊገነዘቡ፥ እርስ በርሳቸው የሚግባቡባቸውን መንገዶች ሊከፍቱ፥ አንዳንድ መርሆዎችን ለመፍታት ከመሞከር ሊጀምሩ፥ በአመለካከት የሚለዩዋቸውን ወገኖች ሊወዱና ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል።

ይህንን ውይይት ከማጠቃለላችን በፊት፥ እነዚህ መርሆዎች ከሁለት ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። እነዚህም የሴቶች አገልግሎትና ግብረ ሰዶማዊነት ናቸው። በተለይም ለሴቶች አገልግሎት የሚከራከሩ አንዳንድ ሰዎች ለግብረ ሰዶማዊነትም ተመሳሳይ ሙግቶችን ስለሚያቀርቡ እነዚህን ጉዳዮች አጣምሮ መመልከቱ ተገቢ ይመስለናል።

ሴቶች በመምህርነት ወይም በሰባኪነት ሊያገለግሉ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ በመሠረታዊነት በሁለት ምንባቦች ላይ ያተኩራል። 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡34–35 እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡11–12። በሁለቱም ምንባቦች ዝምታና መገዛት ተያይዘው የተገለጹ ሲሆን፥ መገዛት የተሰኘው ለባሏ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2 ላይ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሠለጥን እንደማትችል ተገልጾአል። ለዚህ ምንባብ ሙሉ በሙሉ መታዘዝ ማለት በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሴት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዳታስተምርና እንዳትሰብክ መከልከል ብቻ ሳይሆን ወንዶች ሊያነቡ በሚችሏቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርእስ ጉዳዮችም ላይ መጽሐፍ እንዳትጽፍ ማቀብ ይሆናል። በተጨማሪም፥ ወንዶች በሚገኙባቸው ክፍሎች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ወይም ተዛማጅ ትምህርቶችን (ሃይማኖታዊ ትምህርትን ጨምሮ) በክርስቲያን ኮሌጆች ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ማስተማርንና ሚሲዮናዊ የማስተማር አገልግሎትን የሚያግድ ይሆናል። ነገር ግን በአሁኑ ዘመን ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር የለባቸውም የሚሉ ወገኖች ክፍሉን እምብዛም አይተረጉሙትም። ከዚህም በላይ ሁልጊዜም ማለት ይቻላል ወረድ ብሎ የተጠቀሰውን የአለባበስ ጉዳይ (1ኛ ጢሞ. 2፡9) ባሕላዊ አንጻራዊነት አድርገው ይገልጹታል።

በሌላ በኩል፥ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡11–12 ባሕላዊ አንጻራዊነት ሊሆን የመቻሉ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ በሦስቱም የመጋቢያን መልእክቶች ሐቲት ሊደገፍ ይችላል። በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ሴቶች ችግር ይፈጥሩ ስለነበር፥ (1ኛ ጢሞ. 5፡11–15፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡6–9)፥ የሐሰት አስተማሪዎች መጠቀሚያ ሳይሆኑ አልቀሩም። በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ሴቶች እንደሚያስተምሩ (የሐዋ. 18፡26) እና ትንቢት እንደሚናገሩ (የሐዋ. 21፡8፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡5) ስለተገለጸ፥ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡11–12 ስለ አካባቢያዊ ችግር የሚናገር መሆኑ አያጠራጥርም። ለማንኛውም የ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡11–12 ክልከላ ባሕላዊ አንጻራዊነት መሆኑን ከዚህ በላይ የቀረቡት መርሆች ያስረዳሉ።

የግብረ ሰዶማዊነት ጉዳይ ግን የተለየ ነው። በዚህ ረገድ መርሆዎቹ ባሕላዊ አንጻራዊነት እንደማይነካቸው ያስረዳሉ። ግብረ ሰዶማዊነት ሥነ ምግባራዊ ውድቀት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ ኪዳን የተወገዘው ግብረ ሰዶማዊነት ሰዎች ሌሎችን የሚበድሉበት መሆኑን በመግለጽ ራሳቸውን የቻሉ ትልልቅ ሰዎች በምርጫቸው የሚፈጽሙት ግብረ ሰዶማዊነት ከዚያ የተለየ መሆኑን የሚያስረዱ ሰዎች ተነሥተዋል። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱን ተግባር የሚከለክል መረጃ በሐቲታዊ መንገድ ማግኘት

እንደማይቻል ይሚገታሉ። እንዲሁም ደግሞ እነዚህ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት ያልነበሩ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ባሕላዊ አማራጮች እንደሆኑ የሚከራከሩም አሉ። በመሆኑም (እንደ ቁ. 5፥ 6) የመሳሰሉ አንዳንድ መርሆዎች አዲስ ኪዳን ግብረ ሰዶማዊነትን የከለከለው ከባሕላዊ አንጻራዊነት አኳያ መሆኑን እንደሚያመለክቱ በመግለጽ አንዳንድ መርሆዎችም ትክክል አለመሆናቸውን ያስረዳሉ።

ይሁንና፥ ይህ አሳብ ሐቲታዊ ወይም ታሪካዊ ድጋፍ እንደሌለው ግልጽ ነው። ጳውሎስ በሮሜ 1፡24–28 የሚቃወመው ግብረ ሰዶማዊነት አንዱ ሌላውን የሚበድልበት ዓይነት ("abusive" type) አልነበረም። ይህ ሴቶችና ወንዶች በምርጫቸው የሚያከናውኑት ተግባር ነበር። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ስለ ግብረ ሰዶማዊነት የሚናገረው ቃል ወንድ ከወንድ ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት የሚያመለክት ነው። ስለሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር ግብረ ሰዶማዊነትን ስለሚያወግዝ፥ ግብረ ሰዶማዊነትን በሥነ ምግባራዊ ጉዳይ ውስጥ ስለሚፈርጅና የዛሬዎቹ የግብረ ሰዶማዊነት አማራጮች ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት እንደሚለዩ የሚያስረዱ መረጃዎች ስለሌሉ፥ ባሕላዊ አንጻራዊነት ነው ብሎ ለማለፍ የሚያስችል መሠረት የለንም።

## የተግባር ሥነ መለኮት ችግር

በመልእክቶች ውስጥ አብዛኛው ሥነ መለኮት ከተግባር ላይ ያተኮረ በመሆኑ በሥርዓታዊ መንገድ እንዳልተቀናጀ ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ አስተውለናል። ይህ ማለት ግን በመልእክቶች ውስጥ የተገለጹትን ወይም ከዚያ ውስጥ የተውጣጡትን ሥነ መለኮታዊ አሳቦች በሥርዓታዊ መንገድ ማቅረብ አይቻልም ማለት አይደለም። ይልቁንም፥ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ከሚወጣቸው ኃላፊነቶች አንዱ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነ ሰው ሁልጊዜም በትክክለኛ ሐቲት ላይ ተመሥርቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ሥነ መለኮት ደግሞና ደጋግሞ ሊቀርጽ ይገባል። ብዙውን ጊዜ የአንድ የመልእክቶች ጸሐፊ ሥነ መለኮት ከግልጽ አሳቦቹ ባሻገር በቅድመ ግንዛቤዎቹ (implications) እና በአንድምታዎቹ (presuppositions) ውስጥ የሚገኝ መሆኑ እሙን ነው።

በዚህ ክፍል ለማመልከት የምንፈልገው አንድ ሰው ተግባራዊ ሥነ መለኮትን በሚጠቀምበት ጊዜ በጥንቃቄ ሊያደርገው እንደሚገባ ማሳሰብ ነው። እነዚህም መልእክቶች በሁኔታዎች ላይ የመመሥረት ባሕርይ ያላቸው ከመሆናቸው አንጻር ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ናቸው።

1. ከዚህ በሁኔታዎች ላይ የመመሥረት ባሕርይ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ባለን ሥነ መለኮታዊ ውስንነት ረክተን ማቆም አለብን። ለምሳሌ፥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች የሁለት ክርስቲያን ወንድማማቾች በአረማዊ ፍርድ ቤት መዳኘት ግራ የሚያጋባ ነገር መሆኑን ለማስረዳት አንድ ቀን ክርስቲያኖች በዓለምና በመላእክት ላይ እንደሚፈርዱ ያስረዳል (1ኛ ቆሮ. 6፡2-3)። ከዚያ በላይ ምንባቡ የሚለው ነገር የለውም። በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖች በሚመጣው ዓለም በሌሎች ላይ እንደሚፈርዱ ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን ይህ እንዴት እንደሚሆን የምናውቀው ነገር የለም። ጳውሎስ ያለውን ከመድገም ሌላ የምናቀርበው ተጨማሪ አሳብ ሁሉ ግምታዊ ብቻ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡16-17 ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞች የቅዱስ ቁርባን ተካፋዮች ከመሆናቸው የተነሣ ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ መመገብ እንደሌለባቸው ይከራከራል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ስለ ቅዱስ ቁርባን የሚያቀርበው አሳብ አብዛኞቹ ወንጌል አማኝ ፕሮቴስታንቶች ከሚገነዘቡት ያለፈ ይመስላል። እዚህ ላይ የቀረበው ገለጻ የሚያሳየው መታሰቢያነቱን ብቻ ሳይሆን በትክክል ከጌታ ጋር መካፈልን ይመስላል። ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ተነሥተን የምንካፈለው በመንፈስ ሲሆን፥ በረከቱም በእምነት እንደሚገኝ ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን እንዲህ በምናደርግበት ጊዜ እንኳ የጳውሎስን ሥነ መለኮታዊ አስተሳሰብ ለመገንዘብ ከቀረበው ምንባብ እየወጣን በመሆናችን ብዙዎች ምርጫችንን አይደግፉልንም። ስለሆነም የዚያ ተካፋይነት ሁኔታ ምን እንደሚመስልና በረከቱም እንዴት እንደሚገኝ በግልጽ እንዳልተነገረን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ምንባቦቹ ራሳቸው ከሚሉት ውጭ የሚቀርበው አሳብ በትክክለኛ ሐቲት ላይ ተመሥርቶ የሚነገረን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ሐቲታዊ ጥንካሬ አይኖረውም። ስለሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ለማወቅ የምንፈልገውን ሁሉ ሳይሆን ልናውቅ የሚያስፈልገውን ሰጥቶናል እንላለን።

2. አንዳንድ ጊዜ በመልእክቶች ውስጥ ሥነ መለኮታዊ ችግሮች የሚያጋጥሙን፥ በሁኔታዎች ላይ ከተመሠረተው ባሕርያቸው የእነርሱን ጥያቄዎች ከሚመልሱ ምንባቦች የራሳችንን ጥያቄዎች በመጠየቃችን ነው። ስለ ውርጃ፥ ስለ ዳግም ጋብቻ፥ ወይም ልጆችን ስለማጥመቅ ቀጥተኛ መልስ እንዲሰጡን በምንጠይቃቸው ጊዜ፥ የኋለኛውን ዘመን ጥያቄዎች እንዲመልሱልን እንፈልጋለን። አንዳንድ ጊዜ ይህንን ሊያደርጉ ቢችሉም በዚያን ጊዜ ጥያቄው ስላልተነሣ ብዙዎቹን አይመልሷቸውም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ራሱ ለዚህ ግልጽ ምሳሌ አለ። ጳውሎስ ስለ ፍች ሲናገር፥ «እኔ ግን አላዝም፥ ጌታ እንጂ» ይላል (1ኛ ቆሮ.

7፡10)። ይህ ማለት ክርስቶስ ራሱ ስለዚያ ጉዳይ ተናግሯል ማለት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው አረማዊ ሚስቱን መፍታት አለበት ወይ? ለሚለው የግሪኮች ጥያቄ ክርስቶስ ምላሽ የሰጠ አይመስልም። ችግሩ ክርስቶስ ካገለገለበት የአይሁዶች ባሕል ውጭ ነበር። ጳውሎስ ግን ለዚህ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ስለተገደደ፥ «እኔ እላለሁ፥ ጌታም አይደለም» ሲል ገልጾአል (ቁ. 12)። ከችግሮቹ አንዱ እንግዲህ ማናችንም የጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣንና የመንፈስ ቅዱስ አመራር የሌለን መሆናችን ነው። ስለሆነም ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ምላሽ ልንሰጥ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነመለኮት ላይ ባለን ግንዛቤ ላይ በመመሥረት ይሆናል። ይህም ስለ ፍጥረት፥ የሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅ፥ ስለ ክርስቶስ ቤዛነትና ስለ መጨረሻው ማጠቃለያ ያለንን አስተሳሰብ የሚጨምር ነው። ይህም ችግሩን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ርእዮተ ዓለም አንጻር እንመለከተዋለን ማለት ነው። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ አሳብ የሚሰጡ ምንባቦች በማይኖሩበት ሁኔታ ውስጥ የማረጋገጫ ጥቅስ መጥቀስ አይቻልም።

ስለሆነም፥ መልእክቶችን ለማንበብና ለመተርጎም ያቀረብናቸው የሥነ አፈታት አሳቦች እነዚህ ናቸው። በዚህም አንገብጋቢው ዓላማችን መጽሐፍ ቅዱስን በበለጠ ትክክለኛነት እንድንገነዘበው ነው። ከዚያ የሚበልጠው ዓላማችን ደግሞ ቃሉን ተረድተን ሁላችንም እግዚአብሔር አምላካችንን በይበልጥ እንድንታዘዝ ነው።

# 5

# የብሉይ ኪዳን ትረካዎችና ተገቢ አጠቃቀማቸው

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ «ትረካዎች» ከማናቸውም ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች ይበዛሉ። ለምሳሌ ያህል፥ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ 40 በመቶ የሚሆነው ይህንን ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ብሉይ ኪዳን ራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት አራተኛውን እጅ ስለሚሸፍን ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብዛኛው በትረካ መልክ እንደ ተጻፈ መረዳቱ አስቸጋሪ አይሆንም። የሚከተሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአብዛኛው ወይም ሙሉ በሙሉ በትረካ መልክ የተጻፉ ናቸው። እነዚህም ኦሪት ዘፍጥረት፥ መጽሐፈ ኢያሱ፥ መጽሐፈ መሳፍንት፥ መጽሐፈ ሩት፥ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፥ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፥ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ፥ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፥ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ፥ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ፥ መጽሐፈ ዕዝራ፥ መጽሐፈ ነህምያ፥ ትንቢተ ዳንኤል፥ ትንቢተ ዮናስና ትንቢተ ሐጌ ይገኙባቸዋል። በተጨማሪም፥ ኦሪት ዘጸአት፥ ኦሪት ዘኁልቁ፥ ትንቢተ ኤርምያስ፥ ትንቢተ ሕዝቅኤል፥ ትንቢተ ኢሳይያስና መጽሐፈ ኢዮብ ብዙ የትረካ ምንባቦችን አካትተዋል። በአዲስ ኪዳን አብዛኛው የአራቱ ወንጌላትና ጠቅላላው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በትረካ ስልት የተጻፉ ናቸው።

መንፈስ ቅዱስ እጅግ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በትረካ እንዲጻፍ ሲመራ የሚያደርገውን ያውቅ ነበር ብለን እናምናለን። የዚህ ዓይነቱ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የእግዚአብሔርን የመገለጥ ዓላማ ለማስተላለፍ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ እናስባለን። ጠቃሚነቱ እንዴት እንደሆነና እግዚአብሔርን ስናገለግል እንዴት በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንወያያለን።

## የትረካዎች ባሕርይ

### *ትረካዎች ምንድን ናቸው?*

ትረካዎች ታሪኮች ናቸው። ምንም እንኳ በአንዳንድ ስፍራዎች ታሪኮች ብለን ብንጠራቸውም በአመዛኙ ትረካዎች ማለቱን እንመርጣለን። ለዚህም ምክንያቱ ታሪክ የፈጠራ ታሪክን ወደ ማመልከቱ የሚያዘነብል መሆኑ ነው። በተጨማሪም፥ ወጥ ገጸ ባሕርያትና ወጥ ሤራዎች ያለውን አንድ የተሟላ ታሪክ የሚያመለክት ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ትረካ ግን ብዙውን ጊዜ «የእግዚአብሔር ታሪክ» ሲባል የምንሰማው ነው። ይህም ሙሉ

በሙሉ እውነተኛ፥ እጅግ አስፈላጊና ብዙውን ጊዜ የተወሳሰበ ታሪክ ነው። ይህም የትኞቹም ሰዎች ሊያዘጋጁቸው ከሚችሏቸው ታሪኮች በላይ የሚያስደንቅ፥ በሤራው፥ በገጸ ባሕርያቱና በአገላለጹ ማራኪ ሆኖ የቀረበ ነው። ስለሆነም የዚህ ታላቅ መለኮታዊ ታሪክ አካል ለሆኑት ክፍሎች ትረካ የሚለው ቃል በሙያዊ አጠቃቀሙ ተስማሚ ይመስላል። ለዚህም ምክንያቱ ቃሉ ብዙም ያልተዛባና ይበልጥ ታማኝ ሆኖ መገኘቱ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ስለ ነገሮች ከስተት ይነግሩናል። ነገር ግን ትረካዎቹ በተራ ነገሮች ላይ ያተኮሩ አይደሉም። ዓላማቸው እግዚአብሔር በፍጥረቱና በሕዝቡ መካከል ሲሠራ ማሳየት ነው። ትረካዎች እግዚአብሔርን ያስከብሩታል፤ እኛም እርሱን አውቀን እንድናከብረው ያደርጉናል። ከዚህም በላይ ስለ ቸርነቱና ጥበቃው ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዱናል። በተጨማሪም ለሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑትን ሌሎች ብዙ ነገሮችን ያስተምሩናል።

ትረካዎች ሁሉ ሤራና ገጸ ባሕርያት (ሰው፥ አምላክ፥ እንስሳት፥ እፅዋት፥ ወይም ሌላም ዓይነት) አሏቸው። ይህም ሆኖ የብሉይ ኪዳን ትረካዎች የልዩና አጠቃላዩ ሤራ አካላት የሆኑ ሤራዎች ሲኖሩት፥ ልዩ ገጸ ባሕርያትም አሉት። ከእነዚህም መካከል እጅግ ልዩ ሆኖ የሚገለጸው እግዚአብሔር ራሱ ነው።

## *የትረካዎች ደረጃ*

የብሉይ ኪዳን ትረካዎችን ስታነብና ስታጠና ታሪኩ በሦስት ደረጃዎች እንደሚነገር መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። *ዋንኛው ደረጃ* (ትዞፕ ል ል) አጠቃላዩ የእግዚአብሔር ዓላማ በፍጥረቱ አማካኝነት ተግባራዊ መሆኑ ነው። የዚህ ዋንኛ ደረጃ የሤራ ገጽታዎች የመጀመሪያው ፍጥረት፥ የሰው ልጅ በኃጢአት መውደቅ፥ የኃጢአት ኃይልና በሁሉም ስፍራ መዳረስ፥ የደኅንነት አስፈላጊነት፥ የክርስቶስ ትስእብትናና መሥዋዕት ናቸው። ይህ ዋንኛ ደረጃ ብዙውን ጊዜ «የደኅንነት ታሪክ» ወይም «የቤዛነት ታሪክ» በመባል ይታወቃል።

የመካከለኛ ደረጃ (middle level) ትረካ ገጽታዎች የአብርሃም መጠራት፥ በእምነት አባቶች አማካኝነት የአብርሃም የዘር ሐረግ መመሥረት፥ የእስራኤል በግብጽ ባርነት ሥር መቆየት እንዲሁም፥ ከባርነት መውጣታቸውና ተስፋ የተገባችላቸውን የከነዓን ምድር መውረሳቸው፥ ባለማቋረጥ እስራኤል ኃጢአት መፈጸሙና ለእግዚአብሔር አለመታመኗ፥ ቀጥሎም የእግዚአብሔር በትዕግሥት ከእነርሱ ጋር መኖር፥ በመጨረሻውም ሰሜናዊው እስራኤልና ከዚያም ይሁዳ መውደማቸውና ከምርኮው በኋላ የቅዱስ ሕዝብ መመለስ ናቸው።

ከዚያም ዝቅተኛው ደረጃ (bottom level) ይቀጥላል። እዚህ ውስጥ ሌሎች ሁለት ደረጃዎችን የሚመሠርቱ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የግል ትረካዎች ይገኛሉ። እነዚህም የዮሴፍ ወንድሞች እንዴት ዮሴፍን ወደ ግብጽ ለሚሄዱ የዓረብ ነጋዴዎች አሳልፈው እንደ ሸጡት፥ የጌዴዎን እግዚአብሔርን መጠራጠርና ቆዳ እያነጠፈ መፈተኑ፥ የዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ማመንዘር፥ ወዘተ. . . ናቸው።

ይህንን አጥብቀህ አስተውል። እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን ትረካ (ዝቅተኛው ደረጃ) በዓለም ያለው የእስራኤል ትረካ (መካከለኛ ደረጃ) አካል ሲሆን፥ ይህም በበኩሉ ስለ ዋንኛው የእግዚአብሔር ፍጥረትን መቤዠት የሚያስረዳው ትረካ (ዋንኛው ደረጃ) አካል ነው። ይህ ዋንኛው ትረካ ከብሉይ ኪዳን አልፎ ወደ አዲስ ኪዳን ይሸጋገራል። በሌሎች ሁለት ደረጃዎች ያለውን ክፍል ካላወቅህ ለየትኛውም ትረካ ተገቢውን ትርጉም ልትሰጥ አትችልም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ትረካ በሌሎች አጫጭር ትረካዎች ተዋቅሮ ይገኛል። እንዲህ ዓይነቱ ትረካ «ጥቅል ትረካ» ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ለተግባራዊ ዓላማዎች ሁሉ ስለ ሦስቱ የትረካ ደረጃዎች የምንናገረው ጥቅል ትረካዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር መኖራቸውን በማወቃችን ምክንያት ሊለወጥ አይችልም።

እነዚህን የትረካ ደረጃዎች ማወቅህ በራስህ ሕይወትና ለሌሎች በምታበረክተው አገልግሎት ብሉይ ኪዳንን በትክክል እንድታዛምድ ይረዳሃል ብለን እናምናለን። ክርስቶስ መጻሕፍት «ስለ እኔ ይመሰክራሉ» ሲል (ዮሐንስ 5፡27–29) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሚገኙት ስለ እያንዳንዳቸው ምንባቦች መናገሩ አልነበረም። መሢሐዊ ወይም ሌሎችም የክርስቶስ አምሳያ ምንባቦችን (ከ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡4 ጋር አነጻጽር) የብሉይ ኪዳን ጠቃሚ ክፍሎች ናቸው። ነገር ግን ከጠቅላላው የብሉይ ኪዳን መገለጥ ጥቂቱን ክፍል ብቻ የሚሸፍኑ ናቸው። ይሁንና፥ ክርስቶስ የተናገረው ስለ ትረካው ዋንኛ ደረጃ ሲሆን፥ ይህም ስርየቱ በማዕከላዊነት የተገለጸበት ነው። የሚራውም ጡዘት (climax) የፍጥረት ሁሉ ለእርሱ መገዛት ነው። ስለሆነም መጻሕፍት በወጥነታቸው ለእርሱ በመመስከር፥ በእርሱ የፍቅር አገዛዝ ላይ እንደሚያተኩሩ ማስረዳቱ ነው።

ስለሆነም፥ እያንዳንዳቸው ትረካዎች (አንዳንድ ጊዜ የጥቅልነት ባሕርይ ያላቸው) በዐቢይ ትረካ ሥር፥ ዐቢዮቹ ደግሞ በዋንኛ ትረካ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። አንዳንድ ጥቅል ትረካዎች ከብዙ አጫጭር ትረካዎች የተገነቡ ናቸው። ይህ ከፊል ሜራዎች ያሏቸው ታሪኮች ሁሉ ባሕርይ በመሆኑ የሚያስደንቅ አይሆንም። በአዲስ ኪዳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተነገረው የእግዚአብሔር ጠቅላላ ታሪክ

ዋንኛ ትረካ ውስጥ የግለሰብ ትረካዎች አሉ (ሉቃስ–የሐዋርያት ሥራ)። ለምሳሌ፥ «የዮሴፍ ታሪክ» (ዘፍጥ. 37–50) በመባል የሚታወቀው ሰፊ ጥቅል ትረካ ስለ ዮሴፍ ብዙ አጫጭር ትረካዎችን አካቷል። ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያዎቹ ሕልሞቹ (ዘፍጥ. 37፡5–11)፥ የጲጥፋራ ባሪያ ሆኖ ያሳለፋቸው የውድቀትና የትንሣኤ ጊዜያት (ዘፍጥ. 39)፥ ያዕቆብን በከነዓን ምድር መቅበሩ (ዘፍጥ. 50፡1–14)፥ ወዘተ... ይገኙባቸዋል። ይሁንና፥ ሁሉም የታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ትረካ አካላት ናቸው።

አንድን ትረካ በራሱ ማጥናቱ ጉዳት የለውም። እንዲያውም ይህንን ማድረጉ የሚደገፍ ነው። ነገር ግን አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ ያህል፥ በመጨረሻው ያንን ትረካ በትልቅ ዓውዱ ውስጥ መመልከት ይኖርብሃል።

*ትረካዎች የሚከተሉትን አይደሉም*

1. የብሉይ ኪዳን ትረካዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለኖሩት ሰዎች የሚናገሩ ታሪኮች ብቻ አይደሉም። በቀዳሚነት እግዚአብሔር በእነዚያ ሰዎች ሕይወት ስለፈጸማቸው ተግባራት የሚናገሩ ናቸው። ከሰብአዊ ትረካዎች ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ በተለይ በመለኮታዊ ትረካዎች የተሞላ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዐቢይ ገጸ ባሕርይ እግዚአብሔር ነው። ገጸ ባሕርያት፥ ክስተቶች፥ ዕድገቶች፥ ሤራና የታሪክ ጡዘቶች ቢኖሩም፥ ከዚህ ሁሉ በላይ በትረካዎች ውስጥ ዋንኛው መሪ ተዋናይ እግዚአብሔር ነው።

2. የብሉይ ኪዳን ትረካዎች በስውር ፍችዎች የተሞሉ (allegories) አይደሉም። ነገር ግን በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግሩ የትረካ ገጽታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሚሠራባቸው፥ የሰዎችን ተግባራት የሚለውጥባቸውና በሰዎች በኩል የራሱን ፈቃድ የሚፈጽምባቸው መንገዶች (አንዳንድ ጊዜ ከሰዎቹ ፍላጎት ውጭ፤ ለምሳሌ፥ ዘፍጥረት 50፡20ን ተመልከት) ሁልጊዜም በግልጽ የምንገነዘባቸው አይደሉም። እግዚአብሔር በተወሰነ ሁኔታ ላደረጋቸው ነገሮች መንስዔዎቹ ምን ምን እንደሆኑ ብሉይ ኪዳን ከሚያቀርበው ዘገባ በትክክል ልንረዳ አንችልም። እግዚአብሔር ምን እንዳደረገ የሚናገሩ ምንባቦች እንኳ እንዴት ወይም ለምን እንዳደረገው አይገልጹልንም።

በሌላ አገላለጽ፥ ትረካዎች ስለ አንድ ጉዳይ የምናነሣቸውን ጥያቄዎች በሙሉ አይመልሱም ማለት ነው። በትኩረታቸው የተወሰኑ በመሆናቸው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከሚሠራቸው ድርጊቶች የተወሰነውን ክፍል ብቻ ይነግሩናል። እኛም በዚያ የተወሰነ ግንዛቤ ልንረካና በብዙ ነጥቦች ላይ የማወቅ ጉጉታችንን ልናኖር ይገባል።

እንደዚያ ካልሆነ ከምንባቦቹ በስቲያ ያሉትን አሳቦች በመተርጎም በታሪኩ ውስጥ የሌሉትን ነገሮች ጨምረን ልናነብና ታሪካዊ ዘገባዎችን የስውር ፍች መፈለጊያዎች ልናደርጋቸው እንችላለን። እንደ ምሳሌዎች ሁሉ (ምዕራፍ 8)፥ ትረካዎች በዚህ መንገድ አላግባብ ሊተረጎሙ ይችላሉ።

ታሪኮች ውስጥ ሌሎችን ነገሮች ጨምሮ የማንበብ ሁኔታ የሚከሰተው ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎች ውስጥ ልዕለ ተፈጥሯዊ ነገሮችን ሲለዩ ነው። ይህም ሰዎች ስላልታወቁ በራሪ ነገሮች፥ ከዘመናችን ከብዙ ክፍለ ዘመናት በኋላ ስለሚመጡ የጊዜ ማሽኖች፥ ወይም ከሰው ግንዛቤ በፊት ስለ ጠፉት ጥንታዊ ምሥጢራዊ የሳይንስ ግኝቶች በሚያነሡዋቸው ጥያቄዎች ምክንያት የሚከሰት ነው። እግዚአብሔር የፈጠራቸውን እጅግ በርካታ ተአምራዊ ነገሮች እንዴት እንደፈጠረ የማይናገር መሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ያላነሣውን ጉዳይ ለማወቅ የሚደረግ ጉጉት አንዳንድ ሰዎችን ግራ የሚያጋቡና እውነትነት የሌላቸውን አሳቦች እንዲያምኑ ሊያደርግ ይችላል። ሐሰት በሆኑ ሳይንሳዊ ግኝቶች መደነቅ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተአምራዊ ነገሮች የተሳሳተ ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፈጸማቸውን ነገሮች እንዴት እንዳደረጋቸው አልተናገረም። የዚህን የሥራ ሂደት ለማወቅ የሚደረግ ምኞት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ጋር የማይስማሙ ማብራሪያዎችን ወደ መቀበሉ ያመራል።

3. የብሉይ ኪዳን ትረካዎች ብዙውን ጊዜ ቀጥተኛ ትምህርት አያስተላልፉም። በቀጥታ በክስተቶቹና ገጠመኞቹ ውስጥ ስለተሳተፉት ነገሮች ከማወቅ ይልቅ ክስተቶቹንና ገጠመኞቹን እንድንጋራ በማድረግ ሕጋዊ ወይም ዶክትሪናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሊያደርጉ በማይችሉት መንገድ በልዩ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ባሕርይና መገለጥ አጉልተው ያሳያሉ። በአሁኑ ጊዜ አንድን ነገር ለመገንዘብ በገጠመኙ ውስጥ ማለፍ እንደሚያስፈልግ የሚቀርቡ አሳቦች ትክክል አይደሉም። ነገር ግን የእውነት ባሕርይ አላቸው። አንዳንድ ጊዜ አንድን ነገር በሚገባ የምናውቀውና ባሕርያችንም የሚለወጠው የተሳተፍንበት እንደሆነ ነው። የብሉይ ኪዳንን ትረካዎች በምታነብበት ጊዜ ሌሎች ታሪኮችንም በምታነብበት ጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ተሳታፊዎቹ ምንም ያህል ከአንተ ቢለዩ ወይም ሁኔታቸው ምንም ያህል ከአንተ የተለየ ቢሆንም በአሳብ ከእነርሱ ጋር መዛመድህ አይቀርም። ስለሆነም ትረካዎች እግዚአብሔር በዓለሙ ውስጥ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ከፍተኛ እውቀት ያስጨብጡሃል። ምንም እንኳ ይህ እውቀት ቀዳሚይ ሳይሆን ካልዕይ ቢሆንም፥ ባሕርይህን ሊለውጥ የሚችል እውነተኛ እውቀት ነው።

ክርስቲያን ከሆንህ፥ ብሉይ ኪዳን መንፈሳዊ ታሪክህ ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያቀረባቸው ጥሪዎችና የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች መንፈሳዊ ጥሪዎችህና የተስፋ ቃሎችህ ናቸው (ገላ. 3፡29)። ከሁሉም በበለጠ ጠቃሚና ተግባራዊ መልኩ፥ እግዚአብሔር በእነዚያ የቀድሞ ዘመናት ያመጣቸውን ክስተቶች እንድትከተል ይፈልጋል። ይህንንም ያደረገው ሰዎችን እርሱ በሚፈልገው መንገድ ቃሉን እንዲመዘግቡ በመንፈስ ቅዱስ በመምራቱ ነው።

ምንም እንኳ የብሉይ ኪዳን ትረካዎች ቀጥተኛ መልእክት ባያስተላልፉም፥ በሌላ ስፍራ በቀጥታ የተሰጠውን ትምህርት ያብራራሉ። ይህም ኢ-ርቱዕ የሚባለው ዓይነት የማስተማር ዘዴ ሲሆን፥ ከሌሎች ርቱዕ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ጋር በመሆን መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀም የሚችለውን የመማር ልምድ ሊያስገኝ ይችላል። ለምሳሌ፥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በፈጸመው ዝሙት ውስጥ (2ኛ ሳሙ. 11)፥ «ዳዊት ዝሙት በመፈጸሙ የተሳሳተ ነገር አደረገ» የሚል ዓይነት ዓረፍተ ነገር አናገኝም። ምክንያቱም ይህ ቀደም ሲል በቀጥተኛ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸ በመሆኑ (ዘጸ. 20፡14) ዝሙት ስሕተት መሆኑን፥ እንድታውቅ ይጠበቅብሃል። ትረካው በንጉሥ ዳዊት ግላዊ ሕይወትና በመታዘዝ ችሎታው ላይ የሚያስከትለውን አደጋ ያብራራል። ትረካው ስለ ዝሙት ሥርዓታዊ ትምህርት ስለማያቀርብ፥ ለእንዲህ ዓይነቱ ትምህርት ብቸኛ መሠረት ሊሆን አይችልም። ነገር ግን በአንድ ሁኔታ ውስጥ ዝሙት የሚያስከትለውን ችግር ለማብራራት ከቀጥተኛ ትምህርት በበለጠ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ የሚሠርጽ ጠንካራ መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል።

4. እያንዳንዱ ትረካ ወይም በትረካው ውስጥ የሚገኝ ታሪክ የግድ የራሱ የሆነ ሥነ ምግባራዊ ትምህርት ላይኖረው ይችላል። ትረካዎች እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር፥ ክስተትና ገለጻ ከሌሎች በተለየ መንገድ ለአንባቢው መልእክት እንደሚያስተላልፍ ተደርገው በቀጥታ አይተረጎሙም። እንዲያውም ረዘም ባሉት ትረካዎች ውስጥ ሳይቀር የትረካው ክፍሎች ሁሉ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ አንድ ዐቢይ መልእክት ያስተላልፉ ዘንድ በአንድ ላይ ሊቀርቡ ይችላሉ። በትረካ ውስጥ አሳቡን ብዙውን ጊዜ አንድ ወጥ የሚያደርግ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ይኖራል።

በዚህ መንገድ ትረካዎች ከምሳሌዎች (ምዕራፍ 8ን ተመልከት) ጋር ተመሳሳይ ናቸው። በሁለቱም ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች መልእክቱን የምናገኘው ከተለያዩ ክፍሎች ሳይሆን ከአጠቃላይ አንድነት ነው። መነሻው፥ ውጤቱ፥ ተጽዕኖው፥ ማግባባቱ ሁሉ ከተያያዥ ክስተቶች ቅደም ተከተላዊ ትስስር የሚመጣ ነው። ትረካውን ለመገንባትና

የእግዚአብሔርን መገለጥ ለማስተላለፍ የተለያዩ ነገሮች ተቀናጅተዋል። ስለሆነም በትረካው ውስጥ ለሚገኙት ለእያንዳንዳቸው ዝርዝር መረጃዎችና ክስተቶች ፍች ለመፈለግ መሞከሩ የሚያዋጣ አይሆንም። ትረካውን እንደ አንድ ወጥ እንጂ ጥንቃቄ ባልታከለበት መልኩ በተናጠል መገምገም የለብህም።

## ትረካዎችን ለመተርጎም የሚረዱ መርሆዎች

ከላይ የቀረቡትን አሳቦች ለማብራራት ሁለት ዐበይት የብሉይ ኪዳን ትረካዎችን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለመገምገም መርጠናል። መጀመሪያ ግን እነዚህንም ሆነ ሌሎች ታሪኮችን ሐቲት ለማድረግ በምትፈልግበት ጊዜ የሚያጋጥሙህን ችግሮች ለማስወገድ የሚከተሉት 10 መርሆች ሊረዱህ ይገባል።

1. የብሉይ ኪዳን ትረካ ብዙውን ጊዜ በቀጥታ ዶክትሪናዊ መልእክት አያስተላልፍም።
2. የብሉይ ኪዳን ትረካ ብዙውን ጊዜ በሌላ ስፍራ የቀረበውን ዶክትሪን ወይም ዶክትሪኖች ያብራራል።
3. ትረካዎች የዘገቡት የተፈጸመውን እንጂ ሁልጊዜም ሊፈጸም የሚገባውን ወይም መፈጸም የነበረበትን አይደለም። ስለሆነም አንባቢው ከእያንዳንዱ ትረካ ራሱን የሚያሳትፍበትን ሥነ ምግባራዊ ይዘት ላያገኝ ይችላል።
4. ሰዎች በትረካዎች ውስጥ የሚያደርጉት ነገር የግድ ለእኛ የቀና ምሳሌ ላይሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ እንዲያውም ጥሩ ያልሆነ ምሳሌ መሆኑን እንገነዘባለን።
5. በብሉይ ኪዳን ውስጥ አብዛኞቹ ፍጹም ካለመሆናቸውም በላይ ተግባሮቻቸውም እንዲሁ ነው።
6. ከትረካው መጨረሻ ላይ የተፈጸመው ነገር ጥሩ ወይም መጥፎ መሆኑ ሁልጊዜም አይነገረንም። ያንን እግዚአብሔር በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ካስተማረው አንጻር አገናዝበን እንድናውቅ ይጠበቅብናል።
7. ሁሉም ትረካዎች የሚፈልጓቸውን አሳቦች መርጠው የሚያስተላልፉና ያልተሟሉ ናቸው። ተዛማጅነት ያላቸው ዝርዝሮች ሁልጊዜም አይቀርቡም (ዮሐ. 21፡25 ተመልከት)። በትረካ ውስጥ የሚታየው ደራሲው ለእኛ እናውቀው ዘንድ አስፈላጊ ነው ብሎ ያሰበው ብቻ ነው።
8. ትረካዎች ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎቻችንን ሁሉ ለመመለስ የሚጻፉ አይደሉም። የተወሰኑ ዓላማዎች ስላሏቸው በሌሎች

ስፍራዎችና በሌሎች መንገዶች የሚስተናገዱትን ሁሉ ወደ ዳር በመተው የራሳቸውን አቅጣጫ ይዘው ይሄዳሉ።

9. ትረካዎች በቀጥታም (አንድን ጉዳይ ፊት ለፊት በመግለጽ) ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ (በግልጽ ሳይናገሩ አስከትሎታዊ አንድምታ በመስጠት) ትምህርት ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

10. በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር የሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎች ዋና ገጸ ባሕርይ እንደሆነ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው።

## የትረካ አተረጓጎም ምሳሌዎች

### *የዮሴፍ ታሪክ*

የዮሴፍ ትረካ የምንለው ሰፊ ክፍል ዘፍጥረት ምዕራፍ 37ን እና 39–50ን ያጠቃልላል። እነዚህን ምዕራፎች ስታነብ ዮሴፍ በሁሉም ነጥቦች ላይ ማለት ይቻላል ዋንኛው ሰብአዊ ገጸ ባሕርይ እንደሆነ ትገነዘባለህ። በታሪኩ ውስጥ ዮሴፍ ጎላ ያለ ስፍራ ተሰጥቶታል።

ምናልባትም አባቱ ከሌሎች አብልጦ ስለሚወደው ሊሆን ይችላል (37፡3) ዮሴፍ የወንድሞቹን ክፉት የመናገር ባሕርይ እንደነበረው እናነባለን (ምዕ. 37)። ዮሴፍ የበላይነቱን የሚያሳዩ ሕልሞችን በትዕቢት መናገሩ በቤተሰቡ ውስጥ የተከሰተውን ችግር አላስቆመውም (37፡10–11)። ወንድሞቹ ዮሴፍን ለባርነት ከሸጡት በኋላ ሞቷል ብለው ለአባቱ ነገሩት። ወደ ግብጽ ከተሸጠ በኋላ ዮሴፍ ለጲጥፋራ ከፍተኛ የቤቱ አስተዳዳሪ ሆነ (ምዕ. 39)። ለምን? ይህ የሆነው ተፈጥሯዊ የማስተዳደር ችሎታ ስለነበረው ነበር? አይመስልም። መጽሐፍ ቅዱስ ምክንያቱን በግልጽ አስቀምጦታል፤ «እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ--- ጌታውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ፥ እርሱ የሚሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ እንዲያከናውንለት አየ--- እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ስለ ዮሴፍ ባረከው፤ የእግዚአብሔር በረከት በውጪም በግቢም ባለው ሁሉ ላይ ሆነ» (ዘፍጥ. 39፡2–5)። የዮሴፍ የአስተዳዳሪነት ችሎታ ምንም ያህል የገዘፈ ቢሆንም እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ከነበረው ጣልቃ ገብነት አንጻር በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነበር። በውሸት ወደ ወኅኒ ሲወርድም በዚያው አስተዳዳሪ ሆነ። ለምን? አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ ምክንያቱን በማያሻማ መንገድ ገልጾታል፤ «እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ምሕረትንም አበዛለት፥ በግዞት ቤቱም አለቃ ፊት ሞገስን ሰጠው» (ዘፍጥ. 39፡21ን ከቁ. 23 ጋር አነጻጽር)።

በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚጽፈው ተራኪ የታሪኩ ዋንኛ ባሕርይና ሥነ ምግባራዊ መልእክት በማን ላይ እንደሚያጠነጥን በትክክል

ገልጾአል። ዋናው ገጸ ባሕርይ እግዚአብሔር ነበር። ሥነ ምግባራዊ መልእክቱን የወሰድን እንደሆነ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር እንደነበረ እንገነዘባለን። ከዚህ የዮሴፍ ታሪክ ለመማር እየፈለግህ ዋናውን ገጸ ባሕርይ ከእግዚአብሔር ውጭ ለማድረግ ብትሞክር፥ ማን ሊሆን ይችላል? በልጆቹ መካከል የሚያዳላው ያዕቆብ ነው? ለዮሴፍ ቅንነትን ሊያሳዩ ያልቻሉት ጲጥፋራና ሚስቱ ናቸው? በቀላሉ ችግር ውስጥ የሚዘፈቀው ልበ ሙሉው ዮሴፍ ነው? ከእነዚህ አንዱንም ብትመርጥ የትረካውን ትኩረት እንደምታዛባው ግልጽ ነው። ይህም አጽንኦትህን ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምሪትና ከስተቶችን የመጠቀም ብቃት እንድታርቅ ያደርግሃል።

የታሪኩ ሥነ ምግባራዊ መልእክትስ ምንድን ነው? እንደ ብዙ ሰባኪያንና አስተማሪዎች በእያንዳንዱ ክስተት እንደ ዮሴፍ ለመኖር የሚያስችሉትን አሳቦች በመፈለግ ትሳሳታለህ? እንዲዚያ ከሆነ፥ ይህ ትረካ «ችግር ውስጥ እንዳትገባ ሕልሞችህን ለሌሎች መናገር እንደሌለብህ» ወይም «እስረኞች እንኳ አስተዳደራዊ ችሎታ ካላቸው የተሻለ ሕይወት ሊመሩ እንደሚችሉ» ወይም «ከመታሰርህ በፊት የሆነ የሥራ ልምድ ካለህ በእስር ቤትም እንኳ ጥሩ ልትኖር እንደምትችል» ወይም «የውጭ ዜጎች ከአገሬው በላይ ወደ ሥልጣን እንደሚወጡ» የሚያስተምር መሆኑን ልትናገር ትችላለህ።

በሌላ አገላለጽ፥ ዛሬ ክርስቲያኖች በረከት ለማግኘት ሊያደርጉት ይገባቸዋል በማለት ለምሳሌነት የዮሴፍን ማንነት ወይም ድርጊት ብትመርጥ፥ በትረካው ውስጥ ልታገኝ አትችልም። ትረካው የሚናገረው እግዚአብሔር ለስኬት ሊበቃ በማይችል ሰው ሕይወት ውስጥ ያደረጋቸውን ነገሮች ነው። በሥራ ወይም በአጠቃላይ ሕይወት የተሻለ ደረጃ ላይ ስለመድረስ ትረካው የሚሰጠው ደንብ የለውም። ራሱ ሳይሆን እግዚአብሔር ከእስር የሚወጣበትን ሁኔታ እስካመቻቸበት ጊዜ ድረስ ዮሴፍ ከድጡ ወደ ማጡ ሲሸጋገር ቆይቷል።

እግዚአብሔር በሰጠው ሕልምን የመተርጎም ችሎታ ከእስር ቤት መውጣቱ (ዘፍጥ. 40–41)፥ ከሥልጣን እርከን ላይ መውጣቱና ቤተሰቡን በረሃብ ጊዜ ማዳኑ (ዘፍጥ. 41–50) እና የዮሴፍን ትረካ ለመገንባት የሚያስችሉ ሌሎች ትናንሽ ታሪኮች ስለ ዮሴፍ ተፈጥሯዊ ባሕርይ ወይም ምሳሌያዊ ተግባር የሚያስተላልፉት መልእክት የላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የተለየ ሥነ ምግባራዊ ትምህርት የምትፈልግ ከሆነ በከንቱ መድከምህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው የዮሴፍ ታሪክ ሥነ ምግባራዊ መልእክት እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር መሆኑ ነው። የዮሴፍ ወደ ሥልጣን መውጣትና መውረድ ሁሉ የእግዚአብሔር አሠራር ነበር። የወንድሞቹ ክፉ አሳብ ሳይቀር

ለእግዚአብሔር የረጅም ጊዜ ዓላማ አገልግሏል። ዮሴፍ ራሱ ለወንድሞቹ እንደተናገረው፥ «እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን? እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው» (ዘፍጥ. 50፡19–20)።

ጠቅላላው የክስተቶች ሰንሰለትና የዮሴፍን ትረካ የሚያዋቅሩ ትናንሽ ትረካዎች ሁሉ ከዚያ የሚበልጠው ትረካ አካል ነበሩ። ይህም እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደ አገር የነበረው ዕቅድና በዚሁ የድርቅ ዘመን ከነዓናውያንን፥ ግብፃውያንንና ሌሎችንም ከእነርሱ ጋር ለማዳን የወጠነው ዕቅድ አካል ነበር። ግብፅ እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ሕዝቡን ለዘጸአት በማዘጋጀት የገነባባትና ያበዛበት አገር ነበረች።

የዮሴፍ የሕይወት ዘይቤ፥ ግላዊ ብቃቶች፥ ወይም ተግባራት አጠቃላይ ሥነ ምግባራዊ መርሆች የሚወጡበትን ፍንጭ አይሰጡንም። እንደዚህ ዓይነት ነገር ያገኘህ ከመሰለህ፥ ይህ ከምንባቡ ውስጥ ለማግኘት የፈለግኸው አሳብ ብቻ ነው የሚሆነው። ስለዚህ ምንባቡን በአግባቡ እየተረጎምህ አይደለህም ማለት ነው።

ዮሴፍ ራሱ በመጨረሻ በትረካው ውስጥ የተፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ለበለጠ ዓላማ እንዳደረጋቸው ለመረዳት ችሏል። በኋላ ለወንድሞቹ እንደተናገረው፥ «እኔ እሞታለሁ፤ እግዚአብሔርም መጎብኘትን ይጎበኛችኋል፤ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል፤ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል» ብሏል (ዘፍጥ. 50፡24)።

የትረካው ትኩረት እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የሚፈቅደውን ያደርጋል። እንደ ዮሴፍ፥ ቤተሰቦቹና ፈርዖን የመሳሰሉትን ብቁ ባልሆኑ መሣሪያዎች በመጠቀም፥ እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ያዳነ ሲሆን፥ ለራሱ ልዩ ሕዝብ መፍጠር ጀመረ። የታሪኩን ሥነ ምግባራዊ መልእክት የምናገኘው እዚህ ጋ ነው። ይህም በእግዚአብሔር ቸርነትና ፈቃድ ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም በላይ መንገዶቹን እንድናከብርና በፈቃዱ ልበ ሙሉነት እንዲሰማን የሚያደርግ ነው።

## *የሩት ትረካ /ታሪክ*

የሩት መጽሐፍ አጭርና ራሱን የቻለ ሲሆን፥ ሤራውን ለመከተል ከባድ አይደለም። ገጸ ባሕርያቱንም ለማወቅ ጊዜ አይፈጅብንም። ይህም ለቁጥር 9 የተለየ ትኩረት በመስጠት ከላይ የቀረቡትን መርሆዎች ለማብራራት ተስማሚ አማራጭ ያደርገዋል። በዚህ መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስ በትረካ የሚያስተላልፍልህ ትምህርት ርቱዕም

ኢ-ርቱዕም ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት እንሻለን። ርቱዕ አስተምህሮ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚጽፈው ተራኪ («እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ») የሚልበት ዓይነት ነው። ኢ-ርቱዕ አስተምህሮ በታሪኩ ውስጥ በግልጽ የቀረበ ሆኖ በብዙ ቃላት ያልተገለጸ ነው። ይህ ከገጾች ላይ የሚነበብ ሳይሆን ከታሪኩ አንድምታ የሚታይ ነው።

በርቱዓዊ አቀራረብ የተሰጠውን ትምህርት መለየቱ ከባድ ላይሆን ይችላል። ከበድ ሊል የሚችለው ኢ-ርቱዓዊው አቀራረብ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ለማከናወን ጥበብ፥ ትጋትና መንፈስ ቅዱስ ምንባቡን ባስገኘበት ጊዜ ለወሰደው ጥንቃቄ፥ በጸሎት የታገዘ አክብሮት መስጠትን ይጠይቃል። የሚያስፈልገው ደግሞ ነገሮችን ወደ ትረካው አስገብቶ ማንበብ ሳይሆን እዚያው ውስጥ በተጻፈው ብቻ መርካቱ ነው።

የሩትን ታሪክ እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጎ መመልከት ይቻላል። ሞዓባዊት መበለት የነበረችው ሩት ከእስራኤላዊቷ አማቷ ከኑኃሚን (መበለት) ጋር ወደ ቤተልሔም ትሰደዳለች (ሩት 1)። በቤተልሔም ቦዔዝ የተባለ የኑኃሚን ዘመድ ሩት ለእርሷ ስላደረገቻቸው መልካም ነገሮችና ስለ እምነቷ በመስማት ያስጠጋትና ከመስኩ ላይ ቃርሚያ ትቃርማለች (ሩት 2)። ኑኃሚን ባቀረበችው አሳብ መሠረት፥ ሩት ቦዔዝን እንደምትወድና ያገባኛል ብላ ተስፋ እንደምታደርግ ታሳውቀዋለች (ሩት 3)። ቦዔዝ እርሷን ለማግባትና የቀድሞ ባሏን የመሐሎንን የንብረት መብት ለማስከበር የሚቻልበትን ሕጋዊ መስመር ይከተል ጀመር። የቦዔዝና የሩት ልጅ ኢዮቤድ መወለድ ለኑኃሚን ትልቅ መጽናኛ ሆነ። በመጨረሻም፥ ንጉሥ ዳዊት የኢዮቤድ የልጅ ልጅ ለመሆን በቃ (ሩት 4)።

የሩትን ታሪክ የማታውቅ ከሆነ፥ መጽሐፉን ቢያንስ ሁለት ጊዜ አንብበው። ከዚያም በትረካው ውስጥ የቀረቡትን የሚከተሉትን ኢ-ርቱዓዊ ነጥቦች ተመልሰህ አስተውል።

1. ትረካው ሩት በእስራኤል አምላክ እንዳመነች ይነግረናል። ይህንንም የሚያደርገው «ሩት በእግዚአብሔር አመነች» ብሎ በመናገር ሳይሆን፥ ሩት ለኑኃሚን፥ «ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል» ስትል የተናገረችውን በመገንዘብ ነው (1፡17)። ትረካው እግዚአብሔርን እንደ አምላኳ አድርጋ ስለወሰደች እንደተለወጠች እንድንገነዘብ ይጠብቅብናል። አሁንም ትረካው፥ «--- እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ፤ እንዲሁም ይጨምርብኝ--- » (1፡17) ስትል የተናገረችውን አሳብ በመገንዘብ እምነቷ የውሸት ሳይሆን የልብ መሆኑን በኢ-ርቱዓዊ መንገድ ያስረዳናል። እነዚህ ቃላት ቀጥተኛ መልእክት ባያስተላልፉም በአንድ ወቅት የሞዓባውያንን ጣዖታት ታመልክ የነበረችው ሩት አሁን የእስራኤል አምላክ የሆነውን ያህዌ

አምና በእርሱ መመዘኛዎች እንደምትኖር በግልጽ ያሳያሉ። በየትም ስፍራ በቀጥታ ባይገለጽም ትረካው ሩት በእውነተኛው አምላክ እንዳመነች የሚገልጽ መሆኑ አያጠራጥርም።

2. ብዙ እስራኤላውያን ባያደርጉትም፥ ቦዔዝ የሙሴን ሕግ የሚጠብቅ ጻድቅ ሰው እንደነበር ትረካው በኢ-ርቱዓዊ መንገድ ይነግረናል። 2፡3-13፥ 22፤ 3፡10-12 እና 4፡9-10ን በጥንቃቄ ተመልከት። እነዚህ የትረካው ክፍሎች ቦዔዝ ራሱን በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር እንደሚኖርና ለእግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ አድርጎ እንደሚመለከት ያሳያሉ። በተጨማሪም ቦዔዝ በዘሌዋውያን 19፡9-10 ቃርሚያ የመቃረምን ሕግ እንደሚጠብቅ ያስረዳሉ። (ሩት ደግሞ መጻተኛም በመሆኗ ለቃርሚያው ብቁ ነበረች።) እንዲሁም በዘሌዋውያን 25፡23-24 እንደተመለከተው የመቤዠትን ሕግ እንደሚጠብቅ እንረዳለን። በዚያን ዘመን የቃርሚያን ሕግጋት በማይጠብቁ ሰዎች ማሳ ላይ መቃረም አደገኛ ነበር (2፡22)።

ከዚህም በላይ፥ ትረካው ሌሎችንም ጠቃሚ መረጃዎች በኢ-ርቱዓዊ መንገድ አስፍሮት እናገኛለን። እነዚህ መረጃዎች ትረካውን ለመከተልና ለመተርጎም የሚረዱን ናቸው። ይህም ሆኖ፥ መረጃው በርቱዓዊ መንገድ አልቀረበልንም።

3. ትረካው ይህ ታሪክ ለንጉሥ ዳዊት፥ በዚያውም ለኢየሱስ ክርስቶስ የዳራ አካል እንደሆነ በኢ-ርቱዓዊ መንገድ ያስረዳናል። 4፡17-21ን አንብብ። በቁጥር 17 በአጭሩ፥ ከ18-21 ደግሞ ተሟልቶ የቀረበው የዘር ሐረግ ዝርዝር የተቋጨው በዳዊት ስም ነው። ይህ ክፍል በዚህ የዳዊት ስም ላይ እንደሚያተኩር ግልጽ ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ዳዊት የመጀመሪያው ታላቅ የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች የዘር ሐረግ ዝርዝሮች ውስጥ እንመለከታለን። እንዲሁም ደግሞ በሰብአዊ አነጋገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት የዘር ሐረግ እንደመጣ አዲስ ኪዳን ይነግረናል። ስለሆነም ሩት የዳዊት ቅድመ አያት ስትሆን፥ በኢየሱስ የዘር ሐረግ ውስጥ የምትገኝ ሴት ናት። ይህ የጠቅላላው ትረካ አስፈላጊ ትምህርት ነው። ይህ ሩትና ቦዔዝ ለእግዚአብሔር የነበራቸውን ታማኝነት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፥ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ያላቸውንም ስፍራ የሚያመለክት ታሪክ ነው። እነርሱ ይህንን የሚያውቁበት መንገድ ባይኖርም፥ እግዚአብሔር የዳዊትና «የዳዊት ልጅ» የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ አድርጎ የሚጠቀምባቸው ሰዎች ነበሩ።

4. ትረካው በመሳፍንት ዘመን ከነዋሪዎቿ ታማኝነት የተነሣ ቤተልሔም የተለየች ከተማ እንደነበረች በኢ-ርቱዓዊ መንገድ

ይነግረናል። ይህንን አሳብ ከትረካው ውስጥ መመልከቱ ቀላል አይደለም። በታሪኩ ውስጥ ለሚገኙት ተሳታፊዎች ቃላትና ተግባራት ሁሉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ጠቅላላውን ትረካ በጥንቃቄ ማንበብን ይጠይቃል። እንዲሁም ደግሞ ከቤተልሔም በተቃራኒ በሌሎች የእስራኤል ክፍሎች ነገሮች ምን ዓይነት መልክ እንደነበራቸው ማወቅን ይጠይቃል። ተራኪው የሩትን ታሪክ ከመሳፍንት ዘመን ጋር በቀጥታ ስላዛመደው (1፥1)፥ የቤተልሔምን ከተማ ለማወቅ ደግሞ የመጽሐፈ መሳፍንትን ዐበይት ክስተቶችና ጭብጦች ማወቁ አስፈላጊ ይሆናል። መጽሐፈ መሳፍንትን በጥንቃቄ ያነበብህ ከሆነ የመሳፍንት ዘመን (ከ1240–1030 ዓ.ዓ. አካባቢ) እንደ አምልኮተ ጣዖት፥ ቅይጥ አምልኮ (የአረማውያንና የአምልኮተ እግዚአብሔር ቅልቅል)፥ ማኅበራዊ ፍትሕ አልበኝነቶች፥ ማኅበራዊ ሁከቶች፥ የጎሳ ጠቦች፥ ወሲባዊ እርኩሰቶችና ሌሎችም የታማኝነት ጉድለት ምልክቶች የጎሉበት ጊዜ እንደነበር ትገነዘባለህ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ከሚሰነዘር አጠቃላይ ዓመፅ ባሻገር እስራኤልን ወይም በእስራኤል ውስጥ የሚገኙትን ጎሳዎች የታደገባቸው ጊዜያት ቢኖሩም፥ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የቀረበው ገለፃ የሚያስደስት አልነበረም።

ቤተልሔም ከጠቅላላው የእስራኤል የታማኝነት ጉድለት የተለየች መሆኗን ከሩት ታሪክ ውስጥ የሚነግረን ምንድን ነው? ሁሉም የቤተልሔም ነዋሪዎች የሚገባቸውን ያህል የቃርሚያ ሕግጋት እንደማይከተሉ ከሚያመለክተው ከ2፥22 በስተቀር ሁሉም ምንባብ የቤተ ልሔምን ታማኝነት የሚይሳይ ነው። ከገጸ ባሕርያቱ አፍ የሚወጣው ቃል ሁሉ የዚህች ከተማ ነዋሪዎች እንዴት ለጌታ ታማኝነታቸውን ጠብቀው እንደሚኖሩ ያስረዳል።

ከሩትና ከእኅቷ ዖርፋ በስተቀር በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ገጸ ባሕርያት በሙሉ የቤተልሔም ነዋሪዎች መሆናቸውን አስተውል። ኑኃሚንን ብትመለከት በምሬትም ሆነ (1፥8–9፥ 13፥ 20–21) በደስታ ጊዜ (1፥6፤ 2፥19–20) የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቃ የምትፈጽም ሴት ነች። ቦዔዝም እንደዚሁ በሚናገራቸው ቃላት የእግዚአብሔር ተከታይና አምላኩ መሆኑን ያሳያል (2፥11–12፤ 3፥10፥ 13)። በታሪኩ ውስጥ ያከናወናቸው ተግባራት ደግሞ የተናገራቸውን ቃላት እውነትነት ያረጋግጣሉ።

ሰዎቹ ሰላምታ የሚለዋወጡበት መንገድ እንኳ ከልባቸው ለጌታ እንደሚታመኑ ያሳያል (2፥4)። በተመሳሳይ ሁኔታ የከተማይቱ ሽማግሌዎች በጋብቻና በልጆች ላይ የሚሰጡት ቡራኬ (4፥11–12)፥ ብሎም የከተማይቱ ሴቶች ለኑኃሚን የሚያቀርቡት ባርኮት (4፥14) እምነታቸውን ያመለክታል። በእግዚአብሔር ያመነች ሞዓባዊት ሩትን

መቀበላቸው ደግሞ ለእምነታቸው ተጨማሪ ኢ-ርቱዓዊ ምስክርነት ነው።

በመጨረሻም፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመራው ተራኪ እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገ ያስረዳል (1፡6፤ 4፡13)። ተራኪው የቤተልሔም ዜጋ መሆኑን ባናውቅም፥ የዘመኑን አጠቃላይ የታማኝነት ጉድለት እንደሚቃወም መገመት ይቻላል።

ዋናው ነጥብ አንድ ሰው መጽሐፈ ሩትን (ከመጽሐፈ መሳፍንት ጋር በማነጻጸር) በጥንቃቄ እስካነበበ ድረስ ቤተልሔም ምን ያህል የተለየች እንደሆነች መረዳቱ የማይቀር መሆኑ ነው! በየትም ስፍራ ትረካው፥ «በዚያን ጊዜ ቤተልሔም በቅድስናዋ የተለየች ከተማ ነበረች» ብሎ ፊት ለፊት አይነግረንም። ነገር ግን ተራኪው በተዘዋዋሪ መንገድ የሚነግረን ይህንኑ አሳብ ነው። ይህንንም ያደረገው በቀጥታ የሚገለጹ አሳቦችን ያህል በጠነከረና አሳማኝ በሆነ መንገድ ነው።

እነዚህ ምሳሌዎች ሙሉውን ፍች ለማግኘት ለዝርዝር ጉዳዮች፥ ለትረካው አጠቃላይ እንቅስቃሴዎችና ለዓውደ ንባቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ያሳያሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ኢ-ርቱዓዊው አቀራረብ ርቱዓዊውን ያህል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## ማስጠንቀቂያ

ኢ-ርቱዕ ማለት ምሥጢር ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በትረካው ውስጥ «የሰወራቸውን» ነገሮች አገኛለሁ ብለህ ብትነሣ ራስህን ከትልቅ የአተረጓጎም ችግር ውስጥ ትከታለህ። ኢ-ርቱዕ ማለት እንደዚያ ማለት አይደለም። ኢ-ርቱዕ ማለት አንድ መልእክት በብዙ ቃላት ባይገለጽም ከተጠቀሱት ቃላት ግንዛቤ ሊያገኝ ይችላል ማለት ነው። የአንተ ተግባር ማንም ሊያገኝ የማይችላቸውን ምሥጢራት ፈልፍሎ ማውጣት አይደለም። የአንተ ተግባር ትረካው በርቱዓዊም ሆነ በኢ-ርቱዓዊ (በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ) መንገድ የሚናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ማጤን ነው። በኢ-ርቱዓዊ መንገድ የቀረበውን አሳብ ተረድተህ ለሌሎች በልበ ሙሉነት ለማካፈል ካልቻልህ በተሳሳተ መንገድ አንብበሃል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ያስተላለፈው መልእክት ለሁሉም የሚጠቅም ነው። በታሪኩ ውስጥ የቀረበውን አሳብ መመርመርና እዚያው ላይ መደገፍ እንጂ ሌላ አዲስ ታሪክ መጻፍ አይኖርብህም (2ኛ ጴጥ. 2፡3)!

## አንዳንድ የማጠቃለያ ማስጠንቀቂያዎች

ብዙውን ጊዜ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ውስጥ የሌሉትን ነገሮች የሚያገኙት ለምንድን ነው? እግዚአብሔር እንዲያውቁ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ማንበብ

የራሳቸውን አሳቦች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስገብተው የሚያነቡት ለምንድን ነው? ለዚህ ሦስት ዐበይት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ ሰዎች ከራሳቸው ሕይወት ጋር የሚዛመድ መረጃ ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ነው። ሁለተኛ፥ የሚፈልጉትን መልስ አሁኑኑ ከዚሁ መጽሐፍና ከዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ለማግኘት ስለሚጣደፉ ነው። ሦስተኛ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀረበው አሳብ ሁሉ በቀጥታ ከሕይወታቸው ጋር እንደሚዛመድ የሚጠቁም የተሳሳተ ግንዛቤ ስላላቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ሀብት ነው። ስለሆነም አንድ ክርስቲያን ለሕይወቱ ምሪት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስፈልገውን መልእክት ሁሉ ይዟል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች የሚፈልጓቸውን ውስንና ግላዊ መልሶች ሁልጊዜም ላይዝ ይችላል። ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች ደግሞ በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሁሉም ገጾች ውስጥ የሚገኙ አይደሉም። ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መልስ ለማግኘት ከሚገባው በላይ ሲጣደፉ ስሕተቶችን ይፈጽማሉ። በዚህም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በተሳሳተ መንገድ ይተረጉማሉ።

እንዲህ ዓይነቱን ዝንባሌ ታስወግድ ዘንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ በመፈለግ የሚፈጽሟቸውን ስምንት በጣም የተለመዱ ስሕተቶች እንደሚከተለው አቅርበናል። እነዚህ ስሕተቶች በብዛት በትረካ ምንባቦች ላይ የሚከሰቱ ቢሆኑም፥ በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችም ውስጥ ሊንጸባረቁ ይችላሉ።

1. *ስውር ፍች መፈለግ (allegorizing)*፡ አንዳንድ ሰዎች በግልጽ ፍች ላይ ትኩረት እንደ ማድረግ፥ ከምንባቡ በስቲያ ሌላ ትርጉም ይፈልጋሉ። ምንም እንኳ እንደ ሕዝቅኤል 23 እና አንዳንድ የዮሐንስ ራእይ ዓይነት ስውር ፍች የሚያስተላልፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቢኖሩም፥ ከቀላል የትረካ ምንባብ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ትርጉም ለማግኘቱ መሞከሩ ትክክል አይሆንም።

2. *ዓውደ ንባቡን መጣስ (decontextualizing)*፡ ብዙውን ጊዜ ሰዎች የአንድን ትረካ ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ዓውዶችን ችላ ብለው በአነስተኛ ክፍሎች ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ ለትርጉም የሚያግዙትን ፍንጮች ሳይጨብጡ ይቀራሉ። ከዓውደ ንባቡ ብዙ በራቅህ መጠን የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያሻውን እንዲል የምትፈልገው ዓይነት መልእክት እንዲያስተላልፍልህ ልታደርግ ትችላለህ።

3. *ምርጫ (selectivity)*፡ ይህ ዓውደ ንባብን ከመጣስ ጋር የሚመሳሰል ነው። በመሆኑም የምንባቡን ጠቅላላ አሳብ

በመተው የተወሰኑ ቃላትና ሐረጎች የሚመረጡበት መንገድ ነው። ጠቅላላውንና ከፊሉን ሚዛናዊ እንደ ማድረግ የዚህ ዓይነቱ ስሕተት አንዳንድ ከፊሎችንና ሁሉንም አጠቃላይ መልእክቶች የማግለል ባሕርይ ይታይበታል።

4. *የተሳሳተ ውህደት (false combination)*፡ የዚህ ዓይነቱ ዘዴ በምንባቡ ውስጥ ያልተያያዙትን አሳቦች ከዚያና ከዚህ እየለቃቀሙ በማዋሃድ የተፈለገውን መልእክት እንዲያስተላልፉ የሚደረግበት መንገድ ነው። ለዚህ በብዛት ለሚከሰት የአተረጓጎም ስሕተት ግልጽ ምሳሌ የሚሆነው በመዝሙር 23፥ ዳዊት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለዘላለም እንደሚኖርና በጠላቶቹ ፊት ገበታን እንዳዘጋጀለት የሚናገረውን አሳብ ወስዶ የአንድ ክርስቲያን እውነተኛ ጠላቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚገኙ መደምደም ይሆናል። (ጠላቶቹ ከዳዊት ጋር አብረው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የማይኖሩ ቢሆኑ ኖሮ ከእነርሱ ጋር አይሆንም ነበር ሲሉ ያስረዳሉ።)

5. *ዳግማዊ ብያኔ መስጠት (redefinition)*፡ ግልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ቅጽበታዊ መንፈሳዊ ደስታ ባለመፍጠር ወይም ሊሰሙ የማይፈልጉትን መልእክት በማስተላለፍ ሳይስማማቸው ሲቀር፥ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ሌላ ፍች እንዲሰጥ ለማድረግ ይጥራሉ። ለምሳሌ፥ «እናንተ ባለጠጎች ወዮላችሁ--- » እና «ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ--- » (ሉቃስ 6፡24፥ 26) የሚሉትን የክርስቶስን አባባሎች ይወስዱና በሚከተለው መልኩ እንደገና ይተረጉሙታል። «ብዙ ገንዘብ ስላላችሁ በእግዚአብሔር ላይ ያላችሁን እምነት የተዋችሁ ሰዎች ወዮላችሁ!» «ከዓለማዊ ነገሮች የሰዎችን እርካሽ ውዳሴ ለማግኘት ብላችሁ ወደ ከሀዲነት የተለወጣችሁ ሰዎች ወዮላችሁ!» እነዚህ አባባሎች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደገና ስለተተረጎሙ ይህንኑ ተግባር የፈጸሙትን ሰዎች እስከማይነኩ ድረስ ጠባብ አሳብ እንዲያስተላልፉ ተደርጓል ማለት ነው።

6. *ከቀኖናዊ ሥልጣን ያለፈ አተረጓጎም (extracanonical authority)*፡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በሌላ መንገድ ሊታወቁ የማይችሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች እንደሚገልጡ የሚናገሩትን የዶክትሪን ስብስቦች ወይም መጻሕፍት በቁልፍነት በመጠቀም፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢራት እንደሚከፍቱ ያምናሉ። በተለይም ኑፋቄያዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ እውቀት እንደሚጠይቅ

እንቆቅልሽ አድርገው በመውሰድ ከቀኖናዊ ሥልጣን ባለፈ መንገድ ይተረጉሙታል።

7. *ምንባቦቹን ሥነ ምግባራዊ ማድረግ* (*moralizing*)፡ ይህ የአኗኗር መርሆዎች ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሊወጡ ይችላሉ ከሚል ግምት የሚመጣ ነው። እንዲህ ዓይነት ግምት ያለው አንባቢ ከእያንዳንዱ ትረካ መጨረሻ ላይ፥ «የዚህ ምንባብ ሥነ ምግባራዊ ትምህርት ምንድን ነው?» ሲል ይጠይቃል። ለምሳሌ፥ «እስራኤላውያን በግብጽ ያንን ያህል በባርነት ታግሠው ከመቆየታቸው ታሪክ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል ምን እንማራለን?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ ትረካዎች መርሆዎችን ለማብራራት ሳይሆን የእግዚአብሔርን የአዳኝነት ታሪክ ዕድገት ለማሳየት የተጻፉ መሆናቸውን ስለማይገነዘብ የተሳሳተ ነው። እነዚህ ታሪካዊ እንጂ አስረጅ ትረካዎች አይደሉም።

8. *ግላዊ ማድረግ* (*personalizing*)፥ ይህ ሁሉም ክፍሎች ከሌሎች በተለየ መንገድ ከአንተ ወይም ከቡድንህ ሕይወት ጋር እንደሚዛመዱ በማሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ነው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡበት ጊዜ ሳይቀር በራሳቸው ላይ ወደ ማተኮሩ ያዘነብላሉ። የእግዚአብሔርን የአዳኝነት ታሪክ የሚገልጸው ትልቁ ምስል ሳያረካቸው ሲቀር፥ የግል ፍላጎታቸውንና ምኞታቸውን የሚያሟሉ ወይም ችግሮቻቸውን የሚቀርፉ ነገሮችን በመፈለጉ ፈተና ላይ ይወድቃሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑት፥ «የበለዓም አህያ እንደተናገረች የሚያስረዳው ታሪክ እኔ ብዙ እንደምናገር ያስታውሰኛል» ወይም «ስለ ቤተ መቅደስ መገንባት የሚናገረው ታሪክ አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መገንባት እንዳለብን ያስገነዝበናል» የሚሉ ዓይነት አቀራረቦች ናቸው።

ምናልባትም ትረካዎችን ስለማንበብና ማጥናት ልንሰጥህ የምንችለው ትልቁ ማስጠንቀቂያ ይኼ ይሆናል፤ መጽሐፍ ቅዱስን በግድ የለሽነት አታንብበው። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ የተጻፈው በቀጥታ ለአንተ አይደለም። የዮሴፍ ታሪክ የሚናገረው በቀጥታ ስለ አንተ ሳይሆን ስለ ዮሴፍ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ነገሮችን በእርሱ በኩል እንዴት እንዳከናወነ ያስረዳል። የሩት ታሪክ እግዚአብሔር ለአንተ ሳይሆን ለሩትና ለቤተልሔም ሰዎች ስላደረጋቸው መልካም ነገሮች ይናገራል። ከእነዚህና ከሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ብዙ ልትማር ትችላለህ። ነገር ግን

እግዚአብሔር እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርያት ያደረጓቸውን ነገሮች እንዳሉ እንድትገለብጥ አይጠብቅብህም። በእነርሱ ላይ የተፈጸመው ነገር በአንተ ላይ እንዲፈጸምም ላይፈልግ ይችላል። በምዕራፍ 6 ስለዚህ ጉዳይ ተጨማሪ ማብራሪያዎች ይኖሩናል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርያት አንዳንድ ጊዜ ጥሩዎች፥ ሌላ ጊዜ መጥፎዎች፥ አንዳንድ ጊዜ አስተዋዮች፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሞኞች ሆነው ተገልጸዋል። አንዳንድ ጊዜ ይቀጣሉ፤ ሌላ ጊዜ በምሕረት ይታለፋሉ፤ አንዳንድ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ እናያቸዋለን።

የአንተ ተግባር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደረገውን ሁሉ ለማወቅ መጣር ሳይሆን፥ በዚያን ጊዜ ስለነበሩት ሰዎች ከተጻፈው ትረካ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል መማር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ሰው አንድን ነገር አድርጓል ማለት አንተም ያንኑ የማድረግ ፈቃድ ወይም ግዴታ አለብህ ማለት አይደለም።

ማድረግ ያለብህ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በቃሉ የሚያዝህን ጉዳይ መፈጸም ብቻ ነው። ትረካዎች እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ መሳተፉን ስለሚገልጹልንና መርሆዎቹንና ጥሪውን ስለሚያብራሩልን ግሩም ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች ናቸው። ስለሆነም ብዙ ነገሮችን ሊያስተምሩን ይችላሉ። ነገር ግን በቀጥታ የሚያስተምሩን ነገር ግላዊ ሥነ ምግባርን አይጨምርም። ይህንን በተመለከተ ወደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሄድ ይኖርብናል። ስለዚህ ግላዊ የሥነ ምግባር ትምህርቶች በግልጽ ወደ ቀረቡባቸው ሌሎች የመጽሐፍ ቅድስ ክፍሎች መሄድ አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስን ባለጸጋነትና በየዘርፉ መገኘት እንደ ተወሳሰበ ሸክም ሳይሆን፥ እንደ ጠቃሚ ሀብት ልንገነዘበው ይገባል።

# 6

# የሐዋርያት ሥራ፡ የታሪካዊ አርአያነት ጥያቄ

ከሞላ ጎደል ከፍ ብለን በተመለከትነው ምዕራፍ ውስጥ የቀረቡት አሳቦች ሁሉ እዚህ ውስጥ ስለሚያገለግሉ፥ በአንድ በኩል የሐዋርያት ሥራን ለብቻው መመልከቱ የድግግሞሽ ያህል ነው። ነገር ግን በጣም ተግባራዊ ለሆነ ሥነ አፈታታዊ ምክንያት የሐዋርያት ሥራ ራሱን የቻለ ምዕራፍ ሊሰጠው ያሻል። ምክንያቱ ቀላል ነው። ይኸውም ብዙ ክርስቲያኖች ሙሉ በሙሉ ድርጊታቸውን ላይገነዘቡ ቢችሉም የሐዋርያት ሥራን የሚያነቡት መጽሐፈ መሳፍንትን ወይም መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕን እንደሚያነቡ አይደለም።

የብሉይ ኪዳን ትረካዎችን በምናነብበት ጊዜ ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ተግባራት በመፈጸም ሥነ ምግባራዊ ትምህርት፥ ስውር መልእክት፥ ትርጉምና የመሳሰሉትን ነገሮች እናደርጋለን። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የተሞከረበትን ዓይነት ተግባር ስናነብ ልክ እንደዚያ አናደርግም። እግዚአብሔር ያደርቀው ወይም ያረጥበው ዘንድ ቆዳ አስጥተን ከቤት ውጭ አናሳድርም። ነገር ግን ሌሎች ሁኔታዎችን በመፍጠር እግዚአብሔርን እንደ ቆዳ እናሰጠዋለን። «በዚህ ሳምንት አንድ ሰው ከካሊፎርኒያ ስልክ ቢደውልልን፥ ወደ ካሊፎርኒያ መሄዳችን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እናውቀዋለን» እንላለን። ይህንን «ምሳሌ» በመከተላችን ጌዴዎን እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ባለማመን የፈጸመው ተግባር መልካም እንዳልሆነ እናስባለን።

በዚህም የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ለራሳችን ሕይወት ብዙውን ጊዜ መልካም ምሳሌዎች እንዳልሆኑ እንገነዘባለን። በሌላ በኩል፥ ክርስቲያኖች የሐዋርያት ሥራንም መጽሐፍ የሚያነቡት በዚሁ መንገድ ነው። የሐዋርያት ሥራ የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መናገር ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ዘመን ለምትኖር ቤተ ክርስቲያን ምሳሌያዊ (ሞዴል) ሆኖ የሚያገለግል ነው።

በአብዛኛው የወንጌል አማኝ ፕሮቴስታንቶች የአስተሳሰብ ለውጥ ያካሄዱ ናቸው። በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የነበረውን የቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያናዊ ልምምድ ዘወር ብለን እናይና ልንከተለው እንደሚገባ ምሳሌ ወይም ከዘመናችን ጋር ልናዛምደው እንደሚገባን አሳተሳሰብ አድርገን እንወስደዋለን። ስለሆነም፥ ብዙውን ጊዜ፥ «የሐዋርያት ሥራ በግልጽ እንደሚያስተምረው--- » የሚሉትን

ዓይነት ነገሮች እንናገራለን። ነገር ግን ሁሉም ግልጽ ትምህርት በእኩል ደረጃ ግልጽ እንዳልሆነ ይታወቃል።

እንዲያውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደሚገኙት ክፍፍሎች የመራን የሐዋርያት ሥራ ምን እንደሚያስተምር በትክክል አለማወቃችን ነው። የሕጻናት ወይም የአዋቂዎች ብቻ ጥምቀት፥ ኮንግርጌሽናልና ኤጲስ ቆጶሳዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፥ የጌታን እራት በየሳምንቱ እሑድ እሑድ የመቀበል አስፈላጊነት፥ በምእመናኑ የድምፅ ብልጫ ዲያቆናትን መምረጥ፥ ንብረትን መሸጥና የጋራ ሀብት ማፍራት፥ እባብን መያዝ /!/ ሳይቀር ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ድጋፍ እንዳገኙ የሚነገሩላቸው ጉዳዮች ናቸው።

የዚህ ምዕራፍ ዋንኛ ዓላማ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ አርአያነት ችግሮች አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ አሳቦችን ማቅረብ ነው። ስለሆነም በዚህ ክፍል የምናነሣው አሳብ በወንጌላት ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ክፍሎችን ጨምሮ ለሁሉም ታሪካዊ የትረካ ቅርጾች የሚጠቅም ይሆናል። ከዚያ በፊት ግን የሐዋርያት ሥራን እንዴት እንደምናነብና እንደምናጠና አንዳንድ ነጥቦችን ለመጥቀስ እንፈልጋለን።

በሐዋርያት ሥራ ውይይታችን ወቅት ሉቃስ ይህን መጽሐፍ ሲጽፍ ምን ዓላማ እንደነበረው በመደበኛነት እናነሣለን። ሁልጊዜም መንፈስ ቅዱስ ከሉቃስ ዓላማ በስተጀርባ እንዳለ መገንዘባችን ሊታወቅ ይገባል። እኛ መዳናችንን መፈጸም ቢኖርብንም በእኛ የሚሠራው ግን እግዚአብሔር ነው (ፊልጵ. 2፡12–13)። እንደዚሁም ሉቃስ የሐዋርያት ሥራንና የሉቃስ ወንጌልን በሚጽፍበት ጊዜ የተወሰኑ አሳቦች ነበሩት። ከዚያ ሁሉ በስተጀርባ ግን የመንፈስ ቅዱስ የተቆጣጣሪነት ሚና እንደነበረ እናምናለን።

## የሐዋርያት ሥራ ሐቲት

ምንም እንኳ የሐዋርያት ሥራ ተነባቢ መጽሐፍ ቢሆንም፥ ለቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቀላል አይደለም። ለዚህም ምክንያቱ ሰዎች መጽሐፉን የሚያጠኑት ለተለያዩ ምክንያቶች በመሆኑ ነው። አንዳንዶች የሐዋርያት ሥራ ስለ መጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን በሚያቀርባቸው ታሪካዊ ዝርዝሮች ላይ ያተኩራሉ። ሌሎች ደግሞ የሉቃስ የታሪክ ዘጋቢነት ተግባር በትክክል መከናወኑን በማሳየት መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለማሳየት ይፈልጋሉ። አብዛኞቹ ግን ወደ መጽሐፉ የሚመጡት ሙሉ በሙሉ ለሃይማኖታዊ ወይም ጥሞናዊ ምክንያቶች ነው። የቀድሞዎቹ

ክርስቲያኖች ምን እንደሚመስሉ በመገንዘብ የእነርሱን ምሳሌነት ለመከተል ይፈልጋሉ።

ስለሆነም ሰዎችን ወደ ሐዋርያት ሥራ የሚያመጣቸው ፍላጎት ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ብዙ ምርጫዎች እንዲኖሩ ያደርጋል። ለምሳሌ፥ ጥሞናዊ መልእክት ፈልጎ ወደ መጽሐፉ ለሚመጣ ሰው በምዕራፍ 5 ከሚገኘው የገማልያል ንግግር በላይ በምዕራፍ 9 የጳውሎስን መለወጥ የሚተርከው ክፍል ወይም በምዕራፍ 12 የተጠቀሰው የጴጥሮስ መታሰር ታሪክ የበለጠ ተፈላጊነት ይኖረዋል። እንዲህ ዓይነቱ ንባብ ወይም ጥናት ብዙውን ጊዜ ሰዎች ቅደም ተከተላዊ ወይም ታሪካዊ ጥያቄዎችን በቀላሉ እንዲያልፉ ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ ያህል የመጀመሪያዎቹን አሥራ አንድ ምዕራፎች በምታነብበት ጊዜ በዚህ ክፍል ሉቃስ ያካተተው መረጃ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ዓመታት የፈጀ መሆኑን መረዳቱ አስቸጋሪ ነው።

ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ መጽሐፉን በንቃት እንድታነብና እንድታጠና፥ መጽሐፉን በሉቃስ ዓይኖች እንድትመለከትና አንዳንድ አዳዲስ ጥያቄዎችን እንድትጠይቅ ልንረዳህ እንሞክራለን።

### *የሐዋርያት ሥራ እንደ ታሪክ*

ቀደም ባለው ምዕራፍ የተሰጡት አብዛኞቹ ሐቲታዊ አሳቦቹ ለሐዋርያት ሥራም ያገለግላሉ። እዚህ ላይ አስፈላጊው ነገር ሉቃስ ከአሕዛብ ወገን ሲሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈው ትረካው ደግሞ ግሩም የሆነ ሄለኒስቲክ ወይም ግሪካዊ ሥነ ታሪክ መሆኑ ነው። ይህም ከቱሳይዲድስ ዘመን (ከ460–400 ዓ.ዓ. አካባቢ) ጀምሮ በግሪክ የሄለኒስቲክ ዘመን ሁሉ የተስፋፋ የታሪክ አጻጻፍ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ አንዳንድ ነገሮችን መዝግቦ ለማስቀመጥ ተብሎ የሚጻፍ አልነበረም። ይልቁንም የማበረታቻ ወይም የማጽናኛ መልእክት ለማስተላለፍ፥ የሥነ ምግባር ትምህርት ለመስጠትና ሃይማኖትን ከተቀናቃኝ አሳቦች ለመጠበቅ ተብሎ የሚጻፍ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ሉቃስ የብሉይ ኪዳን ትረካዎችን በማንበብና ባነበባቸው አሳቦች ሕይወቱን በመምራት የኖረ ሰው በመሆኑ፥ የዚህ ዓይነቱ በሃይማኖት አነሣሽነት የሚዘጋጅ ታሪክ ስለ ቀድሞው የክርስትና ታሪክ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ በግልጽ ተንጸባርቋል።

ስለሆነም ሁለቱም የሉቃስ መጻሕፍት (የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ) ከእንደዚህ ዓይነቱ ታሪክ ጋር ይስማማሉ። በአንድ በኩል አንባቢውን እያዝናኑ የሚነበቡ ሲሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከምርጥ የሄለኒስቲክ ሥነ ታሪክና የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ጋር

የሚስማሙ ናቸው። በተመሳሳይ ጊዜ ሉቃስ ከማዝናናት ወይም መልእክት ከማስተላለፍ ያለፉ ዓላማዎች ነበሩት። በዚህ ታሪክ ውስጥ መለኮታዊ ተግባር እየተካሄደ በመሆኑ፥ ሉቃስ አንባቢዎቹ ይህንን እንዲረዱለት ይፈልጋል። ለሉቃስ ከክርስቶስ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የቀጠለው መለኮታዊ ተግባር ከብሉይ ኪዳን የቀጠለ የእግዚአብሔር ታሪክ ነበር። ስለሆነም የሐዋርያት ሥራን ስታነብና ስታጠና የሉቃስን ሥነ መለኮታዊ ፍላጎቶች ማጤኑ እጅግ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የሐዋርያት ሥራ ሐቲት «ምን ተከሰተ?» የሚለውን ንጹሕ ታሪካዊ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን፥ «ሉቃስ ማቴሪያሎችን በዚህ መንገድ መርጦ ሲያዘጋጅ ዓላማው ምን ነበር?» የሚለውን ሥነ መለኮታዊ ጥያቄም የሚጨምር ነው።

የሉቃስን ፍላጎት የሚመለከተው ጥያቄ እጅግ አስፈላጊና አስቸጋሪም ነው። እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለሥነ አፈታታችን በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ነው። የሉቃስ ዓላማ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም የምትከተለውን ሞዴል ለማዘጋጀት መሆኑ ሊታወቅ ቢችል፥ ያ ሞዴል ክርስቲያኖች የሚከተሉት፥ ማለትም እግዚአብሔር በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲከተሉት የሚፈልገው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ዓላማው ሌላ ከሆነ፥ ሥነ አፈታታዊ ጥያቄዎችን በሌላ መንገድ መጠየቅ አለብን ማለት ነው። በሌላ በኩል፥ ቴዎፍሎስ ማን እንደሆነና ሉቃስ ለምን ለዚህ ሰው እንደ ጻፈ ስለማናውቅና የሉቃስ ዓላማዎች ብዙ ስለሚመስሉ የሐዋርያት ሥራን ለምን እንደ ጻፈ ማወቁ አስቸጋሪ ነው።

ነገር ግን የሉቃስ ዓላማ ለአፈታት ጥበብ ካለው ጠቀሜታ ሳቢያ በሐቲታዊ ደረጃ ንባብም ሆነ ጥናት በምታካሂድበት ጊዜ፥ ይህንኑ ጥያቄ በአእምሮህ ልትይዝ ይገባል። ይህ የመልእክቶችን ሐቲት በምትሠራበት ጊዜ አንቀጾችን እንደ ማሰብ ነው። በዚህ ጊዜ ግን ከአንቀጾች አለፍ ብለህ ትረካዎችንና የመጽሐፉን ክፍሎች ሁሉ ታስባለህ።

ሐቲታዊ ፍላጎታችን እንግዲህ በ«ምን» እና «ለምን» ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ቀደም ብለን እንደተገነዘብነው፥ መጀመር ያለብን ከ«ለምን» ሳይሆን ከ«ምን» ሊሆን ይገባል።

### የመጀመሪያው ደረጃ

እንደ ሁልጊዜው የመጀመሪያው ደረጃ ማንበብ ሲሆን፥ ጠቅላላውን መጽሐፍ በአንድ ቁጭታ መጨረሱ የተሻለ አማራጭ ነው። በምታነብበት ጊዜ ምልከታዎችን በማካሄድ ጥያቄዎችን ልታነሣ ይገባል። በእርግጥ የሐዋርያት ሥራ ትረካ በጣም መሳጭ በመሆኑ

ምዕራፎቹን እያነበቡ ምልከታዎችን ለማካሄድና ጥያቄዎችን ለማንሣት ልትቸገር ትችላለህ። ይህም በመሆኑ ሐቲታዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳለብህ ዘንግተህ ማንበብህን ልትቀጥል ትችላለህ።

ስለሆነም እዚህ ላይ የቤት ሥራ ልንሰጥህ ብንፈልግ የሚከተለውን ሊመስል ይችላል። (1) በአንድ ወይም በሁለት ጊዜ የሐዋርያት ሥራን አንብበህ ጨርስ። (2) በምታነብበት ጊዜም ቁልፍ ሰዎችንና ቦታዎችን፥ አንኳሽ ፍላጎቶችን (ሉቃስ የሚያተኩረው በምን ላይ ነው?)፥ የመጽሐፉን ትክክለኛ አከፋፈሎች በአእምሮህ ያዝ። (3) አሁንም ወደ መጽሐፉ ተመልሰህ ቅኝታዊ ንባብ አካሂድና ቀደም ሲል በአእምሮህ የያዝሃቸውን ነገሮች ከጥቅሶቻቸው ጋር ጻፍ። (4) ሉቃስ ለምን ይህንን መጽሐፍ ጻፈ? ብለህ ራስህን ጠይቅ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሐዋርያት ሥራን የሚመስል ሌላ መጽሐፍ ስለሌለ፥ እዚህ ላይ ንባብህንና ጥናትህን ለመምራት በጣም የተወሰነ አቅጣጫ ለመከተል እንረዳሃለን።

*የሐዋርያት ሥራ፥ ቅኝት/አሰሳ*

«ለምን» የሚለውን ጥያቄ ሉቃስ ራሱ በሰጠን አከፋፈል ላይ ተመሥርተን እናንሣለን። ብዙውን ጊዜ የሐዋርያት ሥራ ሉቃስ በጴጥሮስ (ምዕ. 1–12) እና ጳውሎስ (13–28) ላይ ባደረገው ትኩረት ላይ ተመሥርቶ ሲከፈል ኖሯል። ወይም ደግሞ በወንጌሉ መልከዓ ምድራዊ መስፋፋት ላይ በመመሥረት (ከምዕ. 1–7 ኢየሩሳሌም፥ ከ8–10 ሰማርያና ይሁዳ፥ ከ11–28 የምድር ዳርቻ በመባል) ይከፈላል። ምንም እንኳ እነዚህ አከፋፈሎች በትክክለኛ ይዘት አኳያ ግንዛቤ ሊለዩ የሚችሉ ቢሆኑም፥ ሉቃስ ራሱ ፍንጭ የሚሰጥበትና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በተሻለ ሁኔታ የሚያያይዝ ሌላ አማራጭ አለ። መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ በ6፡7፤ 9፡31፤ 12፡24፤ 16፡4 እና 19፡20 የሚገኙትን አጫጭር የማጠቃለያ አሳቦች አስተውል። በእነዚህ ስፍራዎች ትረካው ሌላ አቅጣጫ ይዞ ከመሄዱ በፊት ለአፍታ ያህል ቆም የሚል ይመስላል። በዚህ ፍንጭ ላይ በመመሥረት የሐዋርያት ሥራ በስድስት ክፍሎች እንደተከፈለ መመልከት ይቻላል። እነዚህ ክፍሎች ትረካው በጴጥሮስ ከምትመራውና በኢየሩሳሌም ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስ ወደሚመራትና የአሕዛብ ማዕከል ወደሆነችው ሮም የሚደረገውን የማያቋርጥ የወደፊት እንቅስቃሴ ለማካሄድ ረድተዋል። ይህች በጳውሎስ መሪነት የምትንቀሳቀሰው ቤተ ክርስቲያን በዋናነት አሕዛብ የሚገኙባት ነበረች። ጳውሎስ ለአሕዛብ የወንጌሉን መልእክት ወደሚያስተላልፍባት ሮም ሲገባ (28፡28) ትረካው ከፍጻሜ ይደርሳል።

ስለሆነም፥ መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ እያንዳንዱ ክፍል እንዴት ለዚህ «እንቅስቃሴ» መጎልበት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ማስተዋል ይኖርብሃል። እያንዳንዱ ክፍል ለይዘቱና ለእንቅስቃሴው የወደፊት ግሥጋሤ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በራስህ አባባል ግለጽ። ለእያንዳንዱ አዲስ የወደፊት ግፊት ቁልፍ የሚመስለው አሳብ ምንድን ነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በበኩላችን ያደረግነው ጥረት እንደሚከለተው ቀርቧል።

1፡1–6፡7። በዚህ ስፍራ በኢየሩሳሌም የምትገኝ አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን፥ የቀድሞ ስብከቶቿ፥ ተለምዷዊ አኗኗሯ፥ መስፋፋቷና መጀመሪያ የገጠማት ተቃውሞ ተገልጾአል። እዚህ ዘንድ ስብከቶቹን፥ ተቃውሞውንና የቀድሞ ክርስቲያኖች በቤተ መቅደስና በምኵራብ መሰብሰባቸውን ጨምሮ ሁሉም ነገር እንዴት አይሁዳዊ ጠረን እንደነበረው አጢን። ይህ ክፍል በዕርዕ ቋንቋ ተናጋሪዎችና በአረማይክ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል ክፍፍል መከሰቱን በመግለጽ ትረካውን ይቋጫል።

6፡8–9፡31። ይህ ስለ መጀመሪያው መልክዓ ምድራዊ የወንጌል ስርጭት የሚናገር ሲሆን፥ «ሄለኒስት» (ዕርዕ ተናጋሪ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች) ለተበተኑ አይሁዶች (ለሰማርያውያንና ወደ አይሁድነት ለተለወጡ አሕዛብ) የሰበኩበት ነው። ሉቃስ በዚህ ክፍል (1) ሄለኒስት፥ (2) አይሁዳዊ የክርስቲያኖች ተቃዋሚና (3) በተለይ ለአሕዛብ ወንጌሉን የሚያሰራጨው ጳውሎስ እንደተለወጠም ይተርካል። ለዚህ የመጀመሪያ የወንጌል መስፋፋት በር የከፈተው የእስጢፋኖስ ሰማዕትነት ነበር።

9፡32–12፡24። ይህ መጀመሪያ ለአሕዛብ ስለተላለፈው የወንጌል ስርጭት የቀረበ ገለጻ ነው። ለዚህም ቁልፍ ሚና የተጫወተው ታሪኩ ሁለት ጊዜ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተነገረለት የቆርኔሌዎስ በክርስቶስ ማመን ነው። የቆርኔሌዎስ አስፈላጊነት የሚታየው የተለወጠው በቀጥታ እግዚአብሔር ባመቻቸለት መንገድ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ለዚህ ተግባር የተጠቀመው ደግሞ ግሪኮችን ሳይሆን በአይሁድ–ክርስቲያን አገልግሎት ታዋቂ መሪ የነበረውን ጴጥሮስን ከመሆኑ አንጻር ነው። ቆርኔሌዎስን ወደ ክርስቶስ የመምራቱን ሚና የተጫወቱት ግሪኮች ቢሆኑ ኖሮ በአይሁዶች ዘንድ ጥርጣሬ ማስከተሉ አይቀርም ነበር። በዚህ ክፍል ውስጥ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክም ተካትቷል። በዚህ ጊዜ የአሕዛብ መለወጥ ሆን ተብሎ በግሪኮች (ሄሌኒስቶች) አማካኝነት ይካሄድ ነበር።

12፡25–16፡5። ይህ ክፍል በጳውሎስ መሪነት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሕዛብ ዓለም የተስፋፋውን የወንጌል ስርጭት መልክዓ ምድራዊ አቅጣጫን የሚያሳይ ነው። በዚህ ጊዜ ወንጌሉ አሕዛብን የሚጨምር ሆኖ በመገኘቱ አይሁዶች እየተዉት መጥተው ነበር። ችግሩን ለመፍታት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባኤ ተቀምጠው አሕዛብ ወንድሞቻቸውንና እኅቶቻቸውን ሳያገልሉና የአይሁድ ሃይማኖታዊ መመዘኛዎችንም ጨርሰው ሳይጥሉ፥ እንዴት ሁኔታውን ማስተካከል እንዳለባቸው መከሩ። የኋለኛው አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ለአሕዛብ ወንጌሉን ለማሰራጨት እንደ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ አገልግሏል።

16፡6–19፡20። ወንጌሉ ወደ ምዕራብ እየተስፋፋ በመሄድ የአውሮጳን አገሮች ማዳረሱን ይተርክልናል። በተደጋጋሚ ጊዜ አይሁዶች ወንጌሉን ሲገፉት፥ አሕዛብ ግን መቀበላቸውን ቀጠሉ።

19፡21–28፡30። ጳውሎስንና ወንጌሉን ወደ ሮም የሚወስዱ ክስተቶች ተገልጸዋል። በጳውሎስ የፍርድ ችሎት ምርመራ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን፥ ሦስት ጊዜ ከሚቀርብበት ክስ ነፃ እንደሆነ ተመስክሮለታል።

ይህ በመጽሐፉ ውስጥ የሚካሄደውን እንቅስቃሴ ማጠቃለሉን ለራስህ ለማረጋገጥ፥ የሐዋርያት ሥራን በዚህ አስተዋጽኦና የ«እንቅስቃሴ» ስሜት አንብብ። መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ ገለጻችን በዚህ ሁሉ ውስጥ ዋንኛ ሚና የተጫወተውን አንድ አካል እንዳላካተተ ልትገነዘብ ትችላለህ። እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። በእያንዳንዱ ቁልፍ ነጥብና ቁልፍ ሰው ላይ፥ መንፈስ ቅዱስ ፍጹማዊ የሆነ የመሪነት ሚና እንደሚጫወት መጽሐፉን በምታነብበት ጊዜ ትገነዘባለህ። ሉቃስ እንደገለጸው፥ ይህ ሁሉ የወደፊት እንቅስቃሴ የተካሄደው በሰው ዕቅድ አልነበረም። የተካሄደው የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑና መንፈስ ቅዱስም ተግባራዊ እርምጃ ስለወሰደ ነው።

### *የሉቃስ ዓላማ*

ከዚህ የሉቃስ ቅኝታዊ ንብባ በትረካው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያተኮረበት ዓላማ ምን እንደነበረ በቀላሉ ለመግለጽ ልንጣደፍ አይገባም። ነገር ግን አንዳንድ ምልከታዎችን እንደሚከተለው ለማቅረብ እንፈልጋለን። እነዚህም ነጥቦች በከፊል ሉቃስ በማያደርጋቸው ነገሮች ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

1. የሐዋርያት ሥራን ለመረዳት ቁልፉ ነገር በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሉቃስ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ያተኮረባቸውን ነጥቦች ማጤኑ ይመስላል። ይህም እንቅስቃሴ ወንጌሉ በኢየሩሳሌም ላይ

ከተመሠረተበት የአይሁዳዊነት ጅማሬ ተነሥቶ አሕዛብ ወደ ተበራከቱበት ዓለም አቀፋዊ ክስተት የተደረገ ግሥጋሤ ነው። መዋቅርንና ይዘትን ብቻ ብንመለከት እንኳ የአሕዛብን አገልግሎትና በዚያ አገልግሎት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚጫወተውን ሚና ያላካተተ የትኛውም የዓላማ መግለጫ የመጽሐፉን አሳብ የሳተ ነው።

2. ይህ በ«እንቅስቃሴው» ላይ የተደረገው ትኩረት፥ ሉቃስ በግልጽ ባልነገረን አሳቦች ተጠናክሯል። በመጀመሪያ ደረጃ የሐዋርያትን «ሕይወት» ወይም የሕይወት ታሪክ የመተረክ ፍላጎት የለውም። በመጽሐፉ ውስጥ የተነገረን የያዕቆብ አሟሟት ብቻ ነው (12፡2)። ለአሕዛብ ወንጌሉን ለማዳረስ የሚካሄደው እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ ጴጥሮስ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ ይሰወራል። በምዕራፍ 15 ለአሕዛብ ለሚሰበከው የወንጌል አገልግሎት እውቅና ከመስጠቱ ውጭ ጴጥሮስ በብዙ ስፍራዎች ውስጥ አይታይም። ከዮሐንስ በስተቀር ሌሎች ሐዋርያት ያልተጠቀሱ ሲሆን፥ ሉቃስ ጳውሎስን የሚገልጸው ከአሕዛብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ብቻ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፥ ሉቃስ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ወይም ደንብ ላይ ብዙም ፍላጎት አላሳየም። በምዕራፍ 6 ሰባቱ አገልጋዮች ዲያቆናት ካለመባላቸውም በላይ በሆነ ምክንያት ወዲያው ከኢየሩሳሌም ወጥተዋል። ሉቃስ በኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን የጴጥሮስ መሪነት ከጴጥሮስ የክርስቶስ ወንድም ወደሆነው ወደ ያዕቆብ እንዴት ወይም ለምን እንደተሸጋገረ አይነግረንም (12፡17፤ 15፡13፤ 12፡18)። እንዲሁም «ሽማግሌዎች» እንደ«ተሾሙ» ከመግለጽ ውጭ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደ ተመሠረቱ እንኳ አልነገረንም (14፡23)።

ሦስተኛ፥ ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም በሚወስደው አንድ ቀጥተኛ መስመር ላይ ካልሆነ በቀር ስለ ሌሎች መልክዓ ምድራዊ የወንጌል ማስፋፊያ እንቅስቃሴዎች የነገረን ነገር የለም። ስለ ቀርጤስ (ቲቶ 1፡5)፥ እልዋሪቆን (ሮሜ 15፡19 — የአሁኑ ዘመን ዩጎዝላቪያ)፥ ወይም ስለ ፖንተስ፥ ካፓዶቂያና ቢታኒያ (1ኛ ጴጥ. 1፡1) የተገለጸ ነገር የለም። ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ሜሶጶታሚያና ግብፅ ያደረገችውም መስፋፋት እንዲሁ አልተገለጸም።

ይህ ሁሉ የሉቃስ ዓላማ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ መጻፍ እንዳልሆነ ያስረዳል።

3. ነገሮችን ወደ አንድ ዓይነት መመዘኛ ማምጣቱም የሉቃስ ዓላማ አይመስልም። የሰዎችን መለወጥ በሚጠቅስበት ጊዜ ሁልጊዜም የማያልፋቸው ሁለት ነገሮች አሉ። እነዚህም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና

የውኃ ጥምቀት ናቸው። እነዚህም እንኳ ቢሆኑ ቅደም ተከተላቸውን ለዋውጠው የሚጠቀሱ፥ እጅ ተጭኖ ወይም ሳይጫን የሚካሄዱ፥ በልሳን የሚታጀቡ ወይም የማይታጀቡ፥ እምብዛም ንስሐን (ጴጥሮስ በ2፡38–39 ካቀረበው አሳብ በኋላም እንኳ) ተከትለው የማይመጡ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ሉቃስ ከአሕዛብ ወገን ያመኑ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም የነበረውን ዓይነት ማኅበረሰባዊ ሕይወት መምራታቸውን አልገለጸም፤ ፍንጭም አልሰጠም (2፡42–47 እና 4፡32–35)። እንዲህ ዓይነቱ ልዩነት ምናልባትም ለክርስቲያናዊ አኗኗር ወይም የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሞዴል የሚሆን ውስን ምሳሌ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እየቀረበ አለመሆኑን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል።

ይህ ማለት ግን ሉቃስ በእነዚህ የተለያዩ ትረካዎች ሊያስተላልፍልን የሚፈልገው መልእክት የለውም ማለት ነው? የግድ እንደዚያ ማለት አይቻልም። ዋናው ጥያቄ ለመጀመሪያ አድማጮቹ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው? የሚል ነው።

4. ይህም ሆኖ፥ አብዛኛው የሐዋርያት ሥራ ክፍል እንደ ሞዴል እንዲያገለግል ሉቃስ ያሰበበት መሆኑን እናምናለን። ሞዴሉ የሚገኘው ግን በውስን ጉዳዮች ውስጥ ሳይሆን በአጠቃላይ መልእክቶች ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ሉቃስ ይህንን ታሪክ እንዲያቀርብና እንዲተርክ ያነሣሣው ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ አሕዛብ ዓለም በአሸናፊነትና በደስታ መዝለቋን፥ በዚህም ሂደት የሰዎች ሕይወት መለወጡንና አጥቢያ ማኅበረሰቦች መቋቋማቸውን በመመልከት የቤተ ክርስቲያን ቀጣይ አገልግሎት የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሆነ እንድናጤን ከመፈለጉ የመነጨ ይመስላል። ይህ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የወጠነው ዓላማ በመሆኑ፥ ምንም ነገር ሊቋቋመው አልቻለም። የአይሁድ ሸንጎም ሆነ ምኩራብ፥ ግጭትም ሆነ ጠባብነት፥ እስራትም ሆነ ሤራ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሊቀናቀን አልቻለም። ስለሆነም፥ ሉቃስ ቤተ ክርስቲያን በእርሱ ዘመን የነበረችውን እንድትመስል የፈለገ ቢመስልም፥ በየትኛውም ውስን ምሳሌ ሞዴልነቷን እንድንከተል አይጠብቅም።

## ሐቲታዊ ናሙና

በዚሁ የይዘት ቅኝትና ጊዜያዊ የዓላማ እይታ እስከ ሁለት ትረካዎችን (6፡1–7 እና 8፡1–25) በማንበብ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሊነሡ ስለሚገቡት ሐቲታዊ ጥያቄዎች እናጤናለን።

እንደ ሁልጊዜው ይህንኑ ተግባር ለመጀመር የተመረጠውን ክፍልና ዓውደ ንባቡን ደጋግሞ ማንበብ ያሻል። መልእክቶች ላይ

እንደሚደረገው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ደጋግመህ ልታነሣቸው የሚገባቸው ጥያቄዎች የዚህ ትረካ ወይም ንግግር መልእክት ምንድን ነው? የሚል ይሆናል። በሉቃስ አጠቃላይ ትረካ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጠው እንዴት ነው? ለምን በዚህ ክፍል ውስጥ አካተተው? ብዙውን ጊዜ ከአንድ ወይም ሁለት ጥንቃቄ የታከለበት ምንባብ በኋላ ያንን ጥያቄ በአብዛኛው ለጊዜው ልትመልስ ትችላለህ። አንዳንድ ጊዜ ግን በተለይም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አንዳንድ የይዘት ጥያቄዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመለስ ከመጽሐፉ ውጭ ሌሎች ምንባቦች ልታካሄድ ይገባል።

እስኪ ከ6፡1–7 ባለው ክፍል እንጀምር። ይህ ክፍል በጠቅላላው ይዘት ውስጥ የሚያገለግለው እንዴት ነው? እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ፥ የመጀመሪያውን ክፍል (1፡1–6፡7) ለማጠቃለል ያገለግላል። ሁለተኛ፥ ወደ ሁለተኛው ክፍል (6፡8–9፡31) ለመሸጋገር ያገለግላል። ሉቃስ ይህንን እንዴት እንደሚያደርግ ተመልከት። በ1፡1–6፡7 የሉቃስ ፍላጎት ጀማሪው ክርስቲያናዊ ማኅበረሰብ እንዴት ያለ እንደሆነና በኢየሩሳሌም ውስጥ ምን ዓይነት የወንጌል አገልግሎቶችን ያካሄድ እንደነበር ማሳየት ነው። 6፡1–7 እነዚህን ሁለቱንም ገጽታዎች ያካትታል። እንዲሁም ደግሞ በክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ ስለተነሣው ውጥረትም ፍንጭ ይሰጣል። ይህም በኢየሩሳሌም (አረማይክ ቋንቋ በሚናገሩ) እና ከሌሎች አካባቢዎች በመጡ (ዕርዕ ቋንቋ በሚናገሩ) አይሁዶች መካከል የተከሰተ ውጥረት ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ውጥረት ሊረግብ የቻለው በግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች መካከል የተከሰተው አመራር ይፋዊ እውቅና በማግኘቱ ነበር።

ይህንን ያልነው በዚህ ነጥብ ላይ በታሪካዊ ዓውድ ላይ ሌሎች መጻሕፍትን ማንበብ አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ስለ ዲያቆናትና ሄሌኒስቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችና ጂ. ጀርማያስ የጻፉትን "Jerusalem in the Times of Jesus" ዓይነት የሥነ መሠረት መጻሕፍት ላይ/ መጠነኛ ምንባብ ካካሄድህ የሚከተሉትን ጠቃሚ አሳቦች ታገኛለህ።

1. ሄለኒስቶች ግሪኮች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል የዕርዕ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዶች ነበሩ። እነዚህም ወደ ተለያዩ አገሮች የተበተኑና በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁዶች ነበሩ።

2. ብዙዎቹ ሄለኒስቶች በሽምግልናቸው አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት አስከሬናቸው በጽዮን ተራራ እንዲያርፍ በመፈለጋቸው

ነበር። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ስላልነበሩ እነርሱ በሚሞቱበት ጊዜ መበለቶቻቸው መደበኛ የገቢ ምንጭ አይኖራቸውም ነበር።

3. ለመበለቶቹ የሚደረገ ዕለታዊ ድጎማ በኢየሩሳሌም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስን ፈጠረ።

4. እስጢፋኖስና (የፅርዕ ተናጋሪዎች በሚኖሩባት ሲሊሲያ ውስጥ ከምትገኝ ተርሴስ የመጣው፤ ምዕ. 9) ሳውል አባል የሆኑበት የፅርዕ ተናጋሪዎች ምኩራብ በኢየሩሳሌም ውስጥ እንደነበረ ከ6፡9 መረዳት ይቻላል።

5. ምዕራፍ 6 የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ምኩራብ ከፍተኛ ትኩረት እንደሰጠች ያሳያል። «መበለቶቻቸው» የሚለው አሳብ ከመጠቀሱም በላይ ይህንኑ ጉዳይ ለማቃለል የተመረጡት ሰባቱ ሰዎች የግሪክ ስሞች ያሏቸው ሲሆን፥ ከፍተኛ ተቃውሞ የተነሣው ደግሞ ከሌሎች አገሮች ከመጡት አይሁዶች ነበር።

6. በመጨረሻም፥ ሰባቱ ሰዎች ዲያቆናት ተብለው አልተጠሩም ነበር። «ሰባቱ» (21፡8) ተብለው የተጠሩ ሲሆን፥ ለግሪክ ተናጋሪ መበለቶች የሚሰጠውን ዕለታዊ ድጎማ የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር። ከዚህም በላይ የቃሉም አገልጋዮች ነበሩ። (እስጢፋኖስና ፊልጶስ ለዚህ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ)።

ይህ የይዘት እውቀት በተለይ ቀጣዩን አሳብ ለመገንዘብ የሚያስችል ይሆናል። ምክንያቱም ከ6–8፡1 ድረስ ሉቃስ ከኢየሩሳሌም ውጭ የተካሄደውን የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ከሰባቱ አንዱ እንዳከናወነ ትኩረት ሰጥቶ ዘግቦአል። ይህም ከእስጢፋኖስ መሥዋዕትነት ሳቢያ የተከሰተ መሆኑን በግልጽ ጠቅሶአል (8፡1–4)። ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ይህ የፅርዕ ተናጋሪዎች የሚገኙበት ማኅበረሰብ ለእግዚአብሔር ዓላማ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ልትገነዘብ ትችላለህ። ሰዎቹ ከስደት የተነሣ ከኢየሩሳሌም ለመውጣት ቢገደዱም፥ ቀድሞውንም ነዋሪነታቸው እዚያ አልነበረም። ስለሆነም ከተማይቱን ለቅቀው በመውጣት በይሁዳና ሰማርያ የእግዚአብሔርን ቃል አዳረሱ።

ስለሆነም ከ6፡1–7 የቀረበው ትረካ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ በሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና በምእመናን እንደተደራጀች ለመግለጽ የታሰበ አይደለም። ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም መሠረቷ ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ወጥታ መስፋፋቷን የሚነግረን ነው።

በ8፡5–25 የሚገኘው ትረካ ለየት ያለ ነው። የመጀመሪያው እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በትክክል የተገለጸው በዚህ

ክፍል ነው። ይህ ትረካ አያሌ ሐቲታዊ ችግሮችን የያዘና በቅርቡም የሥነ አፈታታዊ መሟገቻ ሆኖ ስላገለገለ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

እንደ ሁልጊዜው ሐቲታችንን በጥንቃቄ ልንጀምር ይገባል። ለዚህም የምንባብ ክፍሉን ደጋግሞ ማንበብ፥ ምልከታዎችን ማካሄድና ማስታወሻ መውሰዱ አስፈላጊ ነው። እዚህ ዘንድ የትረካውን «ምን» ለማግኘት ክፍሉን በራስህ አገላለጽ ለማስቀመጥ ሞክር። የእኛ የማጠቃለያ ምልከታዎች የሚከተሉት ናቸው።

ታሪኩ ቀጥተኛ ነው። በፊውስና አጋንንትን በማውጣት ስለታጀበው የፊልጶስ የመጀመሪያ አገልግሎትን ያስረዳል (8:5–7)። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰማርያውያን በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ። በፊልጶስ በኩል የሚደረገው የእግዚአብሔር ተአምር ከፍተኛ በመሆኑ አስማተኛው ስምዖን ሳይቀር በክርስቶስ ሊያምን ቻለ (8:9–13)። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ስለዚህ ሁኔታ ስትሰማ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላከች። ሰማርያውያንም በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (8:14–17)። በዚህ ጊዜ ስምዖን በጴጥሮስና በዮሐንስ በኩል የሚካሄደውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ሊሸምት ቋመጠ። በዚህም ጊዜ ጴጥሮስ ገሠጸው። ነገር ግን ከመጨረሻ ንግግሩ (8:24) ስምዖን ንስሐ ይግባ ወይ ጴጥሮስ የተናገረውን ፍርድ ይቀበል ግልጽ አይደለም (8:20–23)።

ሉቃስ ታሪኩን ያቀረበበት ሁኔታ ሁለት ነገሮች እየተፎካከሩ መሆናቸውን ያሳያል። እነዚህም ስለ ሳምራውያን መለወጥና የስምዖን ታሪኮች ናቸው። በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ የሚታዩት ሐቲታዊ ችግሮች ቀደም ሲል ከነበሯቸው እውቀቶችና ግንዛቤዎች የሚመነጩ ናቸው። ነገሮች በዚህ ዓይነት መንገድ መፈጸም እንደሌለባቸው ያስባሉ። በሮሜ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ ማንም ያለ መንፈስ ቅዱስ ክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል እየተናገረ የሰማርያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበሉት እንዴት ነው? የስምዖንስ ጉዳይ? ወደ ኋላ የተመለሰ አማኝ ነው ወይስ ገና የሚያድን እምነት ያላገኘ ሰው ነው?

ምናልባትም ዋንኛው ችግር የመነጨው ሉቃስ ነገሮችን ለእኛ አመቻችቶ ባለማቅረቡ ይሆናል። ቀደም ብለን የያዝናቸው እውቀቶች በአስተሳሰባችን ላይ ተጽዕኖ ሳያደርጉ እንዲህ ዓይነቱን ምንባብ መገንዘቡ አስቸጋሪ ነው። የዚህ መጽሐፍ ደራሲያንም ቢሆኑ ከዚህ ችግር የጸዱ አይደሉም። ይሁንና፥ ከሉቃስ እይታ አንጻር ለመገንዘብ እንሞክራለን። ሉቃስ ይህንን ታሪክ እንዲያቀርብ ያደረገው ምንድን ነው? በአጠቃላይ ዓላማ ውስጥ ይህ ታሪክ ምን አስተዋጽዖ አለው?

ስለ ሳምራውያኑ መለወጥ ሁለት ነገሮች ትኩረቱን የሳቡ ይመስላል። (1) ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌሉ ያመራበት የሰማርያ መልክዓ

ምድራዊ አገልግሎት ሐዋርያት ሳያቅዱ ከሄለኒስቶች አንዱ በሆነው ፊልጶስ እየተካሄደ ነበር። (2) ይሁንና ወንጌሉ መለኮታዊና ሐዋርያዊ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው የሉቃስ አንባቢያን መገንዘብ ነበረባቸው። ይህም ሐዋርያት መጥተው እጃቸውን እስኪጭኑባቸው ድረስ የሰማርያ አማኞች መንፈስ ቅዱስን ባለመቀበላቸው ተመልክቷል። ምንም እንኳ የሄለኒስቶች የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ከሐዋርያት ኮንፍራንስ ውጭ ቢካሄድም ለብቻው የሚዘልቅ አለመሆኑን ማሳየት ከሉቃስ አጠቃላይ ዓላማ ጋር የሚስማማ ነበር።

ምንም እንኳ ክፍሉ በግልጽ ባይናገርና ከሉቃስም ዓላማ ውጭ ቢመስልም፥ ዮሐንስና ጴጥሮስ እስኪመጡ ድረስ የዘገየው የመንፈስ ቅዱስ ግልጽ መረጃ ነበር። ይህን አሳብ ለመሰንዘር ያበቁን ሦስት ምክንያቶች አሉ። (1) ጴጥሮስና ዮሐንስ ከመምጣታቸው በፊት ስለ ሳምራውያን የተነገሩት ነገሮች እውነተኛ ክርስቲያናዊ ልምምድን ለመግለጽ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሌሎች ስፍራዎችም ተደግመዋል። (2) በዚህ ስፍራ እንደሆነው፥ በሌሎች የሐዋርያት ሥራ ክፍሎች የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ዋንኛ ጉዳይ ነበር። ዋናው ነገር ሳይኖር እንዴት ክርስቲያናዊ ሕይወት ሊጀምሩ ይችላሉ? (3) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሉቃስ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ማለት ኃይል (1፡8፤ 6፡8፤ 10፡38) ሲሆን፥ ይህም ብዙውን ጊዜ በሆነ ግልጽ ሁኔታ ይከሰት ነበር። ስለሆነም፥ ይኸው የሚታይና ኃይለኛ የመንፈስ ቅዱስን መገለጽ ሳይሆን አይቀርም በሰማርያ ሳይከሰት የቆየውና በኋላም ሉቃስ ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ወይም መንፈስ ቅዱስን ከመቀበል ጋር አስተካክሎ የገለጸው።

የስምዖንም ሚና በዚህ ትረካ ውስጥ በእኩል ደረጃ የተወሳሰበ ነው። ይሁንና፥ ይኸው ስምዖን የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ቀንደኛ ጠላት ሊሆን እንደ በቃ የሚያሳዩ ብዙ ውጫዊ መረጃዎች አሉ። ምናልባትም ሉቃስ ይህንን ታሪክ በመጽሐፉ ውስጥ የጨመረው ስምዖን ከክርስቲያን ማኅበረሰብ ጋር የነበረውን አስከፊ ግንኙነት በማመልከት ሐዋርያዊ ሥልጣን እንደሌለው ለማሳየት ይሆናል። የስምዖን የመጨረሻ ቃል ግራ አጋቢ የሚሆነው በቀደምት የመለወጥ ታሪኮች ላይ ትኩረት የሰጠን እንደሆነ ብቻ ነው። እንዲያውም ጠቅላላው የሉቃስ ትረካ በስምዖን ላይ አሉታዊ አንድምታ አለው። የእርሱ መዳን ወይም አለመዳን የታሪኩ ዋንኛ ጉዳይ አይደለም። ትኩረት የተሰጠው ለአጭር ጊዜ ክርስቲያን ነኝ በሚል ከቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት በመፍጠሩ ላይ ነው። ነገር ግን የጴጥሮስ አቀራረብ የስምዖን ክርስትና የውሸት እንደሆነ የሚያስረዳውን የሉቃስን ብያኔ የሚያንጸባርቅ ይመስላል።

የሉቃስን የ«ምን» እና «ለምን» ትረካ የሚሻው እንዲህ ዓይነቱ ሐቲት በጥሞና ደረጃ ብዙም አርኪ ላይሆን ቢችልም፥ የሐዋርያት ሥራን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመስማት የመጀመሪያው ወሳኝ ክፍል እንደሆነ ለማስገንዘብ እንፈልጋለን። በእያንዳንዱ ትረካው ወይም ንግግር ውስጥ እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር አንድን ነገር ሊያስተምረን እንደማይሞክር ግልጽ ነው። ነገር ግን በሁሉም ትረካዎች ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሊያስተላልፍልን የሚፈልገውን መልእክት በአጠቃላይ ለማሳየት ያገለግላሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ከሚቀርቡት ትረካዎችና እግዚአብሔር ሥራውን ለመፈጸም ከተጠቀመባቸው ሰዎች ብዙ ልንማር እንችላለን።

## የሐዋርያት ሥራ ሥነ አፈታት

ቀደም ብለን እዚህ ላይ የምናተኩረው በአንድ ጥያቄ ላይ ነው። በሐዋርያት ሥራ (እና በየትኛውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ) ውስጥ የሚገኙ ትረካዎች ለኋለኛዋ ቤተ ክርስቲያን በሞዴልነት የሚያገለግሉት እንዴት ነው? ቀድሞ ነገር እንዲህ ዓይነት አገልግሎትስ ይሰጣሉ ወይ? ይህም ማለት የሐዋርያት ሥራ ስለ መጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ከመግለጽ አልፎ በዘመናት ሁሉ ለምትኖር ቤተ ክርስቲያን የሚያስተላልፈው መልእክት አለ ወይ? እንዲህ ዓይነት መልእክት ካለ እንዴት ማግኘት ወይም ለማግኘት የሚያግዙትን መርሆዎች ማመልከት ይቻላል? ካልሆነስ የሞዴልነትን ጽንሰ አሳብ እንዴት እናደርገዋለን? በአጭሩ ለክርስቲያናዊ ዶክትሪን ወይም ክርስቲያናዊ ተሞክሮን ለመገንዘብ ታሪካዊ ምሳሌያዊነት የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?

ሁሉም ክርስቲያኖች ማለት ይቻላል ለተወሰነ ደረጃም ቢሆን ታሪካዊ ምሳሌዎችን ለሁሉም ክርስቲያኖች እንደሚያገለግሉ ሞዴሎች አድርገው እንደሚወስዱ መገንዘቡ ተገቢ ነው። ይህም ሆኖ፥ ብዙዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲጠቀሙባቸው አንመለከትም። በአንድ በኩል፥ ክርስቲያኖች አንዳንድ ትረካዎችን ልንከተላቸው የሚገቡ ግዴታዎች አድርገው ሲወስዱ፥ ሌሎቹን ግን ችላ ይሏቸዋል። በሌላ በኩል፥ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ራሱ የተለያዩ የአሠራር መንገዶች ተገልጸው ሳሉ አንዱን ብቻ ለመከተል ይፈልጋሉ።

በዚህ ረገድ የሚከተሉት አሳቦች እንደ ፍጹማዊ መመሪያዎች ላያገለግሉ ቢችሉም፥ ይህንን ሥነ አፈታታዊ ችግር ለመቅረፍ ያስችላሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## *አንዳንድ አጠቃላይ መርሆዎች*

እዚህ ላይ ዋንኛው ሥነ አፈታታዊ ጥያቄ በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደተከሰተ የሚገልጹ ትረካዎች በቀጣይዋም ቤተ ክርስቲያን ሊሆን የሚገባውን ምሳሌ የሚያኖሩ ናቸው ወይ? የሚል ነው። ከሐዋርያት ሥራ አንድ ሰው፥ «ይህንን ዛሬም ማድረግ አለብን?» የሚልባቸው አጋጣሚዎች አሉ? ወይስ «ይህንን ልናደርግ እንችላለን?» ማለቱ ብቻ ይበቃል።

ብዙዎች የሚጋሩት ግምታችን *መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ምን ማድረግ እንዳለብን ካልነገረን በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የተገለጸው ነገር ለክርስቲያኖች ሁሉ ሊሠራ አይችልም የሚል ነው። ወይም ደግሞ ደራሲው ሁሉም ክርስቲያኖች ሊከተሉት የሚገባ መሆኑን በሌሎች መንገዶች እንዳመለከተ መረዳት ይኖርብናል።* ይህንን ግምት ለመስጠት የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች አሉ።

በአጠቃላይ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚወጡ ዶክትሪናዊ አሳቦች በሦስት (ወይም በአራት) ምድቦች ሥር ይውላሉ። እነዚህም፥ (1) ክርስቲያናዊ ሥነ መለኮት (ክርስቲያኖች የሚያምኑት)፥ (2) ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር (ክርስቲያኖች ባሕርያቸው እንዴት መሆን እንዳለበት)፥ (3) ክርስቲያናዊ ገጠመኝና ተግባር (ክርስቲያኖች ሊያደርጓቸው የሚገቧቸው ነገሮች) ናቸው። ከእነዚህ ምድቦች ውስጥ እኛ ቀዳማይና ካልዓይ የምንላቸውን ሁለት የደረጃ ልዩነቶችን መመልከት ይቻላል። በቀዳማይ ደረጃነት የሚመደቡት በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ መልእክቶች ወይም ትእዛዛት ላይ የተመሠረቱ ዶክትሪናዊ (ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር የሚፈልጋቸው) አሳቦች ናቸው። በሁለተኛ ደረጃነት የሚመደቡት ከአንድምታ ወይም ከአርአያነት የሚወጡ አሳቦች ናቸው።

ለምሳሌ፥ በክርስቲያናዊ ሥነ መለኮት ምድብ እንደ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል፤ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞቷል፤ ደኅንነት የሚገኘው በእግዚአብሔር ጸጋ ነውና ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው የሚሉ አሳቦች ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ለማስተላለፍ የፈለጓቸው መልእክቶች በመሆናቸው ቀዳማይ ናቸው። በካልዓይነት የሚመደቡት የቀዳማይ መልእክቶች አመክንዮአዊ ፍሰቶች ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ በአንድምታ (አስከትሎት) የሚወሰዱ ናቸው። በዚህ ዓይነት የክርስቶስ አምላክነት ቀዳማይ ሲሆን፥ አምላክነቱ ከሰብአዊነቱ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ የሚነግረን ግን ካልዓይ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪንም ተመሳሳይ ልዩነት መመልከት ይቻላል። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ – የእግዚአብሔር እስትንፋስ

ያረፈበት መጽሐፍ መሆኑ ቀዳማይ ሲሆን፥ -የእግዚአብሔር እስትንፋስ ትክክለኛ ገጽታ ካልዓይ መሆኑ ነው። ይህ ማለት ግን ካልዓይ አሳቦች አስፈላጊዎች አይደሉም ማለት አይደለም። እነዚህ ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው በቀዳማይ አሳቦች ላይ በሚኖረው እምነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። እንዲያውም አጠቃላይ ሥነ መለኮታዊ እሴት ቀዳማይ አሳቦችን ከሚያስተናግዱበት ሁኔታ ጋር የተሳሰተ ሊሆን ይችላል።

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚኖርብን ሁልጊዜም ማለት ይቻላል፥ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌነት የሚከተሏቸው አሳቦች ክርስቲያናዊ ገጠመኝ ወይም ተግባር በተባለው ሦስተኛ ምድብ ውስጥ እንደሚውሉ ነው። ይህም ሁልጊዜም ከካልዓይ ምድብ ውስጥ ያስቀምጣቸዋል። ለምሳሌ፥ ክርስቲያኖች የጌታን እራት መውሰዳቸው ቀዳማይ ነው። ክርስቶስ ራሱ ክርስቲያኖች ይህንኑ እንዲያደርጉ ያዘዘ ሲሆን፥ መልእክቶችና የሐዋርያት ሥራም ያጠናክሩታል። ነገር ግን በሳምንት ወይስ በወር መወሰድ አለበት? የሚለው የተለያዩ ክርስቲያኖች የተለያዩ አቋሞች የሚይዙበት ሲሆን፥ የተመሠረተውም በትውፊትና በአርአያነት ላይ ነው። ይህም ቀዳማይ እንዳልሆነ ያስረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚያ ጥያቄ የሚሰጠው ቀጥተኛ ምላሽ የለውም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በጥምቀት (ቀዳማይ) እና በአጠማመቅ ሁኔታ (ካልዓይ)፥ በክርስቲያኖች መሰባሰብ (ቀዳማይ) እና ስንት ጊዜ ወይም መቼ መሰባሰብ እንዳለባቸው (ካልዓይ) ላይ የሚንጸባርቅ ነው። አሁንም ይህ ማለት ካልዓይ ጉዳዮች አስፈላጊዎች አይደሉም ለማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ ክርስቲያኖች ዓርብ ወይስ እሑድ መሰባሰብ አለባቸው? የሚለውን ለመወሰን የሚያስቸግር አሳብ ነው። ሁለቱም ግን በሌሎች ተሞክሮ ላይ የተመሠረቱ ሥነ መለኮታዊ ፋይዳዎች ናቸው።

እንዲተላለፍ የተፈለገው አሳብ ምንድን ነው? የሚለው ደግሞ ከዚህ ጉዳይ ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው። «መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው---» ማለቱ በእኛ መካከል የተለመደ ነው። አንድ ተራ ሰው ይህን ሲል አንድን ነገር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንዳስተማረ መናገሩ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ችግር የሚያጋጥመው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ስንገባ ነው። አንድ ነገር ተስማሚ በሚመስል መንገድ ስለተመዘገበ ብቻ ትምህርት እናገኝበታለን ማለት ይቻላል?

የእግዚአብሔርን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተላልፍ ከሚፈልገው አሳብ እንደምናገኝ የሚገልጸው አጠቃላይ የሥነ አፈታት ደንብ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚገባው ነው። ይህ በተለይ ለታሪካዊ ትረካዎች ሥነ አፈታት ወሳኝ ጉዳይ ነው። የታሪክ ጸሐፊው አንድን ክስተት በዘገባው ውስጥ

የሚጨምረው የመጽሐፉን ታላላቅ ዓላማዎች ስለሚያጎላ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚው ያንን ክስተት ከታሪክ ጸሐፊው ዕቅድ ውጭ የተለየ እሴት እንደሚያስተምር አድርጎ መውሰዱ ትክክል አይሆንም።

ምንም እንኳ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የወጠነው ትልቁ ዓላማ ለአንዳንዶች አከራካሪ ሊሆን ቢችልም፥ ቀደም ሲል በቀረበው ሐቲት ላይ በመመሥረት፥ ቤተ ክርስቲያን አይሁዳውያን አማኞች በኢየሩሳሌም ካቋቋሟት በኋላ እንዴት አሕዛብ የሚገኙባት ዓለም አቀፍ ክስተት ልትሆን እንደበቃች ለማሳየት የፈለገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። መንፈስ ቅዱስም ይህ በጸጋ ላይ ብቻ የተመሠረተው ደኅንነት በዓለም ሁሉ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳበረከተ ለመግለጽ እንደሚፈልግ እንገነዘባለን። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደፊት የምትገሠግሠውን ቤተ ክርስቲያን ምንም ሊረታት እንደማይችል የሚያስረዳው ተደጋጋሚ ዓላማ ሉቃስ አንባቢያኑ ለህልውናቸው ይህንን እንደ ሞዴል እንዲመለከቱ የፈለገ መሆኑን እንድናስብ ያደርገናል። በተጨማሪም የሐዋርያት ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ውስጥ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም በዚያ መጽሐፍ ውስጥ እንደምትታየው ወንጌል አሰራጭ፥ ደስተኛ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላች እንድትሆን የታቀደች ናት ብለን እንድናስብ ያደርገናል።

ነገር ግን ከሌሎች ጋር አብረው ሲወሰዱ ብቻ የሉቃስን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ የሚያሳዩ ዝርዝር ትረካዎችስ? እነዚህ ዝርዝሮች ተመሳሳይ የማስተማሪያ እሴት አላቸው? እነርሱም ለሁሉም ክርስቲያኖች እንደሚሆኑ ሞዴሎች ሊያገለግሉ ይችላሉ? በመሠረታዊነት አብዛኞቹ እንዲህ ዓይነት ዝርዝሮች ለዋናው አሳብ ድጋፍ የሚሰጡ ከመሆናቸውም በላይ ከትረካ ትረካ ዝርዝር ጉዳዮች ፍንትው ያለ መልእክት ስለማያስተላልፉ፥ በሞዴልነት ሊያገለግሉ አይችሉም ማለቱን እንመርጣለን።

ስለሆነም፥ የሐዋርያት ሥራ 6፡1−7ን ስንመለከት፥ ትረካው የሉቃስን አጠቃላይ ዓላማ እንዳገለገለ አስተውለናል። በዚህም የመጀመሪያውን ዐቢይ ክፍል ለማጠቃለልና በተመሳሳይ ጊዜ ሄለኒስቶችን ለማስተዋወቅ እንዳገለገለ ተመልክተናል። እንዲሁም በክርስቲያን ማኅበረሰብ መካከል ያለውን የመጀመሪያ ውጥረት ለማርገብ የተወሰደውን መልካም እርምጃ ለማመልከትም ፈልጎ ይሆናል።

ከዋናው አሳብ በተጓዳኝ ከዚህ ትረካ ውስጥ የምንማራቸው ሌሎች አያሌ ነገሮችም አሉ። ለምሳሌ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን አናሳ ቡድን ችግር ለማስወገድ የሚሻለው መንገድ፥ በቡድኑ

የተመረጠ የራሱ አመራር እንዲኖረው ማድረግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። እነርሱ ያደረጉት ይህንኑ ነበር። እኛም ይህንኑ የግድ ማድረግ አለብን? ሉቃስ እንደዚያ አድርጉ ስለማይል የግድ ማድረግ የለብንም። እንዲሁም ደግሞ ትረካውን ሲጽፍ ለክርስቲያኖች ሁሉ ተሞክሮውን የማስተላለፍ አሳብ እንደነበረው እንድናምን የሚያስችል ምክንያት አልተጠቀሰም። በሌላ በኩል፥ እርምጃው ጥሩ ውጤት ስለሚያስገኝ በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን መጨቃጨቅ ያስፈልጋል? ብሎ ማሰብም ይቻላል።

ዋናው ነጥባችን ሰዎች ከእንዲህ ዓይነት ታሪክ ምንም ዓይነት አሳብ ቢያወጡ፥ እንዲህ ዓይነት አሳቦች የሉቃስ ወንጌል ዋንኛ መልእክት አካላት መሆናቸውን ማስገንዘብ ነው። ይህ ማለት ግን ድጋፍ ሰጪ አሳቦች ውሸት ናቸው ወይም ሥነ መለኮታዊ እሴት የላቸውም ማለት አይደለም። ይህ ማለት ግን በዚያ ትረካ በኩል ለእኛ ሊተላለፍ የተፈለገው የእግዚአብሔር ቃል በቀዳሚነት መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተምረን ከፈለገው አሳብ ጋር የሚዛመድ ነው ማለት ነው።

ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚከተሉት መርሆች ለታሪካዊ ትረካ የሚያገለግሉ ሆነው እናገኛለን።

1. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ለክርስቲያኖች ሁሉ (ንዡርም ት ) እንደሚያስፈልግ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል በቀዳሚነት የትኛውም ትረካ ሊያስተላልፍ ከፈለገው አሳብ ጋር የሚዛመድ ነው።

2. የትረካውን ቀዳማይ ፍላጎት የሚደግፈው አሳብ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚጽፈው ደራሲ ለነገሮች ያለውን ግንዛቤ ሊያንጸባርቅ ይችላል። ነገር ግን ትረካው ሊያስተላለፍ የፈለገውን ያህል ጠንካራ እሴት ሊኖረው አይችልም። ይህ ማለት ግን ድጋፍ ሰጪ አሳቦች እውነት አይደሉም ወይም ለእኛ የሚያስተላልፉት መልእክት የላቸውም ማለት አይደለም። ለማለት የተፈለገው ምንም እንኳ በሌሎች ክፍሎች በግልጽ የቀረበውን አሳብ ለማጠናከር ቢረዱም፥ ድጋፍ ሰጪ አሳቦች ቀዳማይ መሆን የለባቸውም ነው።

3. ታሪካዊ ሞዴልነት ለክርስቲያኖች ሁሉ ያገለግል ዘንድ ሊተላለፍ ከተፈለገው መልእክት ጋር መዛመድ አለበት። የአንድ ትረካ ዓላማ አርአያነትን መመሥረት እንደሆነ ለማሳየት ከተቻለ እንዲህ ዓይነቱን ትረካ በሞዴልነት መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ያህል፥ በ6፡1–7 የሉቃስ ዓላማ ቤተ ክርስቲያን እንዴት መሪዎቿን መምረጥ እንዳለባት ለማሳየት መሆኑን በሐቲታዊ መሠረቶች ማረጋገጥ ከተቻለ፥ ከዚያን ዘመን በኋላ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ምርጫውን በተገለጸው መንገድ መፈጸም ይኖርባቸዋል። ነገር ግን የትረካው ፍላጎት

አርአያነትን መመሥረት ካልሆነ በኋላ ለሚመጡት ክርስቲያኖች የሚኖረው አርአያነት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀጣዩ ክፍል ውስጥ በቀረቡት መርሆች ላይ መመሥረት ይኖርበታል።

የዚህ ሁሉ አስቸጋሪነት ሰፊ በሆኑት የክርስቲያናዊ ልምምድና ተግባር አካባቢዎች አጥብቀን የምንሻውን መርሕ መንፈጉ ነው። ጥምቀት እንዴት ሊካሄድ እንደሚገባ፥ ስንት ዓመት የሆናቸው ሰዎች ሊጠመቁ እንደሚገባ፥ አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን በሚቀበልበት ጊዜ ሊታዩ ስለሚገባቸው የጸጋ ስጦታዎች ፥ በየስንት ጊዜ የጌታን እራት መውሰድ እንዳለብን፥ ወዘተ... ግልጽ የሆነ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። በክርስቲያኖች አካባቢ ከፍተኛ ክፍፍል የሚፈጠረውም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ነው። ሰዎች እነዚህን ልምምዶች ከሐዋርያት ሥራ ያውጡ ወይም በመልእክቶች ውስጥ ከተላለፉት አሳቦች በአስከትሎት ይውሰዱ፥ በተወሰነ አቅጣጫ መሥራታቸውን በመግለጽ ይሟገታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን በመድፈቅ ማጥመቅ እንደሚገባ፥ ሕጻናትን ማጥመቅ እንዳለብን፥ እውነተኛ የደኅንነት ልምምዶች ሁሉ የጳውሎስን ዓይነት አስደናቂዎች መሆን እንዳለባቸው፥ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃቸው እንደ ሁለተኛ የጸጋ ስጦታ በልሳን መገለጽ እንዳለበት፥ የጌታን እራት ዘወትር እሑድ መውሰድ እንደሚያስፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያዘዛባቸው ምንባቦች የሉም። ውኃ ውስጥ ጠልቆ መጠመቅን በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ እንግዲህ ምን እናደርጋለን? መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል? በዚህ ጉዳይ ላይ ከራሱ ከቃሉ፥ በሐዋርያት ሥራ 8፡38-39 «ወደ ውኃ ወረዱ» እና «ከውኃውም በወጡ ጊዜ» ከሚለው፥ ጳውሎስ ጥምቀትን እንደ መሞት፥ መቀበርና መነሣት አድርጎ ከሚገልጽበት (ሮሜ 6፡1-3) በመነሣት በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት የሚካሄደው በደፈቃ ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል።

በሌላ በኩል፥ በሰማርያ በነበረች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማጥመቂያ ገንዳ ስላልነበር በማጥለቅ ማጥመቁ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል መግለጽ ይቻላል። በማጥለቅ ለማጥመቅ የሚቻልባቸው ወንዞች በዚያ አካባቢ አልነበሩም። ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ዲዳኬ (100 ዓ.ም. አካባቢ) ለደፈቃ የሚበቃ ቀዝቃዛና ወራጅ ውኃ ሳይኖር ሲቀር በተጠማቂው ላይ ውኃ ማፍሰስ ይገባል በሚለው መንገድ ተጠምቀው ይሆን? በእርግጥ የዚህን ጥያቄ መልስ አናውቀውም። ዲዳኬ የተለመደው ትክክለኛ መንገድ ውኃ ውስጥ መድፈቅ ሲሆን፥ መጠመቁ ከአጠማመቅ መንገዱ በላይ አስፈላጊ እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል። ምንም እንኳ ዲዳኬ መጽሐፍ ቅዱሳዊ

ጽሑፍ ባይሆንም፥ ጥንታዊና ጤናማ ክርስቲያናዊ ሰነድ ነው። በመሆኑም ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ያልተሰጣቸውን ጉዳዮች እንዴት እንዳስተናገደች በማሳየት ሊረዳን ይችላል። የተለመደው (መደበኛ) ተግባር እንደ ወትሯዊ ሆኖ አገልግሏል። ነገር ግን ወትሯዊ ብቻ በመሆኑ ለሁልጊዜም የሚያገለግል ደንብ ሊሆን አልቻለም። ስለሆነም ይህንን አመራር ልንከተልና በመደበኛነትን ሁሉም ሊያደርገው እንደሚገባ አድገን ልንወስድ አይገባም። በዚህም ክርስቲያኖች ሁሉ አንድን ተግባር ሊያደርጉ እንደሚገባና ካላደረጉት የእግዚአብሔርን ቃል እንዳልታዘዙት መናገሩ ትክክል አይሆንም።

*አንዳንድ ውስን መርሆዎች*

በእነዚህ አጠቃላይ ምልከታዎችና መርሆዎች ላይ በመመሥረት ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሞዴሎች የአፈታት ጥበብ የሚከተሉትን ምክሮች እንሰጣለን።

1. ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሞዴል ላይ ተመሥርቶ ምስያን ( ን ልዡግይ) ለአሁኑ ዘመን ተግባራት እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን መጠቀሙ ከቶውንም ተገቢ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ የጌዴዎን ቆዳ ማንጠፍ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ጠቃሚ ምስያ እንደሆነ በማሰብ ብዙዎች ይጠቀሙበታል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለጌዴዎን እምነት ማጣት በቸርነቱ ምላሽ ቢሰጥና ለሌሎችም ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስድ ቢችልም፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ እንድናደርግ የመከረበት ሁኔታ የለም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለበት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ሁለት በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚጓዙ ምስያዎች ተፈጥረዋል። አንዳንዶች ይህ አማኞች በሚጠመቁበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚሞሉ የሚያስገነዝብ ምስያ መሆኑን በማመን ጥምቀት ሊያድን እንደሚችል የሚያስረዳ ዶክትሪን ይነድፋሉ። ሌሎች ደግሞ ክርስቶስ ቀደም ብሎ በመንፈስ ቅዱስ መወለዱን መሠረት በማድረግ ይህ ከደኅንነት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እንደምንጠመቅ የሚያስረዳ ነው ይላሉ። የክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለይፋዊ አገልግሎቱ የተሰጠው ኃይል መሆኑን ራሱ ሉቃስ እንደተገነዘበ መረዳቱ አዳጋች አይሆንም (ሉቃስ 4፡1፥ 14፥ 18ን ከሐዋርያት ሥራ 10፡38 ጋር አነጻጽር)። ነገር ግን ትረካው የትኛውንም ሥነ መለኮታዊ አቋሞች በምስያነት የሚያገለግል መሆኑ አጠራጣሪ ነው። በተለይም ደግሞ ከተራ ምስያነት አልፎ ለዶክትሪናዊ ትምህርት እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ መጠቀሱ ሁኔታውን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ክርስቲያኖች ሁሉ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተከሰተውን ድርጊት

መከተል ካለባቸው ሁላችንም ተሰቅለን በሦስተኛው ቀን ከሞት መነሣት ነበረብን።

2. ምንም እንኳ የደራሲው ቀዳማይ ዓላማ ባይሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ማብራሪያ የመስጠትና አንዳንድ ጊዜ «ምሳሌያዊ» እሴት አላቸው። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የአዲስ ኪዳን ሰዎች የብሉይ ኪዳንን ታሪካዊ ሞዴሎች የተጠቀሙበት በዚህ መንገድ ነበር። ጳውሎስ ለምሳሌ መለኮታዊ ደኅንነት አግኝቻለሁ ብለው በውሸት የሚኮፈሱትን ሰዎች ለማስጠንቀቅ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎችን ተጠቅሟል (1ኛ ቆሮ. 10፡1–13)። ክርስቶስም ደቀ መዛሙርቱ በዕለተ ሰንበት የፈጸሙትን ተግባር ለማጽደቅ የዳዊትን ምሳሌ እንደ ታሪካዊ አርአያነት ጠቅሷል (ማር. 2፡23–28 እና በወንጌላት ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ተመሳሳይ ንባቦች)።

እኛ ግን የአዲስ ኪዳን ደራሲያን አንዳንድ ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ጋር ያዛመዷቸውን ዓይነት ሐቲትና ምስያዊ ግምገማዎችን እንደገና የማካሄድ ሥልጣን የለንም። በተለይም መጽሐፍ ቅዱሳዊው ምሳሌ የአሁኑን ዘመን ተግባር በሚደግፍበት ጊዜ *ምሳሌው ተግባሩን እንደማያጸድቀው መገንዘቡ ተገቢ ነው።* ሰንበት ለሰው ልጅ መፈጠሩን ለማሳየት ሰዎች በመደበኛነት ኅብስት መብላት ወይም በሰንበት ቀን እሸት መቅጠፍ የለባቸውም። ነገር ግን ምሳሌው ሰንበትን አስመልክቶ አንድን መርህ ያብራራል።

እዚህ ላይ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል። አንድ ሰው አንድን የአሁን ጊዜ ተግባር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ለማጽደቅ በሚፈልግበት ጊዜ፥ የዚያ ተግባር መርህ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከተጠቀሰ ከስሕተት ይተርፋል። መርሁ በተጠቀሰበት ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ እንደ ቀዳማይ የደራሲው ዓላማ ሆኖ መገለጽ ይኖርበታል። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው የጽድቅ ቁጣውን (የራስ ወዳድነት ቁጣን ለመሸፋፈን) ለማጽደቅ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን ያነጻበትን ሁኔታ ቢጠቅስ ይህንኑ መርህ አላግባብ ይጠቀምበታል። በሌላ በኩል፥ በአሁኑ ዘመን የሚታየውን በልሳን የመናገር ጸጋ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሚገኘው ምሳሌ ብቻ ሳይሆን፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12–14 ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች በቀረበው ትምህርትም ላይ መመሥረት ይቻላል።

3. በክርስቲያናዊ ልምምዶችና ተግባራት ረገድ *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ሁሉም ክርስቲያን ሊያደርጋቸው እንደሚገባ ደንቦች ባይወሰዱም እንኳ፥ አንዳንድ ጊዜ ሊደገሙ እንደሚችሉ በምሳሌነት ሊያገለግሉ ይችላሉ።* የኋለኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ለመከተሏ አያሌ ምክንያቶች ያሉ ይመስላል። ነገር ግን በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ክርስቲያኖች አንድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ

ምሳሌ መከተል እንዳለባቸውና ይህ ካልሆነ ግን ታዛዥነት እንደጎደላቸው መናገሩ አከራካሪ ነው። ይህ በተለይ ተግባሩ ሊደረግ የሚገባው ሆኖ አፈጻጸሙ ወጥ በማይሆንበት ጊዜ የሚከሰት ነው። (ክርስቲያኖች ሁሉ በዚህ አሳብ እንደማይስማሙ መታወቅ አለበት። አንዳንድ እንቅስቃሴዎችና ዲኖሚኔሽኖች ሁሉም የአዲስ ኪዳን ምሳሌዎችን በአሁኑ ዘመን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን በሚያስገነዝቡ አሳቦች ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፥ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የአፈታት ጥበብ አዘጋጅተዋል። በተመሳሳይ መንገድ፥ ሌሎችም ይህንኑ አመለካከት በመጋራት ሉቃስም ራሱ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው በልሳን በመናገር ሊረጋገጥ እንደሚገባ ለማሳየት መፈለጉን በአብነት ይጠቅሳሉ። በእነዚህ ሁለቱም አቅጣጫዎች በይበልጥ ጥያቄው የሚያርፈው ከዚህ መርህ ትክክለኛነት ወይም ስሕተትነት ይልቅ ሉቃስ ታሪኩን በሚናገርበት ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ በፈለጋቸው አጠቃላይና ውስን ዓላማዎች ላይ ነው።)

የተወሰኑ ተግባራትን ወይም ምሳሌዎችን መድገም አለብን ወይ? የሚለው ጥያቄ ከሚከተሉት ግንዛቤዎች አንጻር ውሳኔ ሊሰጠው ይገባል። በመጀመሪያ፥ አንድን ምሳሌ ለመድገም ጠንካራ መሠረት ማግኘት የሚቻለው ምሳሌው ካለና በራሱ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተደገመ እንደሆነ ነው። ሁለተኛ፥ ምሳሌው ግልጽ ካልሆነና አንድ ጊዜ ብቻ ከተጠቀሰ፥ የኋለኞቹ ክርስቲያኖች ሊደግሙ የሚችሉት መለኮታዊ ድጋፍ ካለው ወይም በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከቀረበው አሳብ ጋር ተስማሚ ከሆነ ብቻ ነው። ሦስተኛ፥ በባሕል ላይ የተመሠረተ ከሆነ ደግሞ ጭራሹኑ ሊደገም አይገባውም ወይም ከሌላው ባሕል ጋር በሚስማማ መልኩ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል።

በእነዚህ መርሆዎች ላይ በመመሥረት መጥለቅ ትክክለኛው ጥምቀት የሚካሄድበት መንገድ መሆኑን፥ የጌታን እራት ዘወትር እሑድ መውሰዱ ብዙም ጠንካራ መሠረት እንደሌለውና ሕጻናትን ለማጥመቅ ምንም መሠረት እንደሌለ መመልከት ይቻላል። (ይህንን ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ አርአያነት ተነሥቶ መከራከር ቢቻልም፥ በዚህ ክፍል ካተኮርንበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አርአያነት መረጃ ማግኘቱ ቀላል አይሆንም።) በተመሳሳይ መንገድ፥ የክርስቲያን አገልጋይ እንደ ካህናት ማገልገልም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም።

እዚህ ላይ ችግሮችን ሁሉ ፈትተናል ብለን አናስብም። ነገር ግን እነዚህ ከሥራ ላይ ሲውሉ አሳቦች በመሆናቸው፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎችን በምታነብበት ጊዜ በሐቲታዊ መንገድ እንድታስብና ከከፍተኛ ሥነ አፈታታዊ ትክክለኛነት ላይ ለመድረስ እንድትጥር ይረዱሃል ብለን እናምናለን።